አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናልዝምና የኮሙዩኒኬሽን

ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መረሐግብር

በሀገር መከላከያ ሠራዊት ከ2001-2004 ዓ.ም. ድረስ ለርቀት ትምህርት መርሐግብር የቀረቡ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተናዎች ከመማሪያ መጽሐፉ ጋር ያላቸው ዝምድና

በ

ታለጌታ ይመር

ሰኔ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በሀገር መከላከያ ሠራዊት ከ2001-2004 ዓ.ም. ድረስ ሰርቀት ትምህርት መርሐግብር የቀረቡ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተናዎች ከመማሪያ መጽሐፉ ጋር ያላቸው ዝምድና

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናልዝምና የኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መረሐግብር

ለ በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን በማስተማር (TEAM) ኤም.ኤ.ዲግሪ

ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ታለጌታ ይመር

ሰኔ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናልዝምና የኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መረሐግብር

በሀገር መከላከያ ሠራዊት ከ2001-2004 ዓ.ም. ድረስ ለርቀት ትምህርት መርሐግብር የቀረቡ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተናዎች ከመማሪያ መጽሐፉ ጋር ያላቸው ዝምድና

በ

ታለጌታ ይመር

ሰኔ 2005 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

የአማካሪ ስም	ፊርማ
የፈታኝ ስም	ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቋ. ጥ. ተ.
በተ መረጃ ክፍት
ILS
LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

ምስጋና

በመጀመሪያ ይህ ጥናት ተጀምሮ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ያለምንም መሸማቀቅ እና ፍርሀት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ እየቀረብኩ ምክርና አስተያየታቸውን ይለግሱኝ ዘንድ በጠየኳቸው ጊዜ በሙሉ ፈቃደኝነትና ቅንነት የጥናቱን ረቂቅ ደጋግመው በማንበብ "ይህን አውጣ ፤ ይህን ጨምር " በማለት ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶ/ር አረጋ ኃይለሚካኤል (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ያለኝ አክብሮት ላቅ ያለ ነው።

የጥናቱ ዋነኛ የመረጃ ምንጭ የሆነውን የአራት ዓመት ፈተና ፈልጎ በመስጠት ትብብር ላደረገልኝ ለመምህር ተገኔ ማሞ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የተለያዩ ድጋፎችን ላደረጋችሁልኝ ተሠማ ማሞ፣ ታደሰ ኃይሉ እና ጌታሁን ማህለየሱስ ብድር ይግባችሁ።

በመጨረሻም ፣ይህን ጥናት በጥንቃቄ ለተየበችልኝ ወ/ሪት ፋሲካ ዘውዱ ምስጋናዬን ሳቀርብ ከልቤ ነው።

ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምስጋና i

ማውጫ ii

የሰንጠረዥ ማውጫ iv

አጠቃለሎ v

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 2

1.3. የጥናቱ ዓላማ 3

1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት 3

1.5. የጥናቱ ወሰን 4

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳናት 5

2.1. የፈተና ብያኔ 5

2.2. የቋንቋ ፈተና ጠቀሜታ (Use of Language Test) 5

2.3. የቋንቋ ፈተና ዓላማ 6

2.4.የፈተና ዓይነቶች 8

2.4.1. ቅድመ ችሎታን የመለኪያ ፈተና (Aptitudes Test) 8

2.4.2. ጥንካሬና ድክመትን የመለኪያ ፈተና (Diagnostic Test) 9

2.4.3. ችሎታን የመለኪያ ፈተና (Achievement Test) 10

2.4.4. ብቃትን የመለኪያ ፈተና (Proficiency Test) 12

2.5. የጥሩ ፈተና መሠረታዊ መገምገሚያ መስፈርቶች 12

2.5.1. አስተማማኝነት 13

2.5.2. ተገቢነት 14

2.5.3. ተተግባሪነት 15
2.6. የጥያቄ ማቅረቢያ ስልቶች 15
2.7. መርሐ ትምህርት ከመማሪያ መጽሐፍና ከፈተና ጋር ያለው ዝምድና 16
2.8. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት 18
ምዕራፍ ሦስት
የአጠናን ዘዴ 22
3.1. የጥናቱ የመረጃ ምንጮች 22
3.2. የክፍል እና የፈተና ናሙና አመራረጥ 22
3.2.1. የክፍል ደረጃ አመራረጥ 23
3.2.2. የፈተና ናሙና አመራረጥ 23
3.3. የመረጃ ምንጮች አተናተን ዘዴ 24
ምዕራፍ አራት
የጥናቱ ትንተና 25
ምዕራፍ አምስት 51
ማጠቃለያና አስተያየት 51
5.1 ማጠቃለያ 51
5.2 አስተያየት 53
ዋቢ ፅሑፎች
አባሪዎች

የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ ገጽ

ሠንጠረዥ 1፣ በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የክሂል እና የዕውቀት ዘርፍ መልመጃዎች ብዛት 28

ሠንጠረዥ 2 ፣ በሀገር መከላከያ ሠራዊት ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም.የተካተቱ ክሂሎች፣ የሥነ ጽሑፍና የሥነ ልሳን ዕውቀት ብዛት በመቶኛ ስሌትሲገለጹ 31

ሠንጠረዥ 3፣ በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ውስጥ ዝርዝር የጽፈት ትምህርት ይዘቶችን የሚመለከቱ መልመጃዎችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ 44

ሰንጠረዥ 4 ፣ ዝርዝር የጽሕፈት ክሂል ይዘትን በተመለከተ ከ2001 ዓ.ም.እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ የወጡ ጥያቄዎችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ 46

ሠንጠረዥ 5 ፣ በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ዝርዝር የሥነ ጽሑፍ ትምህርት ይዘቶች 48

ሠንጠረዥ 6፣ ከ2001 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ዝርዝር የሥነ ጽሑፍ ትምህርት ይዘት ያላቸው ጥያቄዎችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ 49

አጠቃለሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሀገር መከላከያ ሠራዊት ከ2001 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ለርቀት ትምህርት መርሐግብር የቀረቡ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፊተናዎች ከተማሪው የመማሪያ መጽሐፍ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው። ጥናቱን ከግብ ለማድረስም ከ2001ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ፊተናዎችና የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ በዋና የመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል።ከዚህ በላይ በተጠቀሱት የመረጃ ምንጮች አማካይነት የተገኙት መረጃዎች በቁጥርና በመቶኛ ስሌት እየተሰሉ በዓይነትና መጠናዊ የአተናተን ስልት ከተተነተኑ በኋላ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል።በሀገር መከላከያ ሠራዊት ከ2004 ዓ.ም ድረስ በርቀት ትምህርት መርሐግብር የተዘጋጁት የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፊተናዎች የጽሕፊት ክሂልን ከሚመለከቱ ጥያቄዎች በስተቀር ሁሉም ጥያቄዎች ከተማሪው የመማሪያ መጽሐፍ ጋር እጅግ የጠበቀ ዝምድና እንዳላቸው፣ የጽሕፊት ክሂል ጥያቄዎችም ቢሆኑ እንደሌሎቹ የክሂል ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ አይዛመዱ እንጂ ሁሉም ጥያቄዎች ከመማሪያ መጽሐፍ ውጭ የወጡ እንዳልሆኑ ከተገኙት የመረጃ ምንጮች ለማረጋገጥ ተችሏል። በመጨረሻም ፊተናዎቹና የመማሪያ መፅሐፉ ያላቸው ተዛምዶ የጠበቀ በመሆኑ በቀጣይ የሚዘጋጁ ፊተናዎችም በዚሁ መቀጠል እንዳለባቸው፣ ነገር ግን የተገቢነትና የክሂል ጥያቄዎች አለመመጣጠን ችግር መኖሩ በጥናቱ ስለተረጋገጠ ወደፊት በሚዘጋጁ ፊተናዎች ላይ ትኩረት ቢደረግ መልካም እንደሆነ በአጥኚው አስተያየት ተሰጥቷል።

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ሥር አምስት ዋና ዋና መሰረታዊ ነጥቦች ተዘርዝረዋል። እነዚህም መሰረታዊ ነጥቦች፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ አስፈላጊነትና የጥናቱ ወሰን የሚሉ ናቸው።

1.1. የጥናቱ ዳራ

ስለ ፈተና ምንነት በርካታ ምሁራን የሰጡት ብያኔ በአገላለፅ ካልሆነ በስተቀር በመሰረታዊ ሀሳባቸው ተመሳሳይ ነው፤ ይኸውም ፈተና ተማሪው የተማረውን ትምህርት ምን ያህል ተገንዝቦታል? ትምህርቱን በምን ያህል ደረጃ ተክታትሏል? ተማሪው የተመደበለትን ትምህርት ካጠናቀቀ በኋላ ስለ ትምህርቱ ያለው ግንዛቤ ምን ያህል ዳብሯል? ወዘተ. የሚሉትን ጉዳዮች ለማወቅ የሚያስችል መሳሪያ ነው የሚለው የሁሉም ምሁራን መሰረታዊ ሀሳብ ነው።

Richard (1991፣33) ፈተና በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በተማሪው ላይ የታየውን ዕውቀትና የባህርይ ለውጥ መመዘኛ እንደሆነ ገልጿል። Heaton (1975፣8-9) የፈተናን ብያኔ በተመለከተ ሲገልፅ፣ "የቋንቋ ፈተና ዓላማ ተማሪው ያካበተውን የታላሚውን ቋንቋ ዕውቀት ወይም ብቃት መገምገም ነው።" አበበ (1975) የፈተናን ጠቀሜታ በተመለከተ Wuod (1961፣3) ጠቅሶ እንደሚከተለው ገልጾታል፤ "በመሰረቱ ፈተናዎች እንደ መለኪያ መሳሪያነት ያገለግላሉ። ሌላው እጅግ ጠቃሚነታቸው የማስተማሩን ሂደት በቀጥታ ያግዛሉ፤ ተማሪዎችም ፈተና እንደሚፈተኑ ሲያውቁ በጊዜው ያነባሉ።"

ፈተናዎች በሚዘጋጁበት ወቅት የመማሪያ መፅሐፉን እንዲሁም መርሐ ትምህርቱን መሰረት አድርገው ሊዘጋጁ ወይም ላይዘጋጁ ይችላሉ። ይህ የሚወሰነው እንደ ፈተናው ዓይነት እና ዓላማ ነው። ለምሳሌ የፈተናው ዓይነት የቸሎታ መለኪያ ፈተና ከሆነ የሚዘጋጀው ፈተና በመርሐ ትምህርቱና በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱ የትምህርት ይዘቶችን መሠረት በማድረግ ነው።

ነገር ግን ፈተናው የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ከሆነ በመማሪያ መፅሐፉና በመርሐ ትምህርቱ ላይ ሊመሠረት ይችላል። ምክንያቱም የፈተናው ዓይነት እንደ ፈተናው ዓላማ ይወሰናልና ነው። በአጠቃላይ ከምሁራኑ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ፈተና ተማሪው ከክፍል ወደ ክፍል እንዲዘዋወር ወይም በነበረበት ክፍል እንዲቆይ ማድረጊያ ሳይሆን፣ የተማረውን ትምህርት ምን ያህል ተገንዝቦታል? የመማር ማስተማሩ ሂደት ምን መምሰል አለበት? በተማሪው ላይ የታየው የዕውቀትና የባህርይ ለውጥ ምን ይመስላል? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ ነው።

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ጥናቱ ትኩረት ያደረገው በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር ከ2001ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ የተዘጋጁ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተናዎች በተጠቀሱት ነጥቦች ውስጥ ከተዘጋጁት የመማሪያ መጽሐፉ ጋር ያላቸውን ዝምድና በመፈተሽ ላይ ነው። አጥኚው ይህንን ጥናት ለማካሄድ የፈለገበት ምክንያት፣

1. የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የተማረና ዘመናዊ የሠራዊት አባላትን ለመገንባት ባለው ዕኑ እምነት ከ1995 ዓ.ም. ጀምሮ ሠራዊቱ ባለበት ቦታ ሆኖ እንዲማር የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር ጀመረ። እንሆ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ ለአስር ጊዜ ያህል የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን ብሔራዊ ፈተና አስፈትኗል።ፈተናው የሚዘጋጀውም ለመደበኛ የክልል ተማሪዎች ከሚዘጋጀው ፈተና የተለየ ነው።

   ስለዚህ ለአንድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የስምንተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ለብቻ ሲዘጋጅ የመጀመሪያ በመሆኑ እስከ አሁን ድረስ በተዘጋጁ ፈተናዎች ላይ ምንም ዓይነት የተካሄደ ጥናት ባለመኖሩ፣

2. አጥኚው ከላይ በተጠቀሰው መስሪያ ቤት ውስጥ የርቀት ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ መምህር በመሆኑ የስምንተኛ ክፍል የብሔራዊ ፈተናዎችን መልስ ከፈተናዎች ድርጅት ተቀብሎ ያርማል፤ አማካኝና ፐርሰንታይል ያወጣል፤

ካርድ ይሰራል። በመሆኑም ፈተናውን የሚያዘጋጁት ባለሙያዎች በፈተናዎች አወጣጥ ዙሪያ ምን ያህል ትኩረት እንደሚያደርጉ ለማወቅ ነው።

1.3. የጥናቱ ዓላማ

በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም. ለስምንተኛ ክፍል የተዘጋጁ ብሔራዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ መፈተሽ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ሲሆን፣ አጠቃላይ ዓላማውን መሰረት ያደረጉ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፤

1. የስምንተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የችሎታ መለኪያ ፈተና በመሆኑ የችሎታ መለኪያ ፈተና ባህርያትን መሠረት ያደረገ መሆኑን መመርመር፣
2. ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም. የተዘጋጁት የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ተገቢነት ያላቸው መሆናቸውን መፈተሽ፣
3. ለስምነተኛ ክፍል የተዘጋጁት ፈተናዎች የያዟቸውን ክሂሎች እና የዕውቀት ዘርፎች እንዲሁም ዝርዝር የትምህርት ይዘቶችን መመርመር ነው።

1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

ማንኛውም በዓላማ ላይ የተመሰረተ ጥናት ከተካሄደ በኋላ ይበዛም ይነስም የሚያበረክተው አስተዋፅኦ እንደሚኖር ግልፅ ነው። በመሆኑም ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፤

1. ከ2001ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ ባሉት ዓመታት ውስጥ የተዘጋጁት ፈተናዎች የጥሩ ፈተና መለኪያ የሆነውን ተገቢነት መሠረት አድርገው መዘጋጀት አለመዘጋጀታቸውን ያሳያል፤
2. የተዘጋጁት ፈተናዎች ከተማሪው የመማሪያ መፅሐፍ ጋር የተዛመዱ መሆን አለመሆናቸውን ይጠቁማል፤

3. ጥናቱ በርቀት ትምህርት መርሐ ግብር በስምንተኛ ክፍል ብሔራዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ላይ ሲደረግ የመጀመሪያው ጊዜ በመሆኑ ከዚህ በኋላ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደ መነሻ ሆኖ ያገለግላል።

1.5. የጥናቱ ወሰን

የአንድን የክፍል ደረጃ ፈተና በተመለከተ በዝርዝርና በጥልቀት ለመመርመር ሠፊ ጊዜንና፣ በቂ ገንዘብንና ችሎታን ይጠይቃል። በመሆኑም ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ብቻ ይሆናል። ይኸውም፡-

ሀ. ከ2001ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ የተዘጋጁት የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተናዎች ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር ያላቸው ዝምድና ምን ይመስላል?

ለ. ፈተናዎቹ ሲዘጋጁ የጥሩ ፈተና መስፈርት የሆነውን ተገቢነት መሠረት ያደረጉ ናቸው ወይ?

ሐ. የተዘጋጁት ፈተናዎች የችሎታ መለኪያ ባሕርይን መሠረት አድርገው ተዘጋጅተዋል?

መ. ለስምንተኛ ክፍል የተዘጋጁት ፈተናዎች የያዟቸው ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች ምን ይመስላሉ? ዝርዝር የትምህርት ይዘቶቹስ ምን ምን ናቸው?

በሚሉት ነጥቦች ላይ ብቻ ይወሰናል።

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳናት

2.1. የፈተና ብያኔ

ሰለ ፈተና ምንነት የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል።የብዙዎቹ ብያኔ የሚያጠነጥነው በአንድ መሠረታዊ ጉዳይ ላይ ነው። ይኸውም ፈተና ተማሪው የተማረውን ትምህርት ምን ያህ ያስታውሰዋል? የሚለውን ጥያቄ መመለስ የሚያስችል መሳሪያ ነው በማለት ይገልፃሉ።

Bachman (1990፣18) መለካት (measurement)፣ ምዘና(test) እና ግምገማ (evaluation) የሚሉትን ስያሜዎች ብዙ ሠዎች ተመሣሣይ እንደሆኑ ቢረዱትውም ልዩነትና ተመሣሳይነት እንዳላቸው ገልፀዋል።

ታረቀኝ (1993) Bachman (1990፡18) ጠቅሶ እንደሚከተለው ገልጿል፤ "መለካትና ምዘና የክትትሉን ውጤት መጠን ያሣያሉ። ምዘና የተለየ የባህሪ ዓይነትን ለማወቅ የሚዘጋጅ ነው። ግምገማ ውሳኔ መስጠትን ይጨምራል፣ በመሆኑም ከመለካት ይለያል። መለካትና ምዘና በግምገማ ይጠቃለላሉ። ምዘና ደግሞ አንዱ የመለኪያ መሣሪያ ነው"

2.2. የቋንቋ ፈተና ጠቀሜታ (Use of Language Test)

የቋንቋ ፈተና የራሱ የሆነ የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው ምሁራኑ ያስረዳሉ። Bachman (1990፡ 54) የቋንቋ ፈተና ጠቀሜታን አስመልክተው ሲገልፁ "የእያንዳንዱን የፈተና ጠቀሜታ በሚመለከት ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ ቢኖር በፈተና አዘጋጃጀትና በተማሪዎች ውጤት አተረጓጎም ጊዜ ከፍተኛ አገልግሎት እንዳለው ነው" ይላሉ።

ከባችማን ሐሳብ መረዳት እንደሚቻለው የተማሪውን ውጤት መነሻ በማድረግ ትምህርቱ በምን መልኩ እየተካሄደ እንደሆነ፣ ተማሪዎች ድክመት ያለባቸው በየትኛው

ከሂል ላይ ነው? የሚለውን ለመረዳት ፈተናዎች በምን መልኩ መዘጋጀት እንዳለባቸው፣ ወዘተ ለመገንዘብ የቋንቋ ፈተና አስፈላጊ መሆኑን ነው።

Bachman (1990፡44) ፈተና ሁለት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይገልፃሉ።

1. በትምህርቱ እቅድ ላይ ውሳኔ ለመስጠት እንደ መረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፤
2. በቋንቋ ለመዳና በቋንቋ ትምህርት ላይ የሚታዩትን ችሎታዎችና ፍላጎቶች ለመመርመር አመላካች ነው፤

ከዚህ በተጨማሪ ዳንኤል (1997) ሉየስ ጃክርሜልን ጠቅሶ የፈተናን ጠቀሜታ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች መድቧቸዋል፤

ሀ. ፈተናዎች ልዩ ጥናት የሚያስፈልገውን የሰው ልጅ ለማወቅ ይረዳሉ፤

ለ. ፈተናዎች አስተማሪው ለማቅረብ የሚረዳውን እውነተኛ የድክመትና የጥንካሬውን ሥዕል ለመለየት ያስችላሉ፤

ሐ. ፈተናዎች ትምህርትን ለመምራትና ለማነቃቃት ይረዳሉ።

በአጠቃላይ የቋንቋ ፈተና ጠቀሜታን አስመልክተው ምሁራኑ ያቀረቧቸውን መሠረታዊ ሐሳቦች ስንመለከት፣ ፈተናዎች ቀደም ሲል ይካሄድ የነበረውን የመማር-ማስተማር ሂደት ምን ይመስል እንደነበር ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ፤ የተማሪውን የመማር ፍላጎት የበለጠ ያነቃቃሉ፤ መምህሩ የተማሪዎችን ውጤት መነሻ በማድረግ ለቀጣይ ምን ማድረግ እንደሚገባው ይጠቁማሉ፤ የተማሪውን ብቃትና ፍላጎት በሚመለከት ምርምር ለማድረግ እንደ መረጃ ምንጭነት ሆነው ያገለግላሉ።

2.3. የቋንቋ ፈተና ዓላማ

ማንኛውም ፈተና የራሱ ዓላማ ይኖረዋል፤ የፈተናውም ዓይነት እንደ ዓላማው ይወሰናል። የቋንቋ ፈተና ዓላማን በሚመለከት ተስፋዬ (1981፡119) እንደሚከተለው ገልፀውታል፤

የቋንቋ ፈተና ከሚሰጥባቸው ዓላማዎች መካከል ቅድመ ችሎታን ለመላካት፣ የተደረሰበትን ፈተና ለመለካት፣ ችሎታን ለመለካትና ጥንካሬና ድክመትን ለመለካት የሚወጡ ወይም የሚዘጋጁ ፈተናዎች ይገኙበታል#... የፈተናን ዓላማ ወይም የምንፈትንበትን ዓላማ መገንዘብንም ይጠይቃል# በተለይ የሚዘጋጀው ፈተና በተወሰነ የትምህርት ፕሮግራም ላይ የተመሠረተ ከሆነ የትምህርቱ ዓላማ መታወቁ ግድ ነው# ምክንያቱም ፈተናው ሊያረጋግጥልን የሚጠበቅበት ተማሪው በቀረበለት ትምህርት የሚፈለግበትን ዓላማ መጨበጥ አለመጨበጡን ወይም የተፈለገውን ዓላማ ከግብ ማድረስ አለመድረሱን ነው#

Bachman (1990፡3) የፈተናን ዓላማ አስመልክተው ሲገልፁ "አብዛኛውን ጊዜ የቋንቋ ፈተናዎች የተለያዩ የቋንቋ ማስተማር ስልቶችን ወይም አቀራረቦችን ውጤታማነት ለመመዘን እንደ መረጃ ምንጭነት ሆነው ያገለግላሉ#

ከባችማን ሀሳብ መረዳት የሚቻለው መምህራን የራሳቸው የሆነ የትምህርት አቀራረብ ስልት አላቸው# ነገር ግን የአቀራረብ ስልቱ ውጤታማ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል# ይህንን ደግሞ ቁልጭ አድርጎ ሊያሣየን የሚችለው ፈተና ነው# ስለዚህ አንዱ የፈተና ዓላማ የመምህሩን የማስተማር ስልት መፈተሽ ነው#

Heaton (1991፡5)፣ "የቋንቋ ፈተናዎች ሁለት ዓበይት ዓላማዎችን ይዘው ይዘጋጃሉ# አንደኛው ተማሪው በትምህርቱ የተነቃቃ እንዲሆን ማድረግ ሲሆን ሁለተኛው ተማሪው የደረሰበትን የቋንቋ ብቃት መገምገም ነው#

Davies (1968:70)፣ "አንድ ፈተና የተፈለገውን ነገር እንዲመዝን ከተፈለገ፣ በመጀመሪያ ለምን ዓላማ እነደተዘጋጀ ማወቅ ያስፈልጋል" በማለት ገልፀዋል#

Madsen (1983)፣ የተለያዩ ፈተናዎች የሚዘጋጁት የተለያዩ ዓላማዎችን ከግብ እንዲያደርሱ ስለሆነ በአይነታቸውም ሆነ በአቀራረባቸው አንድ ዓይነት ሊሆኑ አይችሉም፤ እያንዳንዱ ፈተና የራሱ የሆነ ዓላማ አለው# ለምሳሌ የድክመትና ጥንካሬ መለኪያ ፈተና ዓላማው የተማሪውን ድክመትና ጥንካሬ መጠቆም፣ ማስተካከያዎች እንዲደረጉ ክፍተቶችን ማሣየት፣ መደገፍና ማበረታታት ነው#

ከላይ በቀረቡው የምሁራን ሐሳብ መረዳት የሚቻለው የቋንቋ ፈተና የሚዘጋጀው በዘፈቀደ ሳይሆን ዓላማ ተወስኖለት መሆኑን ነው። ዓላማው ከታወቀ የፈተናውን ዓይነት መወሰን በጣም ቀላል ነው።

ለምሣሌ የፈተናው ዓላማ ችሎታን መለካት ከሆነ የሚዘጋጀውም የፈተና አይነት የችሎታ መለኪያ ፈተና እንጅ ብቃትን የመለኪያ ፈተና ሊሆን አይችልም።

በአጠቃላይ የፈተና ዓላማ ተማሪው የቀረበለትን ትምህርት መሠረት በማድረግ የሚፈለግበትን ግብ መምታት አለመምታቱን መገምገም፣ የመምህሩን የማስተማር ስልት ውጤታማነት መመዘን፣ ተማሪው ትምህርቱን በንቃትና በጉጉት እንዲከታተል ማድረግ ነው።

2.4.የፈተና ዓይነቶች

አብዛኛዎቹ ምሁራን የሚስማሙባቸው የፈተና አይነቶች አራት ሲሆኑ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፤

2.4.1. ቅድመ ችሎታን የመለኪያ ፈተና (Aptitudes Test)

"ይህ የፈተና ዓይነት ለአንድ የቋንቋ ትምህርት የሚቀርብ ተማሪ ቋንቋውን ለመማር ወይም ለትምህርቱ የተዘጋጀውን ፕሮግራም ለመከታተል ያለውን ችሎታ ለመለካት የሚሰጥ ፈተና ነው። ይህ ፈተና እንዲገልፅ የሚፈለገው ወይም የሚጠበቀው ተማሪው የተዘጋጀውን ፕሮግራም ሊከታተል ይችላል ወይም አይችልም የሚለውን ነው።" ተስፋዬ (1981፡123)

Harrison (1983፡4) አንድ አዲስ ተማሪ ከሌሎቹ ቡድኖች ጋር ተቀላቅሎ ለመማር ደረጃው ይፈቅዳል ወይስ አይፈቅድም? ችሎታው ከሌሎቹ ተማሪዎች ጋር ተቀራራቢ ነው ወይ? የሚለውን ለማወቅ የሚሰጥ የፈተና ዓይነት እንደሆነ ገልጿል ።

Alderson (1995፣292) የደረጃ ፈተና "Placement test" በማለት የሰየመው ሲሆን "ፈተናው የሚዘጋጀው የተማሪውን የቋንቋ ችሎታ ለመፈተሽና ለዚያ ደረጃ የተዘጋጀውን ትምህርት ለመከታተል መመጠን አለመመጠኑን ለመገንዘብ ነው።

ከላይ የቀረቡትን ሁሉንም ሀሳቦች ለመረዳት ብንሞክር የአገላለፅ እና የስያሜ ልዩነት ካልሆነ በስተቀር የፅንስ ሀሳብ ልዩነት የለቸውም። በመሆኑም ሁሉም ምሁራን የሚያትቱት የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና አንድን የቋንቋ ትምህርት ለመከታተል የተዘጋጀ ተማሪ ያለውን የቀደመ ችሎታ ለመፈተሽ የሚሠጥ የፈተና አይነት ነው።

2.4.2. ጥንካሬና ድክመትን የመለኪያ ፈተና (Diagnostic Test)

ጥንካሬና ድክመትን የመለኪያ ፈተናን በሚመለከት አልደርሰን (1995፡11-12) እንዲህ በማለት ይገልፃል። "ተማሪው በትምህርቱ ሂደት ያጋጠመውን አስቸጋሪ የትምህርት ይዘት በመለየት ተገቢውን ድጋፍ ለመስጠት ታስቦ የሚዘጋጅ የፈተና ዓይነት ነው። ለምሳሌ ተማሪው በየትኛው ክሂል ላይ እገዛ ይፈልጋል? በሰዋስው አጠቃቀም ረገድ ድክመቱ ምን ላይ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ከፍተኛ ጠቀሚታ አለው።

Baker (1989:3) እና Harrison (1983:6) የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተናን አስመልክተው ሲገልፁ፣ ድክመትን ለመለካት የሚዘጋጅ ፈተና በመማር-ማስተማር ሂደት ላይ የሚከሠቱትን ችግሮች ነቅሶ ለማውጣት ወይም ለመለየት ጠቀሚታው የጎላ ነው ይላሉ። Rivers (1968፣ 288)፣ የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተናዎች ክፍል ውስጥ በሚያስተምሩ መምህራን ተዘጋጅተው ለተማሪዎች የሚቀርቡ በመሆናቸው መደበኛ ያልሆኑ ፈተናዎች ናቸው፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ፈተናዎች የመምህራንና የተማሪዎችን ድክመትና ጥንካሬ ለማወቅ ያስችላሉ።

ተስፋዬ (1981፡123) በበኩላቸው የጥናካሬና ድክመት መለኪያ ፈተናን አስመልክተው የሚከተለውን ብለዋል።

> *ይህ የፈተና ዓይነት መምህራን ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች በየጊዜው የሚሰጡት ነው። ዓይነተኛ ዓላማውም የቀረበውን ትምህርት ተማሪዎቹ ምን ያህል እንደተገነዘቡት ወይም እንዳልተገነዘቡት ወይም የትኛው የትምህርት ዘርፍ በሚገባ እንደታወቀና የትኛው ደግሞ እንዳልታወቀ ማሣየት ነው። በውጤቱም መሠረት መምህሩ አስፈላጊውን ዝግጅት ለማድረግ ይቻለዋል።*

Lado (1961፡369) የጥናካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና ከችሎታ መለኪያ ፈተና ጋር የሚቀራረብ ሲሆን የሚለይበት ዋነኛ ነጥብ ቢኖር የጥንካሬና ድክመት ፈተና ዋነኛ ዓላማው በቋንቋው ውስጥ በተወሰኑ የቋንቋ ክሂሎች ወይም አላባዊያን (elements) ተማሪው ያለበትን ድክመትና ጥንካሬ ለመመርመር የታቀደ መሆኑ ነው።

በአጠቃላይ ስለ ድክመትና ጥንካሬ መለኪያ ፈተና ምሁራኑ ከሰጡት ገለፃ መረዳት የሚቻለው በትምህርት ሂደት ውስጥ ተማሪው በየትኛው ክሂል ላይ ድክመት እንዳለበት በመለየት ተገቢውን ዕገዛ የሚደረግበትን መንገድ መፈለግ ነው።

2.4.3. ችሎታን የመለኪያ ፈተና (Achievement Test)

የችሎታ መለኪያ ፈተና መሠረት የሚያደርገው የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርትና የትምህርት ፕሮግራምን እንደሆነ በርካታ ምሁራን ይገልፃሉ።

Heaton (1975"163) የችሎታመለኪያ ፈተና በብዙ መንገዶች ከሂደታዊ ፈተና (Progress tests) ጋር ይመሣሰላል። በየትምህርት ቤቱ በየዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚሰጡት ፈተናዎች የችሎታ መለኪያ ፈተናዎቹ ናቸው። የሚዘጋጁትም መርሃ ትምህርቱን መሠረት በማድረግ ነው።

Alderson (1995፡11-12) የችሎታ መለኪያ ፈተና የሚሠጠው አንድ የቋንቋ ሥልጠና (ትምህርት) መርሐ ግብር ከተጠናቀቀ በኋላ በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ ተመሥርቶ የሚዘጋጅ የማጠቃለያ ፈተና ነው።

ፀጋዬ (1997)፣ እንደገለፁት የችሎታ መለኪያ ፈተና በአብዛኛው መምህራንን የሚመለከት በመሆኑ በማዘጋጀቱም ሆነ በመፈተኑ ተግባር የሚሣተፉት እነሱ ናቸው። ይህን የፈተና ዓይነት Hughes (1989:10) ሲገልፁ፣ አንደ ብቃት መለኪያ ፈተና ሣይሆን በአንድ የቋንቋ ትምህርት ዓላማና ይዘት ላይ በመመስረት ተማሪዎች የቀረበላቸውን ትምህርት ምን ያህል ተገንዝበውታል የሚለውን የመገምገም ዓላማ ያለው የፈተና ዓይነት ነው።

Feldman (1984፡273) እና Heaton (1975፣163)፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና በአብዛኛው በአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ በመምህሩ የሚዘጋጅና

የተማሪዎችን እውነተኛ ዕውቀት፣ ክህሎትና ሌሎች ብቃቶችን ለመለካት የሚያስችሉ ናቸው በማለት ይገልፃሉ።

አበበ (1975) የችሎታ መለኪያ ፈተናን አስመልክቶ ከዚህ የሚከተለውን አስፍሯል፤

> *በተለያዩ የትምህርት ተቋማት ያሉ ተማሪዎች በአንድ ወቅት በጋራ የሚወስዱት የፈተና አይነት ነው። ለዚህም የተዘጋጀ የትምህርት መርሐ ግብር አለ። የችሎታ መለኪያ ፈተና በሁለት ሊከፈል ይችላል።*
>
> 1. *በትምህርት ቤት ውስጥ የሚዘጋጅ የችሎታ መለኪያ ፈተና (classroom achievement test)*
>
> 2. *መደበኛ የችሎታ መለኪያ ፈተና (standardized achievement test)*
>
> *በትምህርት ቤት የሚዘጋጅ የችሎታ ፈተና በአንድ መምህር ሊዘጋጅ ይችላል። መምህሩ በየትኛው የትምህርት ዘርፍ ላይ ይበልጥ ትኩረት አድርጎ እንዳስተማረው ስለሚያውቅና የተማሪውን ደረጃ መገመት ስለሚችል በቀላሉ ማዘጋጀት ይቻላል።*
>
> *መደበኛ የችሎታ መለኪያ ፈተና በሀገራችን በብሄራዊ ደረጃ በዓመት አንድ ጊዜ የሚሰጥ ፈተና ነው። የዚህ ዓይነቱ ፈተና በክፍል ውስጥ ከሚሰጠው ፈተና ይለያል።ምክንያቱም ፈተናው በአንድ መምህር ብቻ የሚዘጋጅ ሣይሆን ፈተና በማዘጋጀት የረጅም ጊዜ ልምድና ችሎታ ያላቸው የትምህርት ባለሙያዎች በቡድን የሚያዘጋጁት ፈተና ነው።*

በአጠቃላይ ምሁራኑ ካቀረቧቸው ገለፃዎች መረዳት የሚቻለው፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና መሠረት የሚያደርገው መርሐ ትምህርቱንና የመማሪያ መጻሕፍቱን ነው። በመሆኑም አንድ መርሐ ግብር ከተጠናቀቀ በኋላ በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚሰጥ ፈተና የችሎታ መለኪያ ፈተና ነው ለማለት እንችላለን።

2.4.4. ብቃትን የመለኪያ ፈተና (Proficiency Test)

ይህ የፈተና ዓይነት በአንድ በተወሰነ የቋንቋ ትምህርት መርሃ ግብር ላይ ተመስርቶ የሚዘጋጅ ሣይሆን የተማሪውን የቀደመ ዕውቀት ለመፈተሽ የሚዘጋጅ ፈተና እንደሆነ ምሁራኑ ይገልፃሉ።

Alderson (1995፡11-12) "ይህ የፈተና ዓይነት በአንድ በተወሰነ የቋንቋ ትምህርት መርሐ ግብር ላይ አይመሰረትም። ዓላማው ተማሪው በተለያየ ወቅት በሥልጠናና ቀደሞ በትምህርት ያገኘውን የቋንቋ ችሎታ ዳራን ለማረጋገጥ የሚሰጥ ፈተና ነው።

Harrison (1983፡7) የብቃት መለኪያ ፈተና ዋና ዓላማ የተማሪውን ወቅታዊ ችሎታ መፈተሽ፣ ተማሪው በተማረው ቋንቋ ምን ሊያደርግበት ይችላል? ወቅታዊ አቋሙ ወደፊት መሆን ለሚፈልገው ነገር ምን ያህል በቂው ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ነው።

ተስፋዬ (1981።123) ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት ተውጣጥተው በአንድ ክፍል ወይም በአንድ ተቋም ውስጥ ለመማር የሚመጡ ተማሪዎች ያላቸውን የቋንቋ ችሎታ ለማወቅ የሚዘጋጅ ፈተና ነው።

በአጠቃላይ ምሁራኑ ካቀረቧቸው ማብራሪያዎች መረዳት የሚቻለው የፈተናዎች አዘገጃጀት ፈተናዎቹ እንደሚሰጡበት ዓላማ የሚለያዩ መሆናቸውን ነው።

2.5. የጥሩ ፈተና መሠረታዊ መገምገሚያ መስፈርቶች

አንድን ፈተና ጥሩ ፈተና ነው ለማለት የጥሩ ፈተና መገምገሚያ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት። እነዚህን መስፈርት አንዳንድ ምሁራን አራት ሲያደርሷቸው አንዳንዶች ደግሞ ሦስት ብቻ እንደሆኑ ይገልፃሉ።

Harrison (1983) "Qualities of a good test" በሚል ርዕስ ስር ሦስቱ የጥሩ ፈተና ባሕሪያት የሚባሉት አስተማማኝነት፣ ተገቢነትና ተተግባሪነት እንደሆኑ ገልጿል።

2.5.1. አስተማማኝነት

ያለው (1998፡196) አስተማማኝነትን በሚመለከት እንዲህ ይላሉ፤ "አስተማማኝነት ሲባል አንድን ባህሪ ወይም ነገር በአንድ መለኪያ በመጠቀም በተደጋጋሚ በመለካት የሚገኝ የውጤት (የልኬት ተመሣሣይነትን፣ ቋሚነትን፣ ወጥነትን ወይም አይለወጤነትን የሚያመለክት ነው"

Haton (1975፡155) አስተማማኝነት ለማንኛውም ጥሩ ፈተና አስፈላጊ መስፈርት ነው። ፈተናው ተገቢነት ያለው እንዲሆን ከተፈለገ አስተማማኝነት እንደ መለኪያ ሆኖ ያገለግላል። ተመሳሳይ የአፈታተን ቁጥጥር ኖሮ፣ በተለያዩ ወቅት በተመሣሣይ ፈታኞች ተፈትነው የሚገኘው ውጤት የተለያየ ከሆነ ፈተናው አስተማማኝነት የጎደለው ነው።

ባጭሩ ምሁራኑ ከሰጡት ገለፃ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች አንድን ፈተና ተፈትነው ያስመዘገቡት ውጤት በድጋሚ ያንኑ ፈተና ተፈትነው ከሚያገኙት ውጤት ጋር ተመሣሣይ መሆን አለበት። እንደዚህ ከሆነ ደግሞ ፈተናው አስተማማኝነት ያለው ነው ለማለት ይቻላል።

Haton (1975፡155)፣ "ፈተና አስተማማኝነት እንዳይኖረው ተፅእኖ የሚያሳድሩ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው" ይላል፤

1. በፈተናው ውስጥ የተካተቱት የፈተና ናሙናዎች መጠን ተገቢነት፣ አብዛኛውን ጊዜ ግንኙነቱ ከይዘት ናሙና ጋር ሲሆን አስተማማኝነት የሚመለከተው የፈተናዎች ስፋትን ነው፤
2. የአፈታተን ሥርዓትን መቆጣጠር፣ አንድ አይነት ፈተና በተለያዩ ተቆጣጣሪ ቡድኖች፣ በተለያዩ ሁኔታዎች እና ጊዜያት መፈተን በግልፅ አስተማማኝነትን የሚወስኑ ተፅእኖዎች ናቸው፤
3. በተለያዩ ፈተናዎች የሚቀርቡት መመሪያዎች ለሁሉም ተፈታኞች ግልፅ ላይሆኑ ይችላሉ፤

4. በተፈታኙ በኩል ያሉ ግላዊ ችግሮች፣ ለምሣሌ አለመነቃቃት ሕመም ሊከሰት ይችላል፤

5. የአስተራረም ጉድለት፣ ይህ ለአስተማማኝነት አለመኖር ዋነኛ ተዕእኖ ፈጣሪ ነው።

2.5.2. ተገቢነት

Haton (1975) አንድ ፈተና ተገቢነት አለው የሚባለው መለካት የሚገባውን ጉዳይ በትክክል የለካ እንደሆነ ነው። ማንኛውም ፈተና አጭር ኢ-መደበኛ ወይም መደበኛ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ፈተናው ተገቢነት ያለው መሆን አለበት።

Harrison (1983) በተመሣሳይ የፈተና ተገቢነት የሚባለው መለካት የሚገባውን ነገር በትክክል የለካ እንደሆነ ነው። የተለያዩ የተገቢነት ዓይነቶች አሉ። ነገር ግን መምህሩ በፈተና ውስጥ ማስቀመጥ የሚገባው ዋናው ጉዳይ የይዘት ተገቢነት ለህያዊ ተገቢነትን ነው።

Alderson (1995፡170) ተገቢነት ለሚሰጡ ፈተናዎች ትክክለኛነት አጠቃላይ ማረጋገጫ ነው። ፈተና ተገቢነት አለው የምንለው እለካለሁ ያለውን በትክክል የለካ እንደሆነ ነው። ማንኛውም ፈተና ለአንድ ዓላማ ተገቢነት ያለው ሲሆን ይችላል፤ ለሁሉም ግን አይሆንም።

ከቀረበው ዝርዝር ሀሳብ መረዳት የሚቻለው አንድን ፈተና ተገቢነት አለው ለማለት ለመመዘን የተፈለገውን ክሂል ነጥሎ በትክክል የመዘነ እንደሆነ ነው። ይህም ማለት የዕህፈት ክሂልን ለመመዘን ፈልገን ጥያቄው ሌላ ተጨማሪ እውቀትን የሚጠይቅ ከሆነ ተገቢነት የለውም።

ለምሣሌ ስለ አብርሃም ሊንከን የህይወት ታሪክ ተማሪው እንዲዕፍ ብንፈልግ፣ ስለግለሰቡ ላይዕፍልን ይችላል። ምክንያቱም የጠየቅነው የዕህፈት ክሂል ብቻ ሣይሆን ታሪክንም ጭምር ነው።

2.5.3. ተተግባሪነት

Brown (1980፡253) አንድ ፈተና ተተግባሪ መሆን አለበት ሲባል ከገንዘብ፣ ከጊዜ፣ ከሠው ሃይል፣ ፈተናውን በትክክል ከመፈተንና ውጤቱንም አርሞ እስከመተርጎም ድረስ ያለውን ተፈፃሚነት ይመለከታል። ፈተናውን ከማዘጋጀት ጀምሮ እስከ ውጤት መተርጎም ድረስ ያለው ብዙ ወጭን የሚጠይቅ ከሆነ ተተግባሪነቱ እየቀነሰ ይሄዳል።

Harrison (1983፡12) ከቀረበው ፅንሰ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ተተግበሪነት ከገንዘብ፣ ከጊዜ እና የሠው ሃይል ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑን ነው።

ለምሣሌ ፈተናው በጣም ከበዛ የወረቀትና የቀለም ወጭም መጨመሩ አይቀሬ ነው። ከዚያም አለፍ ሲል ፈተናውን ለመቆጣጠር እና በአጭር ጊዜ ውስጥ አርሞ ለመመለስ እጅግ አድካሜ ነው። በዚህ ምክንያት ተተግባሪነቱ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ይገባል።

2.6. የጥያቄ ማቅረቢያ ስልቶች

የፈተና ጥያቄዎች የሚቀርቡባቸው ስልቶች በርካታ ናቸው። ከእነዚህ መካከል ለምሳሌ፡- ምርጫ፣ እውነት ወይም ሀሰት፣ አዛምድ ፣ ክፍት ቦታዎችን ሙላ፣ አጭር መልስ ፃፍ፣ የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

የ8ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናዎች ከተዘረዘሩት የጥያቄ ማቅረቢያ ስልቶች ውስጥ የምርጫ ጥያቄዎችን ብቻ የሚጠቀሙ በመሆናቸው በምርጫ መልክ የሚቀርቡ የአጠያየቅ ስልቶችን ብቻ በዝርዝር እንመልከት።

ሂተን (1975፡14) "ለምርጫ ጥያቄ ተስማሚ የምንለው የአማራጮች ብዛት በአብዛኛው አምስት ናቸው። ነገር ግን በጣም በዛ ከተባለ እስከ ሠባት ሊደረስ ይችላል። ነገር ግን ይህ በጣም አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ሰባት ጥሩ ምርጫዎችን ለማዋቀር እጅግ ያስቸግራል። ሌላው ቀርቶ አምስቱን እንኳ የተዋጣላቸው አማራጮች ለማድረግ አስቸጋሪ ነው። በማለት ያስረዳል።

የምርጫ ጥያቄዎችን ስናዘጋጅ ማስተዋል የሚገቡን ነገሮች በሚል Haton (1975፣15) የሚከተሉትን ነጥቦች ዘርዝሯል፤

1. እያንዳንዱ የምርጫ ጥያቄ አንድ መልስ ብቻ ሊኖረው ይገባል፤

2. በአንድ ጊዜ አንድ ነገር ብቻ ጠይቅ፤

3. እያንዳንዱ ጥያቄ የስዋሰው ስሕተት እንዳይኖረው ጥንቃቄ አድርግ፤

4. ሁሉም ምርጫዎች የተፈታኙን የቋንቋ ደረጃ ያመጣዘኑ መሆን ይገባቸዋል፤

5. ምርጫዎቹ የተብራሩና ግልፅ መሆን አለባቸው። ይህም ማለት እምቅ መሆን የለባቸውም።

6. ፈተናዎቹ ከቀላል ወደ ከባድ የተዋቀሩ ቢሆኑ ይመረጣል።

2.7. መርሐ ትምህርት ከመማሪያ መጽሐፍና ከፈተና ጋር ያለው ዝምድና

ለአንድ ተማሪ በቅርብ ሊኖሩት ከሚችሉ የትምህርት መሣሪያዎች ውስጥ አንዱ የመማሪያ መፅሐፉ ነው። ይህም የመማሪያ መፅሐፍ የሚዘጋጀው መርሐ ትምህርትን መሠረት በማድረግ ነው።

መርሐፍ ትምህርትን በሚመለከት አለም እሸቱ (2001)፣ Hutchinson እና Wotues (1991)፣ Dubin እና Olshtian (1986)፣ እንዲሁም Yolden (1991)ን ጠቅሰው እንደሚከተለው ገልፀውታል።

> *መርሐ ትምህርት ተማሪው ምን ይማራል ወይም ምን መማር ይገባዋል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ሰነድ ነው። በመሆኑም መርሃ ትምህርት፣ የሀገሪቱን አጠቃላይ የትምህርት ፍልስፍናና የሀገሪቱን የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ መሠረት በማድረግ፣ ተማሪው ምን መማር እንዳለበትና መምህሩም ምን ማስተማር እንደሚገባው የሚጠቁም መሠረታዊ የትምህርት አካል ነው። በዚህ መርሃ ትምህርት አማካኝነት የአንድ ሀገር የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ ስለሚንፀባረቅ በየደረጃው ያሉ አካላት ማለትም፣ መምህራን፣ መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አደራጆችና ብሎም የፈተና ዝግጅት የሚመለከታቸው*

ክፍሎች ይህንኑ የሀገሪቱን የቋንቋ ፖሊሲ ተከትሎ ለመጓዝ ተፈላጊውን መረጃ የሚያገኙት ከዚሁ ከመርሐ ትምህርቱ ይሆናል።

Carter (1973:605)፣ "የመማሪያ መጽሐፍ በሥርዓት የተደራጀ፣ ለአንድ የትምህርት ዘርፍ የጥናት ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል መሣሪያ ነው" በማለት የመማሪያ መጽሐፍትን አገልግሎት ሲገልፁ፣ Nunan(1994:98)፣ "የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ፣ መርሃ ትምህርቱ በተግባር እንዲገለፅ የሚያደርግ ነው" በማለት የመማሪያ መጽሐፉንና የመርሐ ትምህርትን የጠበቀ ዝምድና ገልፀዋል።

ጠጅቱ (1999)፣ Richards Rodgers (1986;24-25) Harmer (1991:256)፣ ጠቅሰው፣ "የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በመርሐ ትምህርቱ የተገለፁትንና እለት በእለት ተግባራዊ በመሆን የሚታዩትን የትምህርት ዓላማዎች ሰኪታማ ለማድረግ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፤ ይህም ከመርሐ ትምህርቱ ጋር ያለውን ቁርኝት በግልፅ ያሳያል" በማለት ገልፀዋል።

Dubin and Olshtain (1986፣3) "ከመርሃ ትምህርት ዋና ዋና ክፍሎች አንዱ ግምገማ ወይም ፈተና ነው። ግምገማ የመርሃ ትምህርት ዓላማ ተግባራዊነት በመለካት በተማሪዎች ችሎታ፣ በትምህርቱ ድክመትና ጥንካሬ ላይ መረጃ ያቀርባል።

ከላይ ከቀረበው ሐሳብ በመነሣት የመማሪያ መፃህፍትና ፈተና ጥብቅ ዝምድና እንዳላቸው መረዳት ይቻላል። በተለይም አንድ የችሎታ መለኪያ ፈተና ሲዘጋጅ መሠረት የሚያደርገው የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርትን ነው። መርሃ ትምህርት ደግሞ የሥርዓተ ትምህርት ክፍል ነው። ስለዚህ ፈተና ከመርሃ ትምህርት ክፍሎች አንዱ በመሆኑና፣ በተመሳሳይ የመማሪያ መፃህፍት የሚዘጋጁት መርሃ ትምህርቱን መነሻ በማድረግ በመሆኑ ጥብቅ ዝምድና አላቸው ማለት እንችላለን።

በአጠቃላይ መርሐ ትምህርት፣ መማሪያ መጽሐፍና ፈተና የማይነጣጠሉ ጉዳዮች መሆናቸውን ከምሁራኑ ገለፃ መረዳት ይቻላል።

2.8. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የጥናቱ ዓላማ ይለያይ እንጅ ፈተናን በሚመለከት በርካታ ጥናዊ ፅሁፎች ቀርበዋል። እነዚህን ጥናታዊ ፅሁፎች በወፍ በረር ብንቃኝ አልያም በአትኩሮት ብንመለከት አብዛኛዎቹ በአጠናን ዘዴያቸው፣ በመረጃ መሠብሰቢያ መሳሪያቸው፣ በመረጃ አተናተናቸው፣ በክፍል ደረጃ አመራረጣቸው፣ ወዘተ. ይመሣሰላሉ። ከዚህ ቀጥሎ ቀደም ብለው የተጠኑ ጥናቶችን እንመልከት።

አበበ (1975)፣ "የ6ኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ግምገማ" በሚል ርዕስ ከ1962-1972 ዓ.ም. ድረስ የቀረቡ የ6ኛ ክፍል ብሔራዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን ከገመገመ በኋላ ከ1962-1966 ዓ.ም. ድረስ ያሉት ፈተናዎች ከሥርዓተ ትምህርቱ ውጪ እንደሆኑና ብዙ ችግር እንዳለባቸው ገልፆ፣ ከ1971-72 ዓ.ም ያሉት ግን እንደ መጀሪያዎቹ ዓመታት ድክመታቸው የጎላ ሣይሆን የተሻሉ መሆናቸውን በጥናቱ ግኝት ላይ ገልጿል።

ንጉሴ (1978)፣ "የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና አቀራረብና የመማሪያ መጻሐፍ ዝምድና" በሚል ርዕስ ጥናት አድርጎ ከ1973-1983 የቀረቡ የ2ኛ ደረጃ የአማርኛ ፈተናዎች ከመማሪያ መፃህፍቱ ጋር ያላቸው ዝምድና ጥብቅ ቢሆንም የተወሰኑት ጥያቄዎች ግን ከትምህርቱ ይዘት ውጭ እንደሆኑ በጥናቱ አመላክቷል።

መንግሻ (1984)፣ "የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና የንባብ ጥያቄዎች ግምገማ" በሚል ርዕስ ከ1977-1983 ዓ.ም. ድረስ የቀረቡ የአማርኛ ብሔራዊ ፈተናዎች የንባብ ጥያቄዎችን ገምግሟል። ከጥናቱ ያገኘው ውጤትም አንዳንድ ጥያቄዎች ዓላማቸውን ስተው ከቋንቋ ክሂል ውጭ የሌላ ትምህርት አውቀት እንደሚጠይቁና በአጠቃላይ ሲታይ የፈተናዎቹ ጠንካራ ጎን እንደሚያይል ጠቁሟል።

ንጉሴ (1989)፣ "በሀረር ከተማ በሚገኙ ሁለት ከፍተኛ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ1987 ዓ.ም. የተሰጡ የአማርኛ ፈተና ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ ጥናት አድርጎ ፈተናዎቹ የመፃህፍቱን ይዘቶች ወካይ እንደሆኑ ነገር ግን የምንባብ ጥያቄዎች ከምንባቦቹ ጋር እንደማይገናኙ፣ የተወሰኑት ደግሞ ምንባቡን ሣያነቡ ሊመለሱ የሚችሉ እንደሆኑ በግልፅ አሳይቷል።

ታረቀኝ (1993)፣ "ሀገር አቀፍ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከ5-8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ጋር ያለው ዝምድና" የሚል ጥናት አካሂዶ የደረሰበት ውጤት በመርሃ ትምህርቱ እና በፈተናዎቹ መካከል የጠበቀ ቁርኝት እንደለ መስክሯል።

ትንሳኤ (1988)፣ "የአማርኛ ቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ ፈተና መነሻነት" በሚል ርዕስ ጥናት አድርጋለች። ያገኘችው ውጤትም አብዛኛዎቹ የቃላትና የፊደል ጥያቄዎች ተገቢ መመዘኛ ዓለመሆናቸውን አረጋግጣለች።

ራሄል (2001)፣ "ከ 1993-2000 ዓ.ም. ድረስ በቀረቡት የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መልቀቂያ ፈተናዎች የመድበለ ቃላት አፈታተን" በሚል ርዕስ ጥናት አድርጋ፣ የቃላት ፈተናዎቹ የቀረቡባቸው የቃላት አፈታትን መንገዶች ተመጣጣይ፣ ተቃራኒ፣ ፍቻዊ፣ አዛምዶአዊ፣ ቅደም ተከተላዊ የመተካትና የቃላት አመሰራረት ጥያቄ አቀራረቦች እንደሆኑ ገልፃለች።

ካሣዬ (1992) "በአዲስ አበባ መስተዳድር የአየር ጤና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ1989-1991 ዓ.ም. ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደው ነበር። ከጥናቱ ያገኙት ውጤትም 80% ፈተናዎቹ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር እንደሚዛመዱና፣ የሥነ ልሣን እውቀትን የሚለኩ ሆነው መዘጋጀታቸው በጠንካራ ጎናቸው የሚገለፁ ሲሆኑ፣ የመማሪያዎች ግልፅ አለመሆን፣ የሥነ-ፅሁፍ ችሎታን ለመመዘን ብቁ አለመሆናቸው፣ የአታች ጥያቄዎች አለመካተትና አሻሚ አማራጮች አልፎ አልፎ መከሠታቸው ድክመ ጎናቸው እንደሆነ ገልፀዋል።

ሀብታሙ (1991) "በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙ ሶስት የግል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 10ኛ ክፍል ከ1989-1990 ዓ.ም የተሰጡ አንብቦ የመረዳት ፈተና ጥያቄዎች አዘገጃጀትና አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል። ከጥናቱ ያገኙት ውጤት የሚያሣየው፣ ፈተናዎቹ በጥሩ ፈተና አዘገጃጀት መርሆዎች ላይ ተመሰርተው የተዘጋጁ መሆናቸው፣ ሁሉም ጥያቄዎች የአማራጭ ሰጭ ጥያቄዎች በመሆናቸው በርካታ ጥያቄችን ለማካተትና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማረም የሚያስችሉ

መሆናቸውን እንደ ጠንካራ ጎን ሲገልጿቸው፣ የአሻሚ ጥያቄዎች መኖርና የምንባቦች በጣም አጭር ሆኖ መቅረብ ደካማ ጎናቸው እንደሆነ አመላክተዋል።

አገኘሁ (1990) ዓ.ም. "አማርኛን በማስተማር ሂደት የአንብቦ መረዳት ክሂሎች የይዘትና የላህይ አግባብነትና አጠያየቅ ዘዴዎች፣ በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች የ12ኛ ክፍል ሞዴል ፈተናዎች" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኤም. ኤ.ድግሪ ማሟያ ጥናት አካሂደዋል። አጥኚው በጥናታቸው የደረሱበት ውጤትም ለፈተና የቀረቡት ምንባቦች እና የአጠያየቅ ዘዴዎቸው ከምንባብ አፈታተን መርሆዎችና መመዘኛዎች አኳያ ድክመት እንዳለባቸው አመላክተዋል።

በአጠቃላይ የቀረቡትን ሠባት ቀደምት ጥናቶች ስንመለከት በሚመርጧቸው የክፍል ደረጃዎችና በሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮችም ጭምር ይመሣሰላሉ።

ለምሣሌ 2ኛ ደረጃን የመረጡ ንጉሴ (1978)፣ መንገሻ (1984)፣ ንጉሴ (1989)፣ ትንሣኤ (1988)፣ ራሄል (2001) ናቸው።

የትንሳኤ ብርሃኔና የራሔል ወርቁ ጥናት ትኩረት ያደረገው በቃላት ላይ ነው። ስለዚህ እነዚህ አጥኝዎች በመረጡት የክፍል ደረጃ ብቻም ሳይሆን በጥናቱ ርዕስ ጉዳይም ይመሳሰላሉ። የተወሰኑትን ስንመለከት ደግሞ በአመተምህርት የተከፋፈሉ ናቸው። ለምሣሌ አበበ ከበደ ከ1962-1972፣ ንጉሴ ከ1973-1983 ዓ.ም የመረጡ ሲሆን ሁለቱም ያጠኑት የ10 ዓመት ፈተናዎችን ነው።

በተመሣሳይ መንገሻ ከ1977-1983 ዓ.ም፣ ራሄል ወርቁ ከ1993-2000 ዓ.ም በማለት በአመተ ምህረት ከፋፍለዋል።

የሁሉም ጥናታዊ ዕሁፎች የአጠናን ዘዴ እና የመረጃ መሠብሰቢያ መሣሪያ ተቀራራቢ ነው።

በመጨረሻም እነዚህ የቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፎች ከአጥኚው ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር በምን ይመሳሰላሉ? በምንስ ይለያያሉ? ስንል የጥናቱ ትኩረት በፈተና ዙሪያ መሆኑ፣ እንደሌሎቹ ሁሉ በዓመተ ምህረት የተገደበ (ከ2000-2004) የሚል መሆኑ፣ በአጠናን ዘዴ እና በመረጃ መሠብሰቢያ መሳሪያ አጠቃቀሙ ከተጠቀሱት ሰባት ጥናታዊ ፅሁፎች ጋር ያመሳስለዋል።

ነገር ግን በርቀት ትምህርት ደረጃ የቀረበ የፈተናና የመፃህፍት ዝምድናን የሚፈትሽ በመሆኑ ከዚህ በላይ በስም የተጠቀሱት አጥኚዎች ካቀረቧቸው ጥናታዊ ፅሁፎች ፍጹም የተለየ ያድርገዋል።

ምዕራፍ ሦስት

የአጠናን ዘዴ

በምዕራፍ አንድ ሥር እንደተገለፀው ይህ ጥናት በሀገር መከላከያ ሰራዊት የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር ከ2001ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ ለስምንተኛ ክፍል የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር ያላቸውን ዝምድና የሚፈትሽ ነው። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥናቱ መሠረት ያደረገው የአይነታዊ የምርምር ዘዴን (Qualitative Research) እና መጠናዊ የምርምር ዘዴን (Quantitative Research) ሲሆን፣ በስፋት የሚቀርበው በገለፃ (Descriptive) ነው።

3.1. የጥናቱ የመረጃ ምንጮች

ቀደም ብሎ በጥናቱ ዓላማ ላይ እንደተገለፀው፣ ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም ለስምንተኛ ክፍል የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተናዎች ከስምንተኛ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ጋር ያላቸውን ዝምድና መፈተሽ የጥናቱ ተቀዳሚ ተግባር ነው። ይህንንም ጥናት ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት ሠነዶች በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፤

1. በ1994 ዓ.ም. በመከላከያ ሚኒስቴር አማካኝነት የተዘጋጁት የስምንተኛ እና የሰባተኛ ክፍል የተማሪው የአማርኛ ቋንቋ መማህፍት፣
2. ከ2001ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ በሀገር መከላከያ ሠራዊት የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር ለስምንተኛ ክፍል የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተናዎች ናቸው።

3.2. የክፍል እና የፈተና ናሙና አመራረጥ

በሀገር መከላከያ ሠራዊት የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር ለስምንተኛ ክፍል የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተናዎች ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር ያላቸውን ዝምድና ለመፈተሽ የጥናቱ ናሙናዎች በሚከተሉት መንገዶች ተመርጠዋል፤

3.2.1. የክፍል ደረጃ አመራረጥ

በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር የሚማሩት የሠራዊት አባላት ከሠባተኛ እስከ አስረኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ብቻ ናቸው። ነገር ግን ከሠባተኛ ክፍል በታች ያሉ ተማሪዎች ባሉበት ቦታ ሆነው ከሠራዊቱ በተውጣጡና የአጭር ጊዜ ስልጠና በተሰጣቸው መምህራን የገፅ ለገፅ ትምህርት ይማራሉ። በመሆኑም ከተጠቀሱት አራት የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ስምንተኛ ክፍል በሚከተሉት ምክንያቶች ተመርጧል፤

1. አጥኚው ከሠባተኛ እስከ አስረኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን በርቀት ትምህርት ያስተምራል፤ ይፈትናል፤ ውጤትም ያጠናቅራል። ስለዚህ ራሱ ያወጣውን ፈተና ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር ዝምድና የለውም ብሎ ለመግለፅና ደካማ ጎኑን በግልፅ ለማሣየት ካለው ሥጋት የመነጨ ሦስቱ የክፍል ደረጃዎች ማለትም 7ኛ፣ 9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች አልተመረጡም፤

2. ምንም እንኳ የአስረኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና የሚዘጋጀው በፈተናዎች ድርጅት አማካኝነት ቢሆንም የክፍል ደረጃው ያልተመረጠበት ዋናው ምክንያት የአስረኛ ክፍል ፈተና ሀገር አቀፍ ፈተና በመሆኑ ለአንድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ከሚዘጋጀው ፈተና የበለጠ ትኩረት ሊደረግበት ይችላል። ነገር ግን በሀገር መከላከያ ሠራዊት የርቀት ትምህርት መርሐግብር ለስምንተኛ ክፍል የሚወጣው ፈተና ለሌሎች የመደበኛ ተማሪዎች ከሚዘጋጀው ፈተና የተለየ በመሆኑ የፈተና ባለሙያዎቹ ምን ያህል ትኩረት ሠጥተው እንደሚያዘጋጁት ለማወቅ ነው።

3.2.2. የፈተና ናሙና አመራረጥ

በምዕራፍ አንድ ሥር እንደተገለፀው የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር የጀመረው በ1995 ዓ.ም. ነው። በመሆኑም እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ለአስር ጊዜ ያህል የስምንተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ተካሂዷል። አጥኚው ከአስሩ ዓመታት ፈተናዎች ውስጥ ከ2001ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ ያሉትን ፈተናዎች የመረጠው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

ሀ. ጊዜያቸው በጣም በራቀ ፈተናዎች ላይ ጥናት ከማድረግ ይልቅ በቅርብ ጊዜ በወጡ ፈተናዎች ላይ ጥናት ማድረጉ፣ ችግሮች እንኳ ቢኖሩ በቅርብ ጊዜ ለተከሰቱት ችግሮች ጥቆማ መስጠትና የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብ የተሻለ ነው ብሎ ከማሰብ፣

ለ. ዓመታት በራቁ ቁጥር መረጃዎችን የማግኘቱ ዕድል ጠባብ ስለሚሆን፣ መረጃዎችን በቀላሉ ለማግኘት የቅርብ ጊዜ ፈተናዎች በአመቺ ናሙናነት ተመርጠዋል።

3.3. የመረጃ ምንጮች አተናተን ዘዴ

ከተማሪው የስምንተኛ እና የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጻሕፍት እንዲሁም ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም. ከቀረቡት ፈተናዎች የተገኙት የመረጃ ምንጮች በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል፤ ይኸውም የተማሪዎች የመማሪያ መፅሐፍ መቼና በማን እንደተዘጋጀ፣ ስንት ጥራዞችና ምዕራፎች እንዳሉት፣ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ የተካተቱት የቋንቋ ክሂሎችና ዝርዝር የትምህርት ይዘቶች ምን ምን እንደሆኑ በወፍ በረር ተቃኝቷል።

ከዚህ በተጨማሪ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቋንቋ ክሂሎችንና ዝርዝር የትምህርት ይዘቶችን የሚመለከቱ መልመጃዎችና ጥያቄዎች ምን ያህል እንደሆኑ በሠንጠረዥ ውስጥ በመቶኛ ተሰልተው ቀርበዋል። የቀረበውን ሠንጠረዥ መሠረት በማድረግ እያንዳንዳቸው ክሂሎችና ዝርዝር የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል ትኩረት እንደተሠጣቸው ተብራርቷል።

በመጨረሻም ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ የተዘጋጁት ፈተናዎች በሠንጠረዥ ቀርበው የትኛው የቋንቋ ክሂል ምን ያህል የጥያቄ ብዛት እንደያዘ፣ ለየትኛው ክሂል ትኩረት እንደተሰጠና እንዳልተሰጠ፣ ከፈተናዎቹ ውስጥ ለአብነት የሚሆኑ ጥያቄዎችን በማጣቀስ ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር ስላላቸው ዝምድና እና ከተገቢነት አንፃር እየተፈተሹ በዝርዝር ለማብራራት ተሞክሯል።

ምዕራፍ አራት

የጥናቱ ትንተና

በምዕራፍ አንድ ሥር እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሀገር መከላከያ ሠራዊት የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር ከ2001ዓ.ም. - 2004 ዓ.ም. ድረስ ለስምንተኛ ክፍል የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተናዎች ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር ያላቸውን ዝምድና መፈተሽ ነው።

በዚህ ምዕራፍ ሥር ከላይ የተጠቀሰውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡ ክሂሎችን መሠረት በማድረግ ምን ምን የትምህርት ይዘቶች እንደተካተቱ፣ በእያንዳንዱ የትምህርት ይዘት ውስጥ ምን ያህል መልመጃዎችና ጥያቄዎች እንደቀረቡ ለመረዳት ያመች ዘንድ ብዛትንና የመቶኛ ስሌትን የሚያሳይ ሠንጠረዥ ቀርቧል። ከፈተናዎቹ በማስቀደም የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍን መመልከቱ ከተዘጋጁት ፈተናዎች ጋር ምን ያህል ዝምድና አላቸው የሚለውን በቀላሉ ለመረዳት ያመቻልና ነው።

ከ2001- 2004 ዓ.ም. ድረስ በቀረቡት ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የቋንቋ ክሂሎች ብዛት በመቶኛ ስሌት ጭምር እየተሰሉ በሠንጠረዥ ይገለፃሉ። በፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱትን የክሂል ዓይነቶች ብቻ ማመልከት ለጥናቱ በቂ ማጣሪያ ስለማይሆኑ በእያንዳንዳቸው ክሂሎች ሥር የተካተቱ ዝርዝር ይዘቶች በገለፃ መልክ ቀርበዋል።

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በዋነኛነት ጥናቱ የሚያተኩረው የስምንተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር በመዛመድ እና ባለመዛመዱ ላይ ነው። ይህ የብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና ከፈተና ዓይነቶች ውስጥ በደረጃ መለኪያ ፈተናነቱ ይታወቃል። በመሆኑም የችሎታ መለኪያ ፈተና የሚፈተን ተማሪ መፈተን ያለበት የተማረውን ብቻ ነው። ይህ የሚረጋገጠው ደግሞ ተማሪው የተፈተናቸው ፈተናዎች ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር ተዛምደው ሲገኙ ብቻ ነው።

እንደ አበበ (1975) ገለጻ የችሎታ መለኪያ ፈተና በተለያዩ የትምህርት ተቋማት ያሉ ተማሪዎች በአንድ ወቅት በጋራ የሚወስዱት የቋንቋ ፈተና ነው። የችሎታ መለኪያ ፈተና በሁለት መልኩ ሊዘጋጅ ይችላል። አንደኛው በትምህርት ቤት ውስጥ የሚዘጋጅ

የችሎታ መለኪያ ፈተና (Classroom Achievement Test) ሲሆን፣ ሁለተኛው የፈተና ዓይነት ደግሞ መደበኛ የችሎታ መለኪያ ፈተና (standardized achievement test) ነው።

በትምህርት ቤት ውስጥ የሚዘጋጀው የችሎታ መለኪያ ፈተና ክፍል ውስጥ ገብተው በሚያስተምሩ መምህራን የሚዘጋጅ ፈተና ሲሆን፣ ይህም መምህራኑ በየትኛው የትምህርት ይዘት ላይ ሠፊ ትኩረት አድርገው አንዳስተማሩ ስለሚያውቁና የተማሪውን ደረጃ መገመት ስለሚችሉ በቀላሉ ማዘጋጀት ይችላሉ። ነገር ግን መደበኛ የችሎታ መለኪያ ፈተና በብሔራዊ ደረጃ በዓመት አንድ ጊዜ የሚሰጥ ፈተና ነው። በመሆኑም እንዲህ ዓይነቱ ፈተና የሚዘጋጀው ፈተና በማዘጋጀት የረጅም ጊዜ ልምድና ችሎታ ባላቸው የትምህርት ባለሙያዎች ነው። ስለዚህ ፈተናው ሲዘጋጅ ትኩረት የሚያደርገው መርሐ ትምህርቱንና መማሪያ መፅሐፉን ነው።

ተማሪው መፈተን ያለበት የተማረውን ነው፤ በሌላ አገላለፅ "ያስተማርከውን ፈትን" የሚለው መርህ፣ መምህሩ ያስተማረውን ሁሉ መፈተን አለበት ወይም በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረበው የትምህርት ይዘት ሁሉ በፈተናው ውስጥ መካተት አለበት ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ይሁን እንጅ እንደይዘቱ ስፋት በናሙናነት ማቅረብ ያስፈልጋል።

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መፅሐፉ በሁለት ጥራዞች ተከፈፍሎ የተዘጋጀ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ጥራዥ ከምዕራፍ 1-4 ያሉ የትምህርት ይዘቶችን አካቶ የያዘ ነው። ሁለተኛው ጥራዝ ደግሞ ከምዕራፍ 5-9 ያሉ የትምህርት ይዘቶችን አካቶ ይዟል።

የመፅሐፉ አዘጋጆችና አርታኢዎች በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሲሆኑ፣ የታተመውም በብራና ማተሚያ ድርጅት ውስጥ በ1994 ዓ.ም. ነው።

የመጀመሪያው ጥራዝ 94 ገፆች ያሉት ሲሆን፣ ሁለተኛው ጥራዝ 125 ገፆች አሉት። በያንዳንዳቸው ምዕራፎች ሥር የቀረቡትን ዝርዝር የትምህርት ይዘቶች ስንመለከት ፣

- የቋንቋ ምንነትና ተግባራት
- ቃላትና ቅጥያዎች
- አያያዥ ቃላትና ገላጭ ቃላት
- ቃል፣ ሐረግና ዓረፍተ ነገር
- ንባብ እና የመረጃ አሰባሰብ
- ሥርዓተ ነጥቦች፣ አንቀፅና ድርሰት
- ማጻመጥና መናገር
- ሰነ ቃል እና ግጥም
- ፅሕፈት

የሚሉት ተካተው ይገኛሉ።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ትኩረት የሚያደርገው በመማሪያ መፅሐፉና ላይ ሳይሆን በፈተናዎቹ ላይ ነው። በመሆኑም ስለመፅሐፉ ዝርዝር ጉዳይ ለማንሣት የተፈለገበት ዋናው ምክንያት የፈተናዎቹንና የመፅሐፉን ዝምድና በቀላሉ ለመረዳት ያመች ዘንድ እንደሆነ ልብ ይሏል።

ከዚህ ቀጥሎ በመፅሐፉ ውስጥ የቀረቡ የቋንቋ ክሂል መልመጃዎች ብዛትና የጥያቄዎች ብዛት በመቶኛ ስሌት ጭምር ቀጥሎ በሠንጠረዥ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 1፣ በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የክሂል እና የዕውቀት ዘርፍ መልመጃዎች ብዛት

ተ.ቁ	በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ ክሂሎች እና የዕውቀት ዘርፎች	በ8ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የቋንቋ ክሂል መልመጃዎችና ጥያቄዎች ብዛት እና በመቶኛ ስሌት ሲገለፁ			
		በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች ብዛት		በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡ ጥያቄዎች ብዛት	
		ብዛት	%	ብዛት	%
1.	ስነ ልሳን	16	19.1	166	21.9
2.	ቃላት	21	25	247	32.6
3.	ስነ ጽሑፍ	7	8.3	65	8.6
4.	ምንበብ	20	23.8	192	25.3
5.	መፃፍ	16	19	75	9.9
6.	ማዳመጥ	01	1.2	01	0.1
7.	መናገር	03	3.6	12	1.6
	ድምር	84	100	758	100

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በመልመጃዎችም ሆነ በጥያቄዎች ቁጥር ብዛት ቀዳሚውን ስፍራ የያዘው የቃላት ትምህርት ነው። ይኸውም የመልመጃዎቹ ብዛት 21 ሲሆን፣ በመቶኛ ሲሰላ 25 ከመቶ፣ ማንበብ 23.8 ከመቶ፣ ስነልሣንና መፃፍ እያንዳንዳቸው 19.1 ከመቶ ይዘው ይገኛሉ። ዝቅተኛ የመልመጃ ብዛት ይዘው የሚገኙት እንደ ቅደም ተከተላቸው ስነዕሁፍ፣ መናገርና ማዳመጥ ናቸው።

በቃላት ሥር የሚካተቱ የትምህርት ይዘቶች ምን ምን ናቸው ስንል የቃላት ተመሳሳይ ፍች፣ ተቃራኒ ፍችዎችን እና ፊሊጣዊ አነጋገሮችን የሚመለከቱ ናቸው። እናም እነዚህን በተመለከተ በርካታ መልመጃዎች በመፅሐፉ ውስጥ ተካተው ይገኛሉ። ለምሣሌ በምዕራፍ አንድ፣ መልመጃ ሁለት፣ በገጽ 11 ላይ ተማሪዎች በቃላት ተመሳሳይ ፍች እንዲሰጡ በርካታ ቃላት ተዘርዝረዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ተቃራኒ

ፍች መስጠትን የሚመመለከት መልመጃ ሁለት በገፅ 12 ላይ ብቻ አሥራ አምስት ቃላት ተዘርዝረዋል። በአጠቃላይ በመፅሐፉ ውስጥ ከቀረቡት 247 የቃላት ጥያቄዎች ውስጥ 98 በመቶ የሚሆነውን የሸፈነው ተመሣሣይና ተቃራኒ ፍች መስጠትን የሚመለከት ነው። 2 ከመቶ የሚሆነው ደግሞ ፊሊጣዊ ንግግር ነው።

ቃላትን በሚመለከት የቀረቡትን መልመጃዎች ሁሉ ገፅ በገፅ እየጠቀሱ መዘርዘሩ ጥናታዊ ፅሑፉን አሰልቺ ከማድረግ የዘለለ የሚፈይደው ነገር የለምና ወደ ሌላ ክፍል ማለፉ የተሻለ ነው።

በመፅሐፉ ውስጥ ከምንባቡ ውስጥ የወጡ መልመጃዎች ወይም ምንባብን በተመለከተ የወጡ ጥያቄዎች ቁጥር የሁለተኛነትን ደረጃ ይዞ እንደሚገኝ ከሠንጠረዡ መመልከት ይቻላል። የመልመጃዎቹ ብዛት 20 ከመቶ ሲሆን፣ የጥያቄዎቹ ብዛት ደግሞ 25.3 ከመቶ ነው።

ሥነ ልሳን 16 መልመጃዎችን እና 166 ጥያቄዎችን ይዞ እንደሚገኝ ከሠንጠረዡ ማየት ይቻላል። በዚህ ሥር የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች አለፍ አለፍ እያልን እንመልከት። ምዕራፍ አንድ ፣ በገፅ 16 ላይ የቃላት ምስረታ፣ ገጽ 27 እና 31 የድምፅ መጥበቅና መላላት፣ በገፅ 34፣ 35፣ 36፣ 42 ቅጥያን የሚመለከቱ በርካታ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በገፅ 29 ባለቤትና ተሳቢ፣ በገፅ 61 የስም ገላጭ፣ በገፅ 63 የግስ ገላጭ፣ በገፅ 79 እና 80 ሐረግና የዓረፍተ ነገር ስልቶች ወዘተ. በመፅሐፉ ውስጥ ቀርበው ይገኛሉ።

የፅሀፈት ክሂል መልመጃዎች ብዛት ከሥነ ልሳን ጋር እኩል ቢሆንም በጥያቄ ብዛት 75 ወይም 9.9 ከመቶ በመያዝ የአራተኛነትን ደረጃ ይዟል። በዚህ ክሂል ሥር የተካተቱ የትምህርት ይዘቶችን በመፅሐፉ ውስጥ ስንመለከት ገፅ 26 እና 27 ሥርዓተ ነጥቦች፣ ገፅ 35 እና 36 አንቀፅ፣ ገፅ 38 የድርሰት ምንነት፣ ገፅ 109 የደብዳቤ አፃፃፍ፣ ገፅ 122 የዘገበ ምንነትና አይነቶች፣ በዝርዝር ተብራርተውና በመልመጃ መልክ ቀርበው ይገኛሉ።

በአምስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ሥነ ፅሁፍ ነው። በመልመጃዎች ብዛት 7 ወይም 8.3 ከመቶ ይዞ የሚገኝ ሲሆን በጥያቄ ቁጥር ብዛት ደግሞ 65፣ በመቶኛ ስሌት ሲገለፅ የ8.6 ከመቶ ሽፋን አለው።

በሥነ ዕውፍ ስር ወደሚካተቱት ይዘቶች ስንገባ ገፅ 211 የድርሰት አይነቶች፣ ገፅ 72-74 ሥነ-ቃል፣ ገፅ 86 የግጥም ምንነትና ዓይነቶች፣ ገፅ 79 ዘይቤ፣ ገፅ 96 ቅኔ ከገፅ 119-120 የልቦለድ ምንነት፣ የልቦለድ ዓይነቶችና አለባውያን የሚሉ ዋና ዋና የትምህርት ይዘቶችን እናገኛለን።

የመጨረሻውን ደረጃ የያዙት መናገርና ማዳመጥ የሚሉት የክሂል ዘርፎች ሲሆኑ፣ ከሠንጠረዡ ስንመለከት መናገር በመልመጃ ብዛት 3 ወይም የ3.6 ከመቶ ድርሻ ሲኖረው፣ ማዳመጥ 1 ወይም የ1.2 ከመቶ ድርሻ ይዞ ይገኛል።

እነዚህን ክሂሎች ለማስተማር መፅሐፉ በምን መልኩ ተዘጋጅቷል? ወይም በመፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ምን ምን ናቸው ስንል፣ ንግግርን በሚመለከት የንግግር ዝግጅትና አቀራረብ መመሪያ ማዳመጥን በተመለከተ ደግሞ የማዳመጥ መመሪያ የሚል በገፅ 50 እና 54 ላይ ሰፍሮ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ ለሁለቱም ክሂሎች በጋራ የሚያገለግሉ ከገፅ 60-65 ቋውውት፣ ውይይትና ክርክርን የሚመለከቱ ይዘቶች ቀርበዋል።

በአጠቃላይ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት ክሂሎችና ዝርዝር ይዘቶች ከላይ የተገለፁት ናቸው። ይሁን እንጅ የገለፃ ድግግሞሽን ለማስወገድ እና ጥናታዊ ዕውፉ አሰልቺ እንዳይሆን በማሰብ እያንዳንዱ ዝርዝር ጉዳይ ገፅ በገፅ አልተገለፀም። ይህ ሲባል ግን በፈተናው ውስጥ የተካተቱት የትምህርት ይዘቶች በመፅሐፉ ውስጥ መኖር አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ በዝርዝር አልተዳሰሱም ማለት አይደለም።

ከዚህ በመቀጠል የጥናቱ ዋነኛ ትኩረት የሆነው ከ2001 -2004 ዓ.ም ድረስ የቀረበውን ፈተና በዝርዝር እንመለከታለን። ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት በአራቱ ዓመታት ውስጥ የተዘጋጁት ጥያቄዎች ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር ዝምድና አላቸው ወይስ የላቸውም የሚለውን መፈተሽ እንጂ፣ ምን ያህል የሰዋስው ጥያቄዎች ቀርበዋል ወይም ምን ያህል የቃላት ጥያቄዎች ተካተዋል የሚለውን ማነፀፀር አይደለም።

በእያንዳንዱ የፈተና ዘመን የተካተቱ ክሂሎችና ዝርዝር የትምህርት ይዘቶች በሠንጠረዥ ቢገለፁ የጥናቱን አካሄድ ግልፅና ቀላል ያደረገዋል። ስለዚህ ከ2001-2004 ዓ.ም. ድረስ የተዘጋጁት ፈተናዎች ከዚህ እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

ሠንጠረዥ 2 ፣ በሀገር መከላከያ ሠራዊት ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም.የተካተቱ ክሂሎች፣ የሥነ ጽሑፍና የሥነ ልሳን ዕውቀት ብዛት በመቶኛ ስሌት ሲገለጹ

ተ.ቁ	የፈተና ይዘቶች	ከ2001ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም. የቀረቡ ፈተናዎች							
		2001 ዓ.ም.		2002 ዓ.ም.		2003 ዓ.ም.		2004 ዓ.ም.	
		ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%
1.	ሥነ ልሳን	15	25	11	18.3	13	21.7	10	16.78
2.	ቃላት	9	15	10	16.6	15	25	15	25
3.	ሥነ ጽሑፍ	8	13.3	06	10	08	13.3	9	15
4.	ምንባብ	12	20	20	33.3	13	21.7	11	18.3
5.	ጽሕፈት	15	25	14	23.3	10	16.6	13	21.7
6.	ማዳመጥ	01	1.7	-	-	-	-	-	-
7.	ንግግር	-	-	-	-	01	1.7	02	3.3
	ድምር	60	100	60	100	60	100	60	100

የስነ ልሳን ጥያቄዎች

ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው በ2001 ዓ.ም ከተዘጋጁት 60 ጥያቄዎች ውስጥ 15 (25%) ያህሉ የሥነ ልሳን ጥያቄዎች ናቸው።

የቀረቡትን አስራ አምስት የሥነ ልሣን ጥያቄዎች በዝርዝር ስንመለከት ደግሞ ባለቤት፣ ተሣቢና ግስን የሚመለከቱ ስድስት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ከዚህ ውጭ ቅጥያና ገላጭ ቃላት እያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት፣ የድምፅ መጥበቅና መላላት እንዲሁም የቃላት እርባታን በተመለከተ አንድ አንድ ጥያቄዎች ቀርበው ይገኛሉ። ቀሪው አንድ ጥያቄ የአረፍተ ነገር ሥልቶችን የሚመለከት ነው። በአራቱም ዓመት የወጡት የሥነ ልሣን ጥያቄዎች መጠናቸው ይለያይ እንጂ በፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው የሚገኙት የትምህርት ይዘቶች ተመሣሣይ ናቸው። ምክንያቱም ጥያቄዎቹ የሚያተኩሩት በስም ገላጭ፣ በግስ ገላጭ፣ በቃላት መጥበቅና መላላት፣ በቃላት ምስረታ፣ በባለቤትና ተሳቢ ወዘተ ላይ በመሆናቸው ነው።

ስነ ልሳንን በሚመለከት በመፅሐፉ ውስጥ ከቀረቡት በርካታ መልመጃዎች መካከል ጥቂቶቹን ለአብነት እንመልከት።

መመሪያ፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ።

1. ረጅሚ ሙሃባ በታክሲ ስትሳፈር አገኘኋት።" በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የስም ገላጭ የሆነው
   ሀ. በታክሲ ስትሳፈር ለ. ረጅማ ሙሃባ ሐ. ረጅሚ መ. ስትሳፈር
2. "ነፈሱ ፈረስ ያነክሳል።" በሚለው ከስሩ የተሰመረበት ቃል _____ ነው።
   ሀ. መ.ያ ለ. ገላጭ ሐ. ተገላጭ መ. ባለቤት
3. እንደተገነዘብኩት ደራርቱ በፍጥነት ትሮጣለች። በሚለው ውስጥ የማሰሪያ አንቀፅ ገላጩ _____ ነው።
   ሀ. እንደተገነዘብኩት ለ. ደራርቱ ሐ. በፍጥነት መ. ትሮጣለች

መመሪያ፡- ቀጥሎ በቀረበው ምሣሌ መሠረት ተከታዩን ጥያቄ ሥራ። ገፅ 9

ምሣሌ፡- አተረፈ ብሎ ከሰረ ይላል

1. ተዳከመ ብሎ _____ ይላል።
2. አነፀ ብሎ _____ ይላል።
3. አስፋፋ ብሎ _____ ይላል።

መመሪያ፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ

1. "በየዋህነት" በሚለው ቃል ውስጠ መነሻና መድረሻ ቅጥያዎቹ_____ ናቸው።
   ሀ. ነ-እና-ት ለ. በ-እና-ነት ሐ. በየ-እና-ት መ. በ እና-ህነት
2. ቤት ብሎ ቤታችን ካለ የተጨመረው ቅጥያ _____ ነው።
   ሀ. -ታችን ለ. -ችን ሐ. -ኣችን መ. -ን
3. "ተቆጣችን" በሚለው ቃል-ን የሚለው ቅጥያ_____ ያመለክታል።
   ሀ. ያታ ለ. ብዙ ቁጥር ሐ. ባለቤት መ. ተሳቢ

መመሪያ ፤ተስማሚውን በመምረጥ መልስ (ገፅ 28)፤

1. ከሚከተሉት በማጥበቅና በማላላት ሁለት ትርጉም የማይሰጠው የቱ ነው?
   ሀ. መላክ ለ. መናጥ ሐ. መጣል መ. መዛል
2. ቤቱ ሰፊ ነው። በሚለው ዓረፍተ ነገር የተሰመረበት ቃል _____
   ሀ. ጠብቆ ይነበባል ሐ. ጠብቆና ላልቶ አይነበብም
   ለ. ላልቶ ይነበባል መ. ጠብቆም ላልቶም ይነበባል

በአጠቃላይ ከ2001 ዓ.ም.እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ ባሉት ዓመታት ውስጥ የወጡትን የሥነ ልሣን ጥያቄዎች ቀደም ብለን የተመለከትናቸውን ይመስላሉ። በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ከተካተቱት ዝርዝር የትምህርት ይዘቶችና መልመጃዎች ጋር ስናመሳክር፣ አንድም የስነ ልሣን ጥያቄ ከመፅሐፉ ውጭ የሆነ የለም። ስለዚህ ስነ ልሳንን በሚመለከት በፈተናውና በመፅሐፉ መካከል ያለው እጅግ የተቆራኘ ነው።

የቃላት ጥያቄዎች፤

ከሰንጠረዡ እንደተመለከትነው በ2001 እና በ2004 ዓ.ም እንደየቅደም ተከተላቸው ከ9 እስከ 10 የሚሆኑ የቃላት ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን በቀሪዎቹ ሁለት ሁለት ዓመታት ደግሞ አስራ አምስት-አስራ አምስት የቃላት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ይህም የፈተናውን ሩብ ያህል የሚሸፍን ነው።

ቃላትን በሚመለከት የቀረቡት ጥያቄዎች ተመሳሳይ ናቸው። ይኸውም ለቃላት ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍች መፈለግ፣ ለፈሊጣዊ አነጋገሮች ትርጉም መስጠት፣ የተለየ ትርጉም የያዘውን ቃል ፈልጎ ማውጣት፣ የሚሉ ናቸው። የቃላት ፈተና ማቅረቢያ ስልቱም ቢሆን የቃላትን ቀጥተኛ ፍች እና አውደዊ ፍቺ በመፈለግ ላይ የሚያተኩር ነው።

ቀደም ብለን በሰንጠረዥ 1 ላይ እንደተመለከትነው፣ ቃላትን በሚመለከት በመፅሐፉ ውስጥ በርካታ መልመጃዎችና ጥያቄዎች ይገኛሉ። የአጠያየቅ ስልታቸውም ፈተናዎቹ ከቀረቡበት የአጠያየቅ ስልት ጋር ተመሳሳይ ነው። ስለዚህ ቃላትን በሚመለከት ከ2001 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር የጠበቀ ዝምድና አላቸው።

የሥነ ጽሑፍ ጥያቄዎች፤

ሥነ ዕሁፍን በሚመለከት ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ ከስልጣ ጥያቄዎች ውስጥ ከስድስት እስከ ሰባት የሚደርሱ ጥያቄዎች ቀርበው ይገኛሉ። ይህም የፈተናውን 12.9% የሚሸፍን ነው።

እነዚህ በየዓመቱ የሚቀርቡ የሥነ ዕሑፍ ጥያቄዎች ምን ላይ የሚያተኩሩ ናቸው? የሚለውን ስንመለከት በስነ ቃሎች፣ በግጥሞች፣ በልቦለዶች፣ በተውኔቶች እና በድርሰቶች ላይ ነው። ዋናው ነገር እነዚህ ጥያቄዎች በየዓመቱ በፈተና ውስጥ መካተት አለመካተታቸው ሳይሆን፣ ተማሪዎች ከላይ የተጠቀሱትን ይዘቶች ተምረዋል ወይ? በመጽሐፉ ውስጥ ተካተው ይገኛሉ ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው። የነዚህን ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ደግሞ መማሪያ መፅሐፉን መፈተሽ ያስፈልጋል።

በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከተውኔት ውጭ ሁሉም የስነ ዕሁፍ ይዘቶች በዝርዝር ተካተው ይገኛሉ። ተውኔትን በሚመለከተም ሠባተኛ ክፍል ላይ እንደተማሩ ማረጋገጥ ተችሏል። ምክንያቱም በሰባተኛ ክፍል የተማሪው መፅሐፍ ላይ ገፅ 51 "ተውኔት/ድራማ" በሚል ርዕስ ሥር በዝርዝር ሰፍሮ ይገኛል። ከዚህ ውጭ ያሉት የስነ ዕሁፍ ዘርፎች በሠንጠረዥ 1 ሥር በየትኛው ገፅ ላይ እንደሚገኙ ጭምር ስነ ዕሁፍን በተመለከተ ቀርቦ ይገኛል።

በአጠቃላይ በአራቱም ዓመታት ውስጥ የወጡ የሥነ ጽሁፍ ጥያቄዎች ከመፅሐፉ ጋር ያላቸው ዝምድና እጅግ የጠበቀ ነው።

የንባብ ክሂል ጥያቄዎች፤

ከ2001ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ የቀረቡትን ምንባቦች ስንመለከት በ2001 ዓ.ም አራት አንቀፆች ያሉት ምንባብና አንድ አጭር ግጥም ቀርቧል። በ2002 ዓ.ም. በሦስት አንቀጾች የተደራጀ አጭር ፅሁፍ፣ በ2003 ዓ.ም አምስት አንቀፆች ያሉት ምንባብ፣ እንዲሁም በ2004 ዓ.ም. አራት አንቀፆች ያሉት ምንባብ ቀርቧል።

በእያንዳንዱ አመት ከ11-20 የሚደርሱ የምንባብ ጥያቄዎች ተካተዋል። ይህም 23.3 በመቶ የሚሆነው የምንባብ ጥያቄ ነው።

በአራቱም ዓመታት ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች የሚያመሳስሏቸው በምንባቡ ላይ የተመሰረቱ ፈተናዎች መሆናቸው ነው። ልዩነታቸው ደግሞ በ2001 ዓ.ም. የፈተና ዘመን የግጥም ጥያቄ መቅረቡ፣ እንዲሁም የንባብ ስልትን የሚመለከት በ2001 ዓ.ም በጥያቄ ቁጥር 57 እና በ2002 ዓ.ም. በጥያቄ ቁጥር 29 ላይ ተመሳሳይ ጥያቄዎች ቀርበው መገኘታቸው ነው።

እስኪ እነዚህን ተመሳሳይ ጥያቄዎች በመጥቀስ መፅሐፉ ውስጥ የንባብ ስልትን በሚመለከት ከቀረቡ መመሪያዎች ጋር እናነፃፀር፤

29. ከሚከተሉት አንዱ የንባብ ፍጥነትን ያግዛል።

A. የሚያነቡትን ፅሁፍ በጣት እየጠነቆሉ ማንባብ

B. ተነበው የታለፉ ቃላትንና ሐረጎችን መልሶ ማየት

C. የቃላትን ሰብስብን በአንድ እይታ ለማንበብ መሞከር

D. የሚያነቡትን ጽሑፍ ቃላት እየቆጠሩ ማንበብ

57. ከሚከተሉት ውስጥ በፍጥነት ንባብ ወቅት ተገቢ የሆነው ልምድ የትኛው ነው?

A. የሚያነቡትን ፅሁፍ በጣት እየጠነቆሉ ማንበብ

B. ከንፈርን እያነቃነቁ ድምፅ በማሰማት ማንበብ

C. ቃላትን እየቆጠሩ ማንበብ

D. የሚያነቡትን ፅሁፍ አላማ በቅድሚያ ለመገመት መሞከር

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ ሁለት ተቀራራቢ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ወደ ተማሪው የመመሪያ መፅሐፍ ውስጥ ስንገባ የሚከተለውን እናገኛለን።

የፍጥነት ንባብ መመሪያ፤

የንባብ ፍጥነትን ለማሻሻል የሚከተሉትን ነጥቦች ማስተዋል ያስፈልጋል፤

1. በቅድሚያ የምታነቡትን ዕሁፍ ዓላማ ለመገመት ሞክሩ።
2. ከንፈርን እያነቃነቁ፣ድምፅ እያሰሙ ማንበብ የዓይንን እንቅስቃሴ ፍጥነት ስለሚቀንስ ስታነቡ ከንፈራችሁን አታነቃንቁ።
3. ስታነቡ በጣታችሁ አትጠቁሙ።
4. ስታነቡ ቃላትን እየለያችሁ ከማንበብ ይልቅ ሐረጎችንና ዓረፍተ ነገሮችን በአንድ ላይ አንብቡ፣ ወዘተ. የሚሉ መመሪያዎች ቀርበዋል።

እዚህ ላይ ለማንሣት የተፈለገው ነጥብ የጥያቄዎችን መመሳሰል ወይም የጥያቄዎቹን ቀጥተኛ መሆን ለማነፃፀር ሣይሆን የፈተናዎቹንና የመማሪያ መፅሐፉን የጠበቀ ቁርኝት ወይም ዝምድና ለማሣየት ነው።

በአጠቃላይ ምንባብን በሚመለከት የሚወጡ ጥያቄዎች የግንዛቤ ጥያቄዎች በመሆናቸው፣ እንደሌሎቹ ክሂሎች ዝርዝር የትምህርት ይዘት ብዛት ስለሌላቸውና የአጠያየቅ ስልታቸውም አንድ ዓይነት በመሆኑ ከተማሪው መፅሐፍ ጋር የተራራቀ ነው።

የጽሕፈት ክሂል ጥያቄዎች

ዕሀፈትን በሚመለከት በእያንዳንዱ የፈተና ዘመን ከ10 እስከ 15 የሚደርሱ ጥያቄዎች እንደሚካተቱ ከሰንጠረዡ መረዳት ይቻላል። ይህም ከሚወጡት ጠቅላላ ጥያቄዎች ውስጥ 13.3 ከመቶ የሚሸፍን መሆኑን የቀረበው ስሌት በግልፅ ያሣያል።

ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በቀረቡት ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡትን ዝርዝር ይዘቶች ስንመለከት የሚከተሉትን እናገኛለን፤ ድርሰት፣ የደብዳቤ አይነቶች (ደብዳቤ)፣ ሥርዓተነጥቦች፣ አንድን መልዕክት በተለያየ አባባል መግለፅ፣ ምክንያትና ውጤት፣ የሕይወት ታሪክ፣ ዘገባና ቃለ ጉባዔ በፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው ይገኛሉ።

በአራት ዓመታት ውስጥ የቀረቡትን የጽሀፈት ክሂል ፈተናዎች ከመፅሐፉ ጋር መዛመድ አለመዛመዳቸውን በምንፈትሽበት ጊዜ ሁለት ጥያቄዎች ከመፅሐፉ ውጭ ሆነው እናገኛቸዋልን። እነዚህም ጥያቄዎች በስምንተኛ ክፍል መፅሐፍ ውስጥ ብቻም ሳይሆን በሰባተኛ ክፍል መፅሐፍ ውስጥም አናገኛቸውም። ስለዚህ የፅሀፈት ክሂል ጥያቄዎችን በተመለከተ የተወሰነ ችግር እንዳለ መመልከት ይቻላል።

እነዚህ በፅሀፈት ክሂል ሥር የሚገኙት ዝርዝር የትምህርት ይዘቶች ምን ምን ናቸው? የቀረቡትስ በየትኛው ዓመተ ምሕረት ነው? ስንል የሚከተለውን መልስ ከፈተናዎቹ እናገኛለን፤

በ2002 ዓ.ም. ሥርዓተ ነጥብን በሚመለከት በጥያቄ ቁጥር 45 ላይ፣ እንዲሁም በ2004 ዓ.ም በጥያቄ ቁጥር 13 ላይ ቀርቧል። ከዚህ በተጨማሪም ቃለ ጉባኤን ሚመለከት ጥያቄ በ2001 ዓ.ም በጥያቄ ቁጥር 29 ላይ ቀርቦ ይገኛል።

በ2002 ዓ.ም. እና በ2004 ዓ.ም የቀረቡት ጥያቄዎች ከዚህ የሚከተለውን ይመስላሉ።

45. "ከአዲስ አበባ <u>እስከ</u> ድሬደዋ ድረስ ለመጓዝ በተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶች መጠቀም ይቻላል።" በሚለው በተሰመረበት ቃል ምትክ የትኛውን ሥርዓተ ነጥብ መጠቀም ይቻላል? (የ2002ዓ.ም ጥያቄ)

A.ሙሉ ሰረዝ

C. ድርብ ሰረዝ

B.ነጠላ ሰረዝ

D. ሁለት ነጥብ

13. "ከመጋቢት 26 <u>እስከ</u> ሰኔ 25 ድረስ የሚቆየው ወቅት ፀደይ በመባል ይታወቃል። በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበትን ቃል ሊተካ የሚችለው የትኛው ሥርዓተ ነጥብ ነው? (የ2004ዓ.ም ጥያቄ)

A. እዝባር/

C. ሙሉ ሠረዝ-

B.ቅንፍ ( )

D. ነጠላ ሠረዝ፣

በ2001 ዓ.ም. ቃለ ጉባዔን በሚመለከት የቀረበው ጥያቄ ደግሞ የሚከተለው ነበር።

29. የሴት ወታደር ትርሃስ በክፍለ ጦሯ አንድ ኮሚቴ ውስጥ በጸሀፊነት ስታገለግል፣ የኮሚቴውን ሰብሳባዎች ሂደት በተመለከተ በኃላፊነት የምታዘጋጀው ሰነድ ምን ይባላል?

A. የስብሰባው ሂደት ዘገባ

B. የስብሰባው ሂደት ቃለ ጉባዔ

C. የሰብሰባው ሂደት ማስታወሻ

D. የስብሰባው ሂደት አመልካች ደብዳቤ

በአጠቃላይ የፅሀፈት ክሂልን በሚመለከትከመማሪያ መፅሐፍ ጋር ያለው ዝምድና የተራራቀ ነው።

የማዳመጥ ክሂል ጥያቄዎች

የማዳመጥ ክሂልን በተመለከተ በአራት የፈተና ዓመታት ውስጥ የቀረበው አንድ ጥያቄ ብቻ መሆኑን ከሠንጠረዡ መረዳት ይቻላል። በእርግጥ በመማሪያ መፅሐፉም ውስጥ ቢሆን ለዚህ ክሂል የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነው።

ማዳመጥ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ ነው። ይሁን እንጅ በመማር - ማስተማር ሂደቱም ሆነ በፈተና ላይ የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነው። በእያንዳንዱ የአማርኛ መፅሐፍ መግቢያ ላይ "የዚህ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማዳበር ነው" የሚል መልዕክት እናገኛለን። ወደ ተግባር ሲገባ ግን ለክሂሉ መዳበር ምንም ዓይነት ትኩረት አልተደረገም።

የማዳመጥ ክሂልን በተመለከተ በ8ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ላይ ማቅረቡ ያስቸግር ይሆናል። ምክንያቱም የማዳመጥን ክሂልን ለመፈተን መጀመሪያ ለተማሪው የሚደመጥ ነገር ሊቀርብለት ይገባል። ይህን ለማድረግ ደግሞ በብሔራዊ ፈተና ላይ አይቻልም። ይሁን እንጅ ቄውውት፣ ውይይት፣ ክርክር፣ የማዳመጥ መመሪያዎች፣ ወዘተ. የዚህ ክሂል ዘርፎች በመሆናቸው "በቲዎሪ" ደረጃ በርከት ያሉ ጥያቄዎችን ማቅረብ ይቻል ነበር።

ለክሂሉ የትኩረት ማነስ እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው ፣ተማሪዎች ወደ መደበኛ ትምህርት ቤት ከመግባታቸው በፊት ንግግርን በልምድ ያውቁታል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። ነገር ግን ክሂሉን በልምድ ያውቀዋል የሚባለው ወይም ሊያውቅ የሚችለው በቋንቋው አፍ-ፈት የሆነው ተማሪ እንጂ ኢ-አፍ-ፈት የሆነው ተማሪ አይደለም። ለሁሉም ይህ የጥናቱ ዋነኛ ትኩረት ወይም አላማ አይደለምና ወደሚቀጥለው ርዕሰ ጉዳይ መግባቱ የተሻለ ይሆናል።

በመጀመሪያው አንቀፅ ላይ እንደተገለፀው ከ2001 እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ የማዳመጥ ክሂልን በተመለከተ የቀረበው ጥያቄ አንድ ብቻ ሲሆን፣ እሱም በሚከተለው መልክ የቀረበ ነበር።

58. ከአንድ የውይይት ተሳታፊ ከሆነ ሰው የሚጠበቀው ተገቢ ተግባር የትኛው ነው?

A. የሚያዳምጡትን ዋናና ዝርዝር ሀሳቦች በሙሉ ለመለየት መሞከር

B. የአንዳንድ ሰዎች ንግግር ለውይይቱ ጠቃሚ እስካልሆነ ድረስ ከማጥላላትና ከማንኳሰስ አለመታቀብ

C. አስተያየት መስጠት እንዲቻል ከተለያዩ ተናጋሪዎች ሀሳቦችን በማስታወሻ ለመያዝ መሞከር

D. በውይይቱ ንግግር የሚያደርጉ ሰዎች የሚየቀርቡት ሀሳብ ስህተት ካለበት፣ ወዲያውኑ ንግግራቸውን በማቋረጥ ልክ አለመሆናቸውን በማንቋሸሽ ጭምር መግለፅ

ከላይ የቀረበውን ጥያቄ ስንመለከት ተግባራዊ ጥያቄ ወይም ተማሪው አዳምጦ የሚመልሰው ሳይሆን በግንዛቤ ላይ የተመሰረተ ጥያቄ ወይም የእውቀት ጥያቄ ነው። ምክንያቱም ተማሪው ከዚህ በፊት የማዳመጥ መማሪያዎችን ስለሚያውቅ በቀላሉ ሊመልስ ይችላል።

ይህን ጥያቄ ይዘን የተማሪውን የመማሪያ መፅሐፍ ስንፈትሽ በምዕራፍ ሰባት፣ በገፅ 1 ላይ እንደሚከተለው ቀርቦ እናገኛለን።

1. አንድን መልዕክት ስታዳምጥ ጆሮህን ብቻ ሠጥተህ ቁጭ አትበል።
2. የሰዎችን ንግግር ስታዳምጥ አታቋርጣቸው፤ ማቋረጥ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በስርዓት ይቅርታ በመጠየቅ ያቋረጥክበትን ምክንያት ጠቁም፣
3. ለሰዎች ንግግር ተገቢውን ግምት ስጥ እንጅ በንቀት መንፈስ ለማንኳሰስና ለማጥላላት አትሞክር፣
4. ከዳመጥከው ንግግር ውስጥ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ለመለየት ሞክር፣

በተራ ቁጥር አምሳ ስምንት ላይ የቀረበውን ጥያቄ ከዚህ ምንባብ ጋር ስናነፃፅር ቃል በቃል የተገለበጠ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ዋናው ነገር የፈተናው መመሳሰል ሳይሆን፣ በፈተናውና በመፅሐፉ ይዘት መካከል ምን ያህል የጠበቀ ዝምድና እንዳለ፣ ወይም፣ "ያስተማርከውን ፈትን" የሚለውን የፈተና መርህ በተግባር የሚያሳይ መሆኑን በግልፅ ማየት ይቻላል።

በአጠቃላይ የማዳመጥ ክሂልን አስመልክቶ ከመፅሐፉ ጋር ዝምድና አላቸው ለማለት መጀመሪያ የማዳመጥ ክሂልን የሚመለከቱ ጥያቄዎች በፈተናው ውስጥ ተካተው ሊገኙ ይገባል። ያለበለዚያ ግን ጥያቄዎች በሌሉበት ዝምድናቸውን መናገር አይቻልም።

የንግግር ክሂል ጥያቄዎች

ይህ ክሂል ልክ እንደ ማዳመጥ ክሂል ሁሉ በፈተናም ይሁን በመማር ማስተማሩ ሂደት የተሰጠው ሽፋን እጅግ አነስተኛ ነው። ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለውም ከአራቱ የፈተና ዓመታት ውስጥ የቀረበው ጥያቄ ሦስት ብቻ መሆኑን ነው። በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ያለው የመልመጃ ብዛት 3 ወይም 3.6. ከመቶ ብቻ እንደሆነ በሠንጠረዥ 2 ላይ መመልከት ይቻላል።

ለዚህ ክሂል ትኩረት ማነስ በማዳመጥ ክሂል ላይ የሰጠነውን ምክንያት መጥቀስ ይቻላል። ይኸም ተማሪው ከቤቱ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጣ ማዳመጥና መናገርን አውቆ ነው ከሚል ግምት የመነጨ ነው። ይሁን እንጅ ሁሉም ተማሪ በቋንቋው መናገር የሚችል ነወይ የሚለው ጉዳይ ግምት ውስጥ የገባ አይመስልም።

በተለይም የሀገር መከላከያ ሠራዊት ከተለያየ ብሔረሰብ የተውጣጣ በመሆኑ ሁሉም የርቀት ተማሪ አማርኛ ቋንቋን ይናገራል ማለት አይቻልም። በተለይም እነዚህን ክሂሎች እንደመደበኛው መርሐግብር በርቀት ትምህርት ለማስተማር በጣም አስቸጋሪ ነው።

ምክንያቱም ተማሪው የማዳመጥና የንግግር ክሂሉን ለማዳበር በክፍል ውስጥ እርስ በርስ መወያየት፣ መከራከር፣ ሚውውት ማድረግ፣ መምህሩ የሚያነበውን አዳምጦ መልስ መስጠት፣ ወዘተ ያስፈልጋል። በርቀት ትምህርት መርሐ ግብር እነዚህን ነገሮች ለመተግበር ያስቸግራል።

የጥናቱ ዋና ርዕሰ ጉዳይ ወደ ሆነው የንግግር ፈተና እና የመማሪያ መፅሐፉ ዝምድናን እንመልከት። ሀሳቡን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ንግግርን በሚመለከት የወጡትን ፈተናዎች በቅድሚያ ማየቱ ተገቢ ነው። በ2003 ዓ.ም በጥያቄ ቁጥር 31 ላይ የወጣው ፈተና ከዚህ የሚከተለውን ይመስል ነበር፤

31. በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚደረግ ንግግር አድማጭን ሳቢና ማራኪ እንዲሆን የሚያደርገው የትኛው ነው?

A. የንግግርን ርዕሰ ጉዳይ ማያስተዋውቁ በቀጥታ ወደ ዋናው የንግግሩ ፍሬ ሀሳብ መሸጋገር

B. ከንግግሩ ታዳሚዎች መካከል የተወሰኑት ለንግግሩ በሚሰጡት ትኩረት ማበረታታት

C. የሚያደርጉት ንግግር በአካል እንቅስቃሴ የታጀበ እንዲሆን በማድረግ የአድማጭን ትኩረ ለማግኘት መጣር

D. በንግግሩ ሂደት ከአድማጮች ስሜትና ፍለጎት ይልቅ ለመልዕክቱ መተላለፍ የበለጠ ትኩረት መስጠት

ሊላው በ2002 ዓ.ም. ጥያቄ ቁጥር 30 እና በ2004 ዓ.ም ጥያቄ 60 የወጣው የንግግር ጥያቄ የሚከተለው ነበር።

30. ለአንድ የውይይትና የክርክር ተሳታፊ የማያስፈልገው የትኛው ነው?

A. የዓይን አጣጣልን ማሣመር

B. በግልፅ ቋንቋ መጠቀም

C. የጊዜ ገደብ ማክበር

D. መልሱ አልተሰጠም

60. ለክርክር የሚያመቸው የትኛው ርዕሰ ጉዳይ ነው?

A. ታላቁ የህዳሴ ግድብ የኢትዮጵያ ኩራት ነው።

B. ለታላቁ የህዳሴ ግድብ የቦንድ ግዥው እንደቀጠለ ነው።

C. ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ጎረቤት ሃገሮች ያላቸውን ድጋፍ መግለፃቸው ያስደስታል።

D. ታላቁ የህዳሴ ግድብ ለኢትዮጵያ እንጅ ለጎረቤት ሀገሮች ምንም ፋይዳ የለውም።

ከዚህ በላይ የቀረቡትን ሦስት የንግግር ክሂል ጥያቄዎች ከመማሪያ መፅሐፉ ያላቸውን ዝምድና ለመገንዘብ ያመች ዘንድ ቀጥሎ በመፅሐፉ ውስጥ ያሉት የንግግርና የክርክር አቀራረብ መመሪያዎችን እንመልከት።

2. የንግግር አቀራረብ መመሪያ ገፅ 55

2.1. የንግግርህን ዓላማ ባጭሩ አስተዋውቅ፤

2.2. ርዕሱን ለአድማጮች በሚገባ አስተዋውቅ፤

2.3.ንግግርህን ስታቀርብ የድምፅ ቃናና አወራረድ፣ የፍጥነት ኃይል መጠን እንዲሁም የአካል እንቅስቃሴ አድማጮችህን የሚማርክ ይሁን፤

2.4. ንግግርህን በተሰጠህ የጊዜ ገደብ እንዲያልቅ አድርግ

2.5. ቋንቋው የአድማጮችን የትምህርት ደረጃ፣ ዕድሜ፣ የኑሮ ደረጃ ወዘተ ያገናዘበ ይሁን፤

2.6. ንግግርህን በምታደርግበት ጊዜ የአድማጮችህን ስሜትና ፍላጎት ጠብቅ፣ ወዘተ. የሚሉ መመሪያዎች በግልፅ ተዘርዝረው እናገኛለን።

የንግግር ክሂልን በሚመለከት በተለያዩ የፈተና ዓመታት የወጡ ጥያቄዎችንና በመፅሐፉ ውስጥ ያሉ የትምህርት ይዘቶች በንፅፅር መልክ እንዲቀርቡ የተፈለገበት ዋናው ምክንያት የጥያቄዎች ድግግሞሽ መኖሩን ወይም ፈተናዎቹ በቀጥታ ከመማሪያ መጽሐፉ የተገለበጡ መሆናቸውን ለማመልከት ሳይሆን፣ ተማሪዎች የተፈተኑት የተማሩትን እንደሆነ፣ እንዲሁም በመማሪያ መጽሐፉና በፈተናዎቹ መካከል ያለውን የጠበቀ ዝምድና ለማሣየት ነው።

የይዘት ተገቢነት (Content Validity)

አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት አለው ሊባል የሚችለው ፈተናው ከየክሂል ዘርፎቹ ተመጣጣኝ ወይም ወካይ የሆኑ ናሙናዎችን አካቶ ሲገኝ እንደሆነ ምሁራን ይስማማሉ። በለጠ ያዕቆብ (1995) የይዘት ተገቢነትን በሚመለከት Alderson (1995፡171) በመጥቀስ "የአንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት የሚወሰነው የፈተናው ይዘት ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ ሲተነተን፣ ወካይ የሆኑ ተገቢነት ያላቸውን የቋንቋ ክሂሎች መያዝ አለመያዝ አንፃር ነው።" በማለት ገልፆታል።

ከዚህ አኳያ በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር ከ2001 እስከ 2004 ዓ.ም. ለስምንተኛ ክፍል የተዘጋጁትን ፈተናዎችና መማሪያ መፅሐፉን ከይዘት ተገቢነት አንፃር ምን እንደሚመስሉ ለመዳሰስ እንሞክር። ሁሉንም የክሂል ዘርፎች በመጥቀስ በዝርዝር መመልከቱ አስፈላጊ ስላልሆነ ከክሂልና ከዕውቀት ዘርፎች አንድ አንድ በመምረጥ ማቅረቡ የተሻለ ነው።

ሠንጠረዥ 3፣ በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ውስጥ ዝርዝር የጽፈት ትምህርት ይዘቶችን የሚመለከቱ መልመጃዎችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

ተ.ቁ	ዕሀፈትን የሚመለከቱ ዝርዝር የትምህርት ይዘቶች	የጽሕፈት መልመጃዎች					
		ጽሕፈትን ሚመለከቱ መልመጃዎች ብዛት			ዕሀፈትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ብዛት		
		መልመጃዎች የሚገኙበት ገፅ	በቁጥር	ከመቶኛ ስሌት	መልመጃዎቹ የሚገኙበት ገፅ	በቁጥር	በመቶኛ ስሌት
1.	አንቀጽ	35፣36፣37	1	16.6	35፣36፣37	26	34.2
2.	ድርሰት	41	1	16.6	41	1	1.3
3.	ደብዳቤ	-	0	0	-	0	0
4.	ሥርዓተ ነጥብ	26	1	16.6	26.27፣28	24	31.5
5.	የህይወት ታሪክ	106	1	16.6	106	2	2.6
6.	ዘገባ	-	0	0	-	0	0
7.	ቃለ ጉባዔ	-	0	0	-	0	0
8.	አንድን ሀሳብ በተለያየ አገላለፅ መግፍ	-	0	0	-	0	0
9.	መንስኤና ውጤት	57	1	16.6	58.59	15	19.7
10.	አያያዥ ቃላትን በመጠቀም የተሟላ ሀሳብ መግፍ	50	1	16.6	50፣51	8	10.5
	ድምር		6	100		76	100

ከሠንጠረዡ መረዳት የሚቻለው ስለ ጽሕፈት ክሂል በተመለከተ በመፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች ብዛት አንቀፅ 26 (34.2) ከመቶ፣ ሥርዓተ ነጥብ 24 በመቶኛ ሲሰላ 31.5 ከመቶ መንስኤና ውጤት 15 (19.7) ከመቶ በመያዝ ከአንድ እስከ ሦስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ። አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ሀሳብን በተሟላ መንገድ መግለጽ 8 በመቶኛ ስሌት 10.5፣ የሕይወት ታሪክ 2(2.6) ከመቶ፣ እንዲሁም ድርሰት 1(1.3) ከመቶ ሽፋን እንደያዙ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት ይቻላል። ቀሪዎቹ ደብዳቤ፣ ዘገባ፣ ቃለ ጉባኤና አንድን ሀሳብ በራስ አባባል መግለፅን የሚመለከቱ መልመጃዎች በመፅሐፉ ውስጥ አልቀረቡም። ነገር ግን የተወሰኑት ዝርዝር ይዘቶች በፈተናዎች ውስጥ ተካተው ይገኛሉ። ይህ ደግሞ በመፅሐፉና በፈተናዎች መካከል ያለው ዝምድና የተራራቀ እንዲሆን አድርጎታል።

ለምሣሌ ደብዳቤን በተመለከተ በመልመጃ መልክ ባይቀርብም በመፅሐፉ ውስጥ በዝርዝር ተብራርቷል፤ በፈተናዎችከ2004 ዓ.ም በስተቀር ተካቶ ይገኛል። ቃለ ጉባዔ በ2001 ዓ.ም በጥያቄ ቁጥር 29 ላይ የቀረበ ሲሆን በመፅሐፉ ውስጥ ግን ዘገባን የሚመለከት ምንም ነገር የለም። ለንፅፅር ያመች ዘንድ ይህን ከተመለከትን ወደ ዋናው ጉዳይ እንግባ።

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የይዘት ተገቢነት ሲባል ወሳይ የሆኑ ናሙናዎች መካተት አለመካተታቸውን የሚመለከት ነው። ከዚህ አንፃር ሁኔታውን በግልፅ ለማየት ያመች ዘንድ ቀጣዩን ሠንጠረዥ እንመልከት፤

ሰንጠረዥ 4 ፣ ዝርዝር የጽሕፈት ክሂል ይዘትን በተመለከተ ከ2001 ዓ.ም.እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ የወጡ ጥያቄዎችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

ተ.ቁ	ዕሀፈትን የሚመለከቱ ዝርዝር የትምህርት ይዘቶች	ከ2001 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ዝርዝር የዕሀፈት ክሂል ይዘት ያላቸውን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ብዛት										
		2001 ዓ.ም			2002 ዓ.ም			2003 ዓ.ም			2004 ዓ.ም	
		የጥያቄ ተራ ቁጥር	ብዛት	%	የጥያቄ ተራ ቁጥር	ብዛት	%	የጥያቄ ተራ ቁጥር	ብዛት	%	የጥያቄ ተራ ቁጥር	ብዛት
1.	አንቀጽ	27	1	8.3	42	1	9.1	29፣44፣46	3	42.8	33፣35	2
2.	ድርሰት	-	0	0	37	1	9.1	-	0	0	-	0
3.	ደብዳቤ	30፣31	2	16.6	40፣41	2	18.2	45	1	14.2	-	0
4.	ሥርዓተ ነጥብ	34፣35፣36፣37	4	33.3	43፣44፣45፣46	4	36.3	43፣48፣49	3	42.8	11፣12፣13፣14	4
5.	የህይወት ታሪክ	28	1	8.3	38	1	9.1	-	0	0	34	1
6.	ዘገባ	-	0	0	-	0	0	-	0	0	-	0
7.	ቃለ ጉባዔ	29	1	8.3	-	0	0	-	0	0	37	1
8.	አንድ ሀሳብ በተለያየ አገላለፅ መፃፍ	26	1	8.3	-	0	0	-	0	0	52	1
9.	መንስኤና ውጤት	32	1	8.3	24	1	9.1	-	0	0	-	0
10.	አያያዥ ቃላትን በመጠቀም የተሟላ ሀሳብ መፃፍ	33	1	8.3	60	1	9.1	-	0	0	-	0
	ድምር		12	100		11	100		7	100		10

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በ2001 ዓ.ም የፈተና ዘመን የሥርዓተ ነጥብ ጥያቄን በሚመለከት 33.3 ከመቶ በመያዝ በመጀመሪያው ደረጃ ላይ ሲቀመጥ፣ ደብዳቤ 16.6 ከመቶ ይዞ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ከዘገባ ውጭ ያሉ የትምህርት ይዘቶች ደግሞ የ8.3 በመቶ ድርሻ በመያዝ በተመሣሣይ ደረጃ ላይ ይገኛሉ። ዘገባን በሚመለከት በመፅሐፉ ውስጥ ተካቶ እንደማይገኝ ቀደም ብለን ለማየት ሞክረናል።

በአጠቃላይ ከሌሎቹ የፈተና ዓመታት ጋር ሲነፃፀር የ2001 ዓ.ም ፈተና ከተገቢነት አኳያ የተሻለ ነው።

በተመሣሣይ በ2002፣ 2003 እና 2004 ዓ.ም. የፈተና ዘመን የሥርዓተ ነጥብ ጥያቄ የመጀመሪያውን ድርሻ ይዞ ይገኛል። የ2002 ዓ.ም. የፈተና ዘመን ዘገባ፣ ቃለ ጉባኤና አንድን ሀሳብ በራስ አባባል መግለፅ የሚሉ ዝርዝር ይዘቶችን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን አላካተተም። እነዚህ ዝርዝር የትምህርት ይዘቶች ደግሞ በመፅሐፉ ውስጥ የሉም። ይህም ከፈተናዎችና ከመፅሐፉ ዝምድና አንፃር የተዋጣለት ነው ማለት ይቻላል። ከተገቢነት አኳያም በመፅሐፍ ውስጥ ያልተካተቱን የትምህርት ይዘት በፈተና ውስጥ በወሳይ ናሙናነት ማቅረብ አይቻልም። በአጠቃላይ ከክሂል አንፃር ስንመለከተው ደግሞ ወሳይ ክሂሎችን አካቶ ይዟል።

የ2003 ዓ.ም የፈተና ዘመን ከተገቢነት አንፃር ችግር ያለበት መሆኑን ከሠንጠረዡ መረዳት ይቻላል። ይህ ሲባል ግን ከክሂል አኳያ ወሳይ ናሙናዎች የሉም ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ ከዝርዝር የትምህርት ይዘት አኳያ ስንመለከተው ድርሰት፣ የህይወት ታሪክ አጻጻፍ፣ መንስኤና ውጤት እንዲሁም አያያዥ ቃላትን በጠቀም ሀሳብን የሚያስተላልፉ ጥያቄዎች የሉም። አራት የሥርዓተ ነጥብ ጥያቄዎችን በአንድ የፈተና ዘመን ከማካተት ይልቅ ለሌሎች የትምህርት ይዘቶች ድርሻ ቢሰጥ የተሻለ ይሆን ነበር። የ2004 ዓ.ም የፈተና ዘመንም ተመሣሣይ ችግር ያለበት እንደሆነ ከሠንጠረዡ መረዳት ይቻላል።

ሠንጠረዥ 5 ፣ በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ዝርዝር የሥነ ጽሑፍ ትምህርት ይዘቶች

ተ.ቁ	ሥነ ፅሑፍን የሚመለከቱ ዝርዝር የትምህርት ይዘቶች	የሥነ ጽሑፍ መልመጃዎች					
		ሥነ ፅሑፍን የሚመለከቱ መልመጃዎች ብዛት			ሥነ ፅሑፍን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ብዛት		
		መልመጃዎች የሚገኙበት ገፅ	በቁጥር	ከመቶኛ ስሌት	መልመጃዎቹ የሚገኙበት ገፅ	በቁጥር	ከመቶኛ ስሌት
1.	ሥነ ግጥም	90	1	16.5	90፣91	5	8.5
2.	ምሣሌያዊ አነጋገር	72፣82	02	33.4	72፣73፣74	35	59.3
3.	ልቦለድ	-	0	0	-	0	0
4.	ተውኔት	-	0	0	-	0	0
5.	ዘይቤ	79	1	16.5	79	08	13.6
6.	ድርሰት	41	1	16.5	41	1	1.7
7.	ቅኔ	96	1	16.5	96	10	16.9
	ድምር		6	100		59	100

ከቀረበው ሠንጠረዥ እንደምንመለከተው ምሣሌያዊ አነጋገር 59.3 ከመቶ በመያዝ ከመጀመሪያ ደረጃ ላይ ሲገኝ፣ ቅኔ 16.9 ከመቶ፣ ዘይቤ 13.6 ከመቶ እንዲሁም ሥነ ግጥም 8.5 ከመቶ ድርሻ በመያዝ እንደ ቅደም ተከተላቸው ከሁለተኛ እስከ ሦስተኛ ያለውን ደረጃ ይዘዋል። ልቦለድና ተውኔትን የሚመለከቱ መልመጃዎች ግን በመፅሐፉ ውስጥ የሉም።

የመልመጃዎችን ብዛት በሚመለከት ከምሣሌያዊ አነጋገር በስተቀር ሁሉም ተመሣሣይ እንደሆኑ ከሠንጠረዡ መረዳት ይቻላል።

ከዚህ ቀጥሎ በአራቱ የፊተኛ ዓመታት ውስጥ የቀረቡትን ዝርዝር የትምህርት ይዘቶች ሠንጠረዡን መነሻ በማድረግ እንመለከታለን።

ሠንጠረዥ 6፣ ከ2001 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ዝርዝር የሥነ ጽሑፍ ትምህርት ይዘት ያላቸው ጥያቄዎችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

ተ.ቁ	ሥነ ዕውፍን የሚመለከቱ ዝርዝር የትምህርት ይዘቶች	የጥያቄዎች ብዛት										
		2001 ዓ.ም			2002 ዓ.ም			2003 ዓ.ም			2004 ዓ.ም	
		የጥያቄ ተራ ቁጥር	በቁጥር	ከመቶኛ ስሌት	የጥያቄ ተራ ቁጥር	በቁጥር	ከመቶኛ ስሌት	የጥያቄ ተራ ቁጥር	በቁጥር	ከመቶኛ ስሌት	የጥያቄ ተራ ቁጥር	በቁጥር
1.	ሥነ ግጥም	47፣49	2	25	35፣36	2	28.5	41፣42	2	18.2	49፣50	2
2.	ምሣሌያዊ አነጋገር	52፣56፣59	3	37.5	21፣23	2	28.5	33፣34፣35፣39	5	45.5	28፣29፣30፣31፣32	5
3.	ልቦለድ	53፣54	2	25	39	1	14.5	38፣47	2	18.2	56	1
4.	ተውኔት	-	0	0	-	0	0	37	1	9.1	-	0
5.	ዘይቤ	-	0	0	-	0	0	-	0	0	-	0
6.	ድርሰት	44	1	12.5	37፣56	2	28.5	60	1	9.1	46	1
7.	ቅኔ	-	0	0	-	0	0	-	0	0	-	0
	ድምር		8	100		7	100		11	100		9

ከሠንጠረዡ እንደምንመለከተው በአራቱም ዓመታት የፊተና ዘመን ዘይቤንና ቅኔን የሚመለከቱ ምንም አይነት ጥያቄዎች አልቀረቡም። ነገር ግን በመፅሐፉ ውስጥ በስፋት ተብራርተው በመልመጃ መልክ ቀርበዋል። ከዚህ አኳያ ምሣሌያዊ አነጋገርንና ግጥምን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ሲገኙ የዘይቤና ቅኔ ጥያቄዎች አለመቅረባቸው ከተገቢነት አኳያ ችግር እንዳለበት ያሣያል።

በአጠቃላይ በሀገር መከላከያ ሠራዊት የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር ከ2001 እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ ለ8ኛ ክፍል የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር ያላቸውን ዝምድና በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ተፈትሿል።

ከጥናቱ የተገኘው ውጤት የሚያሣየውም በአራቱም ዓመታት ውስጥ የተዘጋጁት ጥያቄዎች ከፅሀፈት ክሂል በስተቀር ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር እጅግ የጠበቀ ዝምድና ቢኖራቸውም ከተገቢነት አንፃር ችግር ያለባቸ መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና አስተያየት

5.1 ማጠቃለያ

በሀገር መከላከያ ሠራዊት ከ2001 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ በርቀት ትምህርት መርሐግብር የቀረቡ የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከመማሪያ መጽሐፉ ጋር ያላቸው ዝምድና ምን እንደሚመስል በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ተፈትሿል።ጥናቱን ከግብ ለማድረስ በዋና የመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍና ከ2001ዓ.ም እስከ 2004ዓ.ም ድረስ የተዘጋጁት የአማርኛ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ናቸው።ከነዚህ በተጨማሪም የሰባተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በመረጃነት አገልግሏል።

የመረጃ ምንጮችን መነሻ በማድረግ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት የሚያመለክተው መጠናቸው ይለያዩ እንጂ አራቱ የቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ማንበብና መጻፍ) እንዲሁም ሁለቱ የዕውቀት ዘርፎች (ሥነ ልሳንና ሥነ ጽሑፍ) በፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው ተገኝተዋል። እነዚህ ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች ከተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ጋር ያላቸው ዝምድና ምን ይመስላል? የተዘጋጁት ፈተናዎች ከተገቢነት አኳያ ምን ያህል የተዋጣላቸው ናቸው? በክሂሎችና በዕውቀት ዘርፎች ሥር የተካተቱት ዝርዝር የትምህርት ይዘቶች ምን ምን ናቸው? የሚሉት ርዕሰ ጉዳዮች በስፋት ተዳሰው ከጥናቱ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል።

ከ2001 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ የወጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከጽሕፈት ክሂል ጥያቄዎች በስተቀር ከተማሪው የመማሪያ መጽሐፍ ጋር እጅግ የጠበቀ ዝምድና ያላቸው መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል። የጽሕፈት ክሂል ጥያቄዎችም ቢሆኑ እንደ ሌሎቹ ጥያቄዎች ሁሉ ከመማሪያ መጽሐፍ ጋር አይዛመዱ።

በአጠቃላይ በአራቱም የፈተና ዓመታት የወጡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከተማሪው የመማሪያ መጽሐፍ ጋር እጅግ የተዛመዱ፣ተማሪው የተፈተነው የተማረውን መሆኑን የሚያመላክቱ መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል።

በአራቱም አመታት ውስጥ የተዘጋጁት ፈተናዎች ከተገቢነት አኳያ ሲፈተሹ ሁሉም ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች በጥናቱ ውስጥ ባይካተቱም ከክሂል ጽሕፈትን፣ ከዕውቀት ዘርፎች ደግሞ ሥነ ጽሑፍን በመምረጥ በዝርዝር ጥናት ተደርጎባቸዋል።

ጽሕፈት በተመለከተ በ2001 ዓ.ም እና በ2002 ዓ.ም የፈተና ዓመታት የወጡት ጥያቄዎች ከተገቢነት አንፃር ምንም ዓይነት ችግር እንደሌለባቸው ከጥናቱ የተገኘው ውጤት አመልክቷል። ነገር ግን በ2003 ዓ.ም እና በ2004 ዓ.ም የወጡ የአማርኛ ቋንቋ ጥያቄዎች ዝርዝር የጽሕፈት ክሂል ይዘት ያላቸው ጥያቄዎችን በናሙናነት አካተው ባለመያዛቸው የተገቢነት ችግር እንዳለባቸው ከጥናቱ የተገኘው ውጤት ያሳያል።

ዝርዝር የሥነ ጽሑፍ ትምህርት ይዘት ያላቸው ጥያቄዎችን በተመለከተ በአራቱም የፈተና ዓመታት ውስጥ የይዘት ተገቢነት ችግር እንዳለባቸው ከጥናቱ የተገኘው ውጤት ያስረዳል። ለምሳሌ ዘይቤና ቅኔን የሚመለከቱ ዝርዝር የትምህርት ይዘቶች በተማሪው የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በስፋት ቢቀርቡም ፣ በአራቱም የፈተና ዓመታት ዘይቤና ቅኔን የሚመለከት አንድም ጥያቄ እንደማይገኝ ጥናቱ በግልጽ አመልክቷል።

በአጠቃላይ ዝርዝር የጽሕፈት ክሂል ይዘትን በተመለከተ ጥያቄዎች የተገቢነት ችግር እንዳለባቸው ከጥናቱ የተገኘው ውጤት ያሳያል።

በክሂልና በዕውቀት ዘርፎች ሥር የተካተቱትን አጠቃላይ የትምህርት ጥያቄዎች ስንመለከት የጥያቄዎች በቁጥር አለመመጣጠን ችግር ጎልቶ እንደሚታይ፣ ይኸውም ማዳመጥንና ንግግርን የሚመለከቱ ጥያቄዎች አነስተኛ ሲሆኑ ሥነ ልሳንንና ምንባብን በተመለከተ የሚዘጋጁት ጥያቄዎች በርካታ እንደሆኑ ጥናቱ አሣይተዋል፡

5.2 አስተያየት

የስምንተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከችሎታ መለኪያ ፈተና ስር እንደሚመደብ ይታወቃል። በመሆኑም ይህ የችሎታ መለኪያ ፈተና በሚዘጋጅበት ጊዜ መሰረት የሚያደርገው መርሐ ትምህርቱንና የተማሪውን የመማሪያ መጽሐፍ ነው።

ከዚህ አኳያ በሀገር መከላከያ ሠራዊት ከ2001 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በርቀት ትምህርት መርሐግብር የቀረቡት የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከተማሪው የመማሪያ መጽሐፍ ጋር እጅግ የተዛመዱ በመሆናቸው ትክክለኛ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ናቸው። እናም በቀጣይ የሚዘጋጁት ፈተናዎች በዚህ መልኩ ቢቀርቡ መልካም ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ፈተናዎች በሚዘጋጁበት ወቅት በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት ቢያደርግ የተሻለ ነው። ይኸውም ፣

1. ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ በእያንዳንዱ የቋንቋ ክሂልና የዕውቀት ዘርፍ የሚገኙ ዝርዝር የትምህርት ይዘቶችን የሚወክሉ ጥያቄዎች አልቀረቡም። ለምሳሌ በተማሪው የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ዘይቤና ቅኔ በስፋት ቀርበው ቢገኙም በአራቱም የፈተና ዓመታት ውስጥ ዘይቤንና ቅኔን የሚመለከቱ ጥያቄዎች አልቀረቡም።

   ስለዚህ እንደዚህ ዓይነቱ ፈተና የይዘት ተገቢነት የጎደለው በመሆኑ ወካይ የይዘት ናሙናዎችን ለማካተት ቢሞከር የተሻለ ነው፤

2. የቃላት ፣የሥነ ልሳንን፣ የምንባብና የሥነ- ጽሐፍ ጥያቄዎች ሠፊውን ድርሻ ይዘው እንደሚገኙ ጥናቱ አመላክቷል።ነገር ግን ለቀሪዎቹ ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነው። ይህ ደግሞ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን በሚማሩበት ጊዜ በተወሰኑ ክሂሎች ላይ ብቻ ትኩረት እንዲያደርጉ ስለሚጋብዝ የፈተና አዘጋጆች ፈተና በሚያዘጋጁበት ጊዜ የጥያቄዎች ተመጣጣኝነት ላይ ጥንቃቄ ቢያደርጉ መልካም ነው።

3. ማዳመጥና ንግግርን የሚመለከቱ ጥያቄዎች በአራቱም የፈተና ዓመታት ውስጥ እንዳልተካተቱ፣ ቢካተቱም እጅግ አነስተኛ እንደሆኑ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት ያሣያል። ስለዚህ ፈተናውን የሚያዘጋጁት አካላት ለነዚህ ክሂሎች እንደሌሎቹ ክሂሎች ትኩረት ቢሰጣቸውና ተገቢውን የጥያቄ ሽፋን ይዘው ቢያቀርቡ ጥሩ ነው።

ዋቢ ፅሑፎች

ሀብታሙ ግዳይ (1991) "በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙ ሶስት የግል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 10ኛ ክፍል ከ1989-1990 ዓ.ም የተሰጡ አንብቦ የመረዳት ፈተና ጥያቄዎች አዘገጃጀትና አቀራረብ ግምገማ" ኤም፣ኤ.ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)።

መንገሻ ከበደ (1984) "የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና የንባብ ጥያቄዎች ግምገማ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ዲማፅ (ያልታተመ)።

ራሄል ወርቁ (2001) "ከ 1993-2000 ዓ.ም ድረስ በቀረቡት የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መልቀቂያ ፈተናዎች የመድበለ ቃላት አፈታተን"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለሁተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ የቀረበ።

ተስፋዬ ሸዋዬ። (1981)። ስነ ልሣንና ቋንቋን ማስተማር። አዲስ አበባ (ያልታተመ)።

ታረቀኝ ተፈራ (1993) "ሀገር አቀፍ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከ5-8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ጋር ያለው ዝምድና"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ዲማፅ (ያልታተመ)።

ትንሳኤ ብርሃኔ (1988) "የአማርኛ ቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ ፈተና መነሻነት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለሁተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ የቀረበ።

አለም እሸቱ (2001) መሠረታዊ የምርመርና ዘገባ አፃፃፍ። አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት

አበበ ከበደ (1975) "የ6ኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ግምገማ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ዲማፅ (ያልታተመ)።

አገኘሁ ተስፋ (1990) ዓ.ም. "አማርኛን በማስተማር ሂደት የአንብቦ መረዳት ክሂሎች የይዘትና የላህይ አግባብነትና አጠያየቅ ዘዴዎች፣ በአዲስ አበባ ትምህርት

ቤቶች የ12ኛ ክፍል ሞዴል ፈተናዎች"ኤም፣ኤ.ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)።

ካሣዬ ዓለሙ (1992) "በአዲስ አበባ መስተዳድር የአየር ጤና ክፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ1989-1991 ዓ.ም. ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች አቀራረብ ግምገማ" ኤም፣ኤ.ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)።

ጠጅቱ በሬቻ (1999)፣ በአዲስ አበባ ከተማ በግልና በመንግስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የአሥርኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አገር አቀፍ ፈተና ውጤቶች ንፅፅር" ለ(TeAm) ኤም፣ኤ.ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)።

ንጉሴ ደአታ (1978) "የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና አቀራረብና የመማሪያ መፅሀፍ ዝምድና"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ዲማፅ (ያልታተመ)።

ንጉሴ ጥላሁን (1989) "በሀረር ከተማ በሚገኙ ሁለት ከፍተኛ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ1987 ዓ.ም የተሰጡ የአማርኛ ፈተና ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ ግምገማ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ዲማፅ (ያልታተመ)።

ዐጋዬ ግርማ (1997) "1995 እና በ1996 ዓ.ም ለአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል መምህራን ስልጠና የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ የሴሚስተር ማጠቃለያ ፈተናዎች ግምገማ በተመረጡ የአማራ ክልል መምህራን ትምህርት ኮሌጆች መነሻነት" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። ለኤም.ኤ.ደግሪ. ማሟያ የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)

Alderson, J. C. Clapham, C. and Wall, D. (1995*). Language Test Construction and Evaluation.* Cambridge: Cambrige Universitv Press.

Bachman, (Yle F. (1990). *Fundamental Considerations in Language Testing*. Oxford: Oxford University Press.

Baker, D. (1989). *Lanaguage testing: a critical survvey and practical Guide.* London: Eduward Arnold.

Brown, J. D. (196). *Testing in Language Programs*. New Jersey: Prentice Hall Regent.

Carter, V. Good (1973). *Dictionary of Education*. Sanfracisco: Mcgraw-Hill Book Company.

Davies, A. (1968). *Langauge Testing Symposium*. London oxford university Press.

Dubin, F and Olshtain, E. (1986). *Course Design. Develioping Programs and Learning*. New York: Cambridge University Press.

Feldman, R.S. (1994). *Essentials of Understanding Phychology*. 2nd ed. New York: McGraw-Hill-Inc.

Harmer, J. (1991). *The Practice of English Language Teaching*. Longman Group.

Harrison, Andrew (1983). *A Language Testing Hand Book*. London: Macmillan Publisher.

Heaton, J. B. (1975). *Writing English Language Tests*. Singapor: Longman Limited.

Hughes, A (ed). (1989). *Testing Langauge Teachers*. Cambridge: Cambridge University Press.

Lado R. (1961). *Language Testing*. LTD. London New York.

Madsen, H. S. (1983). *Teachniques in Testing*. New York: oxford university Press.

Nunan D. (1994). *Teaching and Reading Foreign Language*. London: Clays Ltd.

Richards, J.C. (1990). *The language Teaching Matrix*. Cambridge: Cambridge unviersity press.

Richards, J.C. and T.S. Rodgers (1986). Aproaches and Methods in Language Teaching: A Description and Analysis. Cambridge: Cambridge University press.

Rivers, W.M. (1968). *Teaching foreign Language skills*. Chicago: university of Chicago Press.

Weir, C. J. (1993). *Understanding and Developing Test*. London: Prentice Hall.

አባሪ አንድ

1 የመከላከያ ሰራዊት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና መጋቢት 2001 ዓ.ም 1

የጥያቄ ብዛት:- 60 የተፈቀደው ጊዜ:- 60 ደቂቃ

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 1 እስከ 16 ድረስ የተለያዩ ሰዋስው ነክ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጭ/ምረጥ::

1. የሚከተሉት ቃላት በአማርኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት ውስጥ የሚደረደሩበትን ትክክለኛውን ስርአት የሚያመለክተው የትኛው አማራጭ ነው?

ሾካካ፣ ምሽግ፣ ሾርባ፣ ትርፍ፣ ምሬት

A. ምሽግ፣ ምሬት፣ ሾካካ፣ ሾርባ፣ ትርፍ
B. ሾርባ፣ ሾካካ፣ ትርፍ፣ ምሬት፣ ምሽግ
C. ምሬት፣ ምሽግ፣ ሾርባ፣ ሾካካ፣ ትርፍ
D. ትርፍ፣ ሾካካ፣ ሾርባ፣ ምሽግ፣ ምሬት

2. "አበበ ያበደርኩትን መጽሃፍ ትናንት መለሰልኝ::" የሚለው አረፍተ ነገር ተሳቢ የትኛው ነው?

A. አበበ
B. መጽሃፍ
C. ትናንት
D. ተሳቢ የለውም

3. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል አንዱ የግስ ገላጭ የለውም::

A. ጀግናው ሠራዊታችን የሞቀ አቀባበል ተደርገለት::
B. ወታደር መሃመድ ወደ አዲስ አበባ ሄደ::
C. አለሚቱ ከትምህርት ቤት መጣች::
D. ምልምል ወታደሮቹ ተመረቁ::

4. "የክፍለ ጦሩ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች አዳዲስ ልቦለድ መጻህፍት ተገዙላቸው::" በሚለው አረፍተ ነገር በተሰመረበት ቃል ውስጥ በስተመድረሻ ያለው ቅጥያ ተግባር ምንድን ነው?

A. ብዛትን ማመልከት
B. ፆታን ማመልከት
C. ተሳቢን ማመልከት
D. ባለቤትን ማመልከት

1 1

5. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ቅጥያ የሌለው የትኛው ነው?

A. እንግሊዛዊ
B. ስእል
C. እርሳሶቹ
D. መርዛማ

6. አንቺ ብለን በረበርሽ ካልን፣ እኛ ብለን _____ እንላለን።

A. በረበርን
B. በረበሩ
C. በረበረች
D. በረበራችሁ

7. "ደረመሰ" ከሚለው ቃል ያልተመሠረተው የትኛው ቃል ነው?

A. መደረማመስ
B. መደርመስ
C. ተደመሰሰ
D. ተደረመሰ

8. ከሚከተሉት ቃላት መካከል አንዱ ጠብቆና ላልቶ የሚነበብ ሆሄ ስለሌለው ሁለት ፍቺ አይኖረውም።

A. መናጥ
B. አባይ
C. ገና
D. ቡና

9. "ወታደር አስጨናቂ በኢላማ ተኩስ አንደኛ ስለወጣ ተሸለመ።" የሚለው አረፍተ ነገር ባለቤት የትኛው ነው?

A. ወታደር
B. ወታደር አስጨናቂ
C. ተኩስ
D. ኢላማ ተኩስ

10. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል አንዱ የስም ገላጭ የለውም።

A. የሰፈሩ ልጆች ሜዳው ላይ ኳስ ይጫወታሉ።
B. የዘንድሮው አዝመራ ሲያዩት ያጠግባል።
C. ጀግናው ሠራዊታችን ግዳጁን ለመወጣት ዝግጁ ነው።
D. ሠራዊቱ አዝመራውን ሲሰበሰብ ዋለ።

1 1

11. ከሚከተሉት ውስጥ ለሃተታዊ አረፍተ ነገር ምሳሌ የሚሆነው የትኛው ነው?

A. አትክልት ለጤና ጠቃሚነቱ አያጠያይቅም።
B. ቫይታሚን ዲ ለምን ይጠቅማል?
C. አንተ ልጅ ያንን መጽሃፍ አቀብለኝ!
D. እፎይ! ያሰብኩት ሆነ!

12. ከሚከተሉት ቃላት መካከል የአንዱ ቅጥያ የተሰየ ነው።

A. ከነከናት
B. ወሰዳት
C. ደግነት
D. መረቃት

13. ከሚከተሉት ሃረጎች መካከል ገላጭና ተገላጭ የሌለው የትኛው ነው?

A. ረጅሙ ጓደኛዬ
B. ደጉ ሰው
C. ቀዩ በሬ
D. ትምህርቱ ገባው

14. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል ከስህተት ነፃ የሆነው የትኛው ነው?

A. እነሱ ከውጭ አገር ነገ ትመጣለች።
B. የቤት እንስሳ መንከባከብ እንወዳለን።
C. አህያዋ በመኪና ተገጭተው ሞቱ።
D. እነሱሌማን ምሳውን አልበላም።

15. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል በሚያስተላልፈው መልዕክት የሚለየው _____ ነው።

A. ሱሰኝነት ከረሃብተኝነት ይበልጣል።
B. ከረሃብተኝነት ሱሰኝነት ይበልጣል።
C. ረሃብተኝነትን ሱሰኝነት ይበልጣል።
D. ሱሰኝነትን ረሃብተኝነት ይበልጣል።

1 1

16. "ወታደር ሙስጠፋ በሚቀጥለው አመት የማእረግ እድገት _____::" ለአረፍተ ነገሩ መልእክት ተገቢ የሚሆነው መቋጪያ የትኛው ነው?

A. አግኝቷል
B. አግኝቶ ነበር
C. ያገኛል
D. ሊያገኝ ችሏል

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 17 እስከ 25 ድረስ የተለያዩ ቃላት ነክ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ::

17. "የአደገኛ እፆች ተጠቃሚ መሆን ከሚያስከትላቸው ጉዳቶች መካከል አንዱ አእምሮን _____ ነው::" በሚለው ከአረፍተ ነገሩ መልእክት አኳያ ለባዶ ቦታው ተገቢ የሚሆነው የትኛው አማራጭ ነው?

A. ማስደሰቱ
B. ማስላቱ
C. ማበልፀጉ
D. ማነሁለሉ

18. "ከበደ ዙሪያ ገባው ወዳጁ ስለሆነ፣ በጀመረው የንግድ ስራ ውጤታማ እንደሚሆን ከወዲሁ ተገምቷል::" የሚለው የከበደ ወዳጅ _____ መሆኑን ያመለክታል::

A. ጥቂት
B. አያሌ
C. እፍኝ የማይሞላ
D. እጅግ አነስተኛ

19. ከሚከተሉት ቃላት መካከል አንዱ በሚሰጠው ፍቺ ይለያል::

A. ረብ
B. ጥቅም
C. ግምት
D. ፋይዳ

20. "ሰሞኑን በነበረባት የስራ ውጥረት የተነሳ እህታችን <u>አይኗ ብር ብሏል</u>::" የተሰመረበት ፈሊጥ ፍቺ የትኛው ነው?

A. ደንግጣለች
B. ከስታለች
C. ፈዛለች
D. ደንዝዛለች

1 1

21. "ከበደ <u>ሲያዝሉት ይነጭ</u> አይነት ሰው በመሆኑ በሰፈሩ ሰው ያለው ተወዳጅነት እስከዚህም ነው::" በሚለው አረፍተ ነገር ከበደ ምን አይነት ሰው ነው?

A. በቅናት የተቃጠለ
B. የሚረዱትን የሚጎዳ
C. እርዳታ የሚሻ
D. በድጋፍ ለመኖር የሚሻ

22. ከሚከተሉት የስያሜ ቃላት መካከል አንዱ በአመዳደቡ ይለያል::

A. ሹካ
B. ጋሻ
C. መድፍ
D. ሳንጃ

23. ዘረፈ ብለን መነተፈ ካልን፣ ቀጠፈ ብለን _____ እንላለን::

A. ዋሸ
B. መነቸከ
C. መሰከረ
D. ወላወለ

24. "ወተት ቅቤ እንዲወጣው _____::" አረፍተ ነገሩ ተገቢ መልእክት እንዲያስተላልፍ ተመራጭ የሚሆነው የትኛው ቃል ነው?

A. ይወዘወዛል
B. ይርገፈገፋል
C. ይናጣል
D. ይንቀሳቀሳል

25. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል አንዱ በአገላለጹ ተቀባይነት አለው::

A. ዶሮዋ ጫጩት ወለደች::
B. እባብ ተናካሽ የሆነ ተሳቢ አውሬ ነው::
C. የጎረቤታችን ውሻ ኮሽታ በተሰማ ቁጥር ሌሊቱን ሲያስካካ ያድራል::
D. አይጦች ሲጥ ሲጥ እያሉ የሚያሰሙት ድምጽ እንቅልፍ ይነሳል::

1 1

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 26 እስከ 33 የተለያዩ ጽሁፍ ነክ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ለየጥያቄዎቹ ትክክል የሆኑትን መልሶች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጭ/ምረጥ::

26. "ጉንፋን የእድሜ ባለፀጋ ከሆኑት ይልቅ በታችኛው የእድሜ ክልል ላይ ያሉትን በብዛት የሚያጠቃ በሽታ ነው::" ይህ አረፍተ ነገር በሌላ አባባል ሲጻፍ ትክክል የሚሆነው የትኛው ነው?

A. ጉንፋን እድሜ ሳይለይ ሁሉንም ሰው የሚያጠቃ በሽታ ነው::
B. ጉንፋን እከሌ ከእከሌ ሳይባል ሁሉንም ሰው የሚያጠቃ በሽታ በመሆኑ ይታወቃል::
C. በየትኛውም የእድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎች በጉንፋን በሽታ በብዛት ይጠቃሉ::
D. የጉንፋን በሽታ በብዛት የሚያጠቃው የእድሜ ባለፀጋ ያልሆኑትን ሰዎች ነው::

27. ተዘበራርቀው የተጻፉት የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች አንድ አንቀጽ የሚመሠርቱበትን ቅደም ተከተል የሚያመለክተው በየትኛው አማራጭ የቀረበው ነው?

ሀ. ሆኖም ግን አብዛኞቹ እባቦች መርዛማ አይደሉም::
ለ. በተለይም ደንና ረጃጅም ሳር በሚበዛባቸው አካባቢዎች ብዙ የእባብ ዝርያዎች ይገኛሉ::
ሐ. እንደሚታወቀው በአለም ላይ ብዙ አይነት የእባብ ዝርያዎች አሉ::
መ. በአለም ላይ ከሚገኙ ከ3000 በላይ ዝርያዎች ውስጥ 15% ብቻ መርዛማና ተናዳፊ ናቸው::

A. መ፣ ሐ፣ ለ፣ ሀ
B. ሐ፣ ለ፣ ሀ፣ መ
C. መ፣ ለ፣ ሀ፣ ሐ
D. ሐ፣ ሀ፣ መ፣ ለ

28. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የአንድ ግለሰብ የህይወት ታሪክ ሲጻፍ መጀመሪያ መገለጽ ያለበት የትኛው ነው?


A. የግለሰቡ የትውልድ ቦታና ዘመን
B. ግለሰቡ ከዚህ አለም በሞት ከተለየ፣ የተለየበት ጊዜ
C. ግለሰቡ በህይወት ዘመኑ ያበረከተው አስተዋፅኦ
D. የግለሰቡ አስተዳደግና የትምህርት ደረጃ

1 1

29. የሴት ወታደር ትርሃስ በክፍለ ጦሯ አንድ ኮሚቴ ውስጥ በጸሃፊነት ስታገለግል፣የኮሚቴውን ስብሰባዎች ሂደት በተመለከተ በሃላፊነት የምታዘጋጀው ሰነድ ምን ይሆናል?

A. የስብሰባው ሂደት ዘገባ
B. የስብሰባው ሂደት ቃለ ጉባዔ
C. የስብሰባው ሂደት ማስታወሻ
D. የስብሰባው ሂደት አመልካች ደብዳቤ

30. የሚከተለው የደብዳቤ ቅርጽ ለየትኛው የደብዳቤ አይነት ተገቢ ነው?



A. ለማመልከቻ
B. ለወዳጅ
C. ለመስሪያ ቤት
D. ለማስታወሻ

31. ከዚህ በላይ በቀረበው ደብዳቤ ተራ ቁጥር "3" ላይ የሚጻፈው ምንድን ነው?

A. ቀን
B. የደብዳቤው ጉዳይ
C. መግቢያ
D. የተቀባይ አድራሻ

1 1

32. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል በመንስኤና ውጤት ግንኙነት ላይ ተመስርቶ የተጻፈው የትኛው ነው?

A. ልቅ የግብረስጋ ግንኙነት ሰዎችን ለኤችአይቪ ከሚያጋልጡ ጉዳዮች መካከል ዋናው ነው::
B. የክረምቱ ዝናብ በአብዛኛዎቹ የሃገሪቱ አካባቢዎች መደበኛ ፈሩን ተከትሎ እንደሚዘንብ ተገለፀ::
C. የጉንፋን ቫይረስ ህይወት ካላቸው ነገሮች ውጭ በህይወት ሊቆይ አይችልም::
D. ስትሮክ ድንገተኛ ራስ ምታትና አካላዊ ዝለትን የሚስከተልና ለሞት ሊዳርግ የሚችል በሽታ ነው::

33. "ከተሞች አካባቢ ያሉ ሰዎች ጠዋት ወደ ስራ ለመጓዝ ታክሲ፣ ሎንቺን፣ አውቶቡስ _____ የግል ተሽከርካሪ መጠቀማቸው የግድ ነው::" በሚለው ለባዶ ቦታው ተገቢ <u>የማይሆነው</u> አያያዥ የትኛው ነው?

A. አሊያም
B. እንዲሁም
C. እና
D. ነገር ግን

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 34 እስከ 37 ድረስ ስርአተ ነጥብን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: በአጠያየቃቸው መሠረት ለየጥያቄዎቹ ትክክል የሆኑትን መልሶች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጥ/ምረጭ::

34. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል በትእምርተ ጥቅስ አጠቃቀሙ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

A. "አስተማሪያችን" በርቱና አጥኑ ብለው መከሩን::
B. አስተማሪያችን "በርቱና አጥኑ!" ብለው መከሩን::
C. "አስተማሪያችን በርቱና አጥኑ!" ብለው መከሩን::
D. አስተማሪያችን "በርቱና አጥኑ ብለው መከሩን::"

35. "ደመናው ከብዷል _____ በኋላ የሚዘንብ ይመስላል::" በሚለው አረፍተ ነገር ለባዶ ቦታው ተገቢ የሆነው የትኛው ስርአተ ነጥብ ነው?

A. ትምህርተ አንክሮ (!)
B. ድርብ ሠረዝ(፤)
C. ነጠላ ሰረዝ(፣)
D. ስርአተ ነጥብ አያስፈልገውም

1 1

36. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል አንዱ የነጠላ ሠረዝ አጠቃቀሙ ትክክል ነው::

A. ህፃናት የተመጣጠነ ምግብ፣ ንፁህ ልብስና ትምህርት ማግኘት አለባቸው::
B. ህፃናት፣ የተመጣጠነ ምግብ፣ ንፁህ ልብስና ትምህርት፣ ማግኘት አለባቸው::
C. ህፃናት የተመጣጠነ ምግብ፣ ንፁህ ልብስና፣ ትምህርት፣ ማግኘት አለባቸው::
D. ህፃናት የተመጣጠነ፣ ምግብ፣ ንፁህ፣ ልብስና ትምህርት ማግኘት አለባቸው::

37. የትምህርተ አንክሮ ምልክት <u>የማያስፈልገው</u> የትኛው አረፍተ ነገር ነው?

A. እንኳን ደህና መጡ!
B. እንደምን አረፈዱ!
C. መምህር አጥፍቻለሁ ይቅር ይበሉኝ!
D. መኪና የመጓጓዣ አይነት ከሆኑት መካከል አንዱ ነው!

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 38 እስከ 45 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች የሚከተለውን ምንባብ *መሠረት* አድርገው የቀረቡ ናቸው:: ለጥያቄዎቹ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጭ/ምረጥ::

1 አንድ ሀገር በኢኮኖሚ እንድትበለጽግ ከተፈለገ አመለካከቱ የዳበረ፣ በተጨባጭ ምክንያትና ውጤት የሚያምንና ለለውጥ ዝግጁ የሆነ ማህበረሰብ ያስፈልጋታል:: ይህን ለማድረግ ደግሞ የንባብ ባህልን ማዳበርና ለንባብ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል:: በትምህርት ቤት የሚሰጠውን ትምህርት ለማበልጸግ፣ ለቀሪው ህብረተሰብ የሚታወቅ ለውጥ ለማምጣት፣ በየሙያ ወይም በየትምህርቱ ዘርፍ የተለያዩ ጽሁፎችን ለንባብ ዝግጁ ማድረግ ወሳኝነት አለው::

2 በሀገራችን በዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ላይ ባሉትም ሆነ በከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ላይ በደረሱት ወገኖች ዘንድ ያለው የንባብ ልምድ የበለጸገ ነው ለማለት አይቻልም:: በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደሩት ከእለት ጉርስ ተርፎ ለመጻህፍት መግዣ የሚሆን ገንዘብ አይኖራቸውም:: ከፍተኛ ገቢ ያላቸውም ቢሆኑ፣ የሃብት ደረጃቸውን የሚያሳድጉበትን የቅንጦት እቃ ከመግዛት ያለፈ ልምድ አላዳበሩም::

3 ለውጥ ማምጣት የሚያስችል እውቀት ለማከማቸት ንባብን ልምድ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ሆኖም የንባብ ባህል ድንገት የሚፈጠር ሳይሆን ቀስ በቀስ የሚዳብር ነው:: የማህበረሰቡን ልምድ ለማዳበር በጣም ተከታታይ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል:: የንባብ ባህልን ለማዳበር ከልጅነት አንስቶ እንቅስቃሴ መካሄድ

1 1

ይኖርበታል። ለዚህም የቤተሰብ ኃላፊነት ከበድ ብሎ ይታያል። ለልጆች መጫወቻዎችን ብቻ ሳይሆን መጻህፍትን ገዝቶ በስጦታ መልክ ማበርከት፣ እንዲሁም በመጻህፍት የሚቀረቡ ታሪኮችን ለልጆች ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ፣ ልጆች የመጻህፍት ንባብ ፍቅር እንዲያድርባቸው ይረዳል። በተቻለ መጠን በትርፍ ጊዜ አንባቢ ሆኖ መገኘትም፣ ልጆች ንባብ መልካም ልምድ መሆኑን እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል።

4 ይህ እንግዲህ ከቤተሰብ የሚጠበቅ ተግባር ሲሆን፣ ከመንግሥትና ከማህበረሰቡ የሚጠበቅ ሃላፊነትም ይኖራል። መጻህፍትን ማቅረብ ብሎም በየአካባቢው አነስተኛ ቤተ መጻህፍትን መገንባት ያሻል። ማህበረሰቡ ልጆቹ በአካባቢያቸው ቤተ መጻህፍት እንዲያገኙ የተቻለውን ጥረት ማድረግ፣ መንግሥትም እንደሌሎቹ ማህበራዊ ተቋማት ሁሉ ለቤተመጻህፍት ግንባታም ትኩረት ሊሰጥ ይገባል። ከሁሉ በላይ ደግሞ፣ ህብረተሰቡ አንባቢና ቤተመጻህፍቱ የሚያቀርቡት በረከት ተጠቃሚ እንዲሆን አጠቃላይ ርብርብ ማድረግ ያስፈልጋል።

ምንጭ፡- አዲስ ዘመን ጋዜጣ፡ መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም

38. የንባብ ባህልን በማዳበር ረገድ ከመንግስት የሚጠበቀው ዋና ተግባር ምንድን ነው?

A. ልጆች መጻህፍት አንባቢ እንዲሆኑ መቀስቀስ
B. ወላጆች ለልጆቻቸው መጻህፍት እንዲገዙ ማበረታታት
C. ቤተ መጻህፍት በየአካባቢው እንዲገነቡ ትኩረት መስጠት
D. በትምህርት ቤቶች በኩል ልጆች የሚያነቧቸው መጻህፍት እንዲገኙ ማድረግ

39. የልጆች የንባብ ባህል እንዲዳብር በወላጆች ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል ጠቀሜታ <u>የሌለው</u> የትኛው ነው?

A. ልጆች መጻህፍት አንባቢ እንዲሆኑ በየእለቱ መጨቅጨቅ
B. እንደልጆች መጫወቻዎች ሁሉ፣ መጻህፍትን በስጦታ መልክ ማቅረብ
C. በመጻህፍት ውስጥ ያሉ ታሪኮችን ድምፅን ከፍ አድርጎ ማንበብ
D. በሚያገኙት ትርፍ ጊዜ ሁሉ አንባቢ በመሆን አርአያነትን ማሳየት

40. የሁለተኛው አንቀጽ መንደርደሪያ ሃሳብ የሚገኘው በየትኛው አረፍተ ነገር ነው?

A. በመጀመሪያው
B. በሁለተኛው
C. በሦስተኛው
D. አንቀጹ መንደርደሪያ ሃሳብ የለውም

1 1

41. ለንባብ ባህል አለመዳበር እንደ ዋና መንስዔ ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው የትኛው ነው?

A. ለንባብ ባህል መዳበር መንግሥት የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆን
B. የወላጆች አንባቢ አለመሆን ባህሉን ወደ ልጆች በማስተላለፍ ረገድ ተፅእኖ የሚያደርግ መሆኑ
C. ለንባብ ባህል መዳበር አስተዋፅኦ ያላቸው አካላት ለባህሉ መዳበር የሚያደርጉት ርብርብ ዝቅተኛ መሆኑ
D. የአንዳንድ ወላጆች የኢኮኖሚ ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑ መጻህፍት ለመግዛት የማያስችል መሆኑ

42. የምንባቡን ይዘት በሚገባ የሚያንፀባርቀው የትኛው ርእስ ነው?

A. የንባብ ባህልን ለማዳበር ሁሉም ይረባረብ
B. ለንባብ ባህል መዳበር የቤተመጻህፍት አስተዋፅኦ
C. የንባብ ባህልን ለማዳበር የወላጆች ሚና
D. ለንባብ ባህል መዳበር መከናወን ያለባቸው ተግባራት

43. ከሚከተሉት ሃሳቦች መካከል የምንባቡ <u>ዝርዝር ሃሳብ</u> ተደርጎ የሚወሰደው የትኛው ነው?

A. የንባብ ባህልን ለማዳበር እከሌ ከእከሌ ሳይባል ርብርብ ማድረግ አለበት::
B. ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ወገኖች መጻህፍት ከመግዛት ይልቅ የቅንጦት እቃ በመግዛት የሃብት ደረጃቸውን ለማሳየት ይጥራሉ
C. የንባብ ባህልን ለማዳበር የሚደረገው እንቅስቃሴ ከልጅነት ጀምሮ መከናወን አለበት::
D. በየአካባቢው ቤተመጻህፍት እንዲገነቡ ማድረግ ለንባብ ባህል መዳበር አስተዋፅኦ ይኖረዋል::

44. ምንባቡ ለየትኛው የድርሰት አይነት ምሳሌ ይሆናል?

A. ተራኪ
B. አመዛዛኝ
C. ገላጭ
D. ስእላዊ

1 1

45. የምንባቡ ዋና መልእክት ምንድን ነው?

A. በተለያየ የትምህርት ደረጃ ላይ ባሉ ወገኖች ጭምር የንባብ ባህል ዝቅተኛ መሆኑን መግለጽ
B. የንባብ ባህልን ለማሳደግ ቤተሰብ የልጆችን የንባብ ባህል በማሳደግ ረገድ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ተግባራትን መዘርዘር
C. የንባብ ባህል እንዲዳብር የተለያዩ ወገኖች የየራሳቸው አስተዋፅኦ ያላቸው መሆኑን ማስገንዘብ
D. የልጆች የንባብ ባህል እንዲዳብር ቤተመጻህፍትን በየአካባቢው ለማስፋፋቱ ተግባር ትኩረት መስጠት እንደሚያሻ መጠቆም

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 46 እስከ 51 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች በሚከተለው ግጥም ላይ የተመሰረቱ ናቸው:: ጥያቄዎቹን በጥሞና በማንበብ ትክክል የሆኑትን መልሶች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጥ/ምረጭ::

ታላላቅ ሃገሮች ዛሬ የሚታዩት
በመስራት ብቻ ነው ለዚህ የበቁት::
እኛም ብንጠነክር ብንሰራ እንደነሱ
ችግራችን ሁሉ አይቀር መደምሰሱ::
ቡዳ ነች ጠይብ ነው ማለቱን ትተን
እንውጣ ለስራ ሁላችን አብረን::
እንዲህ ያለው ስህተት በፊትም ቢሰራ
ዛሬ ለማኖሪያ ፍፁም የለም ስፍራ::
በእንዲህ ያለ መንፈስ እንደተጎዳን
አወቅነው ሁላችን እንግዲህ በቃን
በጊዜው ሞሻሻል በርምጃ ተውጦ
በጥበቡ መጎልመስ ባህሉ ተለውጦ::
በነመሰናክል በእንቅፋት አጊጦ
ቀረ በዘልማድ መኖር አንፈራጦ::

ምንጭ:- "ይ" ነማሶ ተገኝ "ቢ" ፊደል ተውጦ

46. ታላላቅ ሃገሮች ዛሬ ለደረሱበት ደረጃ ሊበቁ የቻሉበት ዋና ምክንያት _____ ነው::

A. "ቡዳ ነች" "ጠይብ ነች" መባባልን ማስወገዳቸው
B. ዘልማዳዊ አኗኗርን ማስቀረታቸው
C. በጥበብ አማካይነት ጎታች ባህሎችን ማሻሻላቸው
D. ጠንክረው በመስራት የገጠማቸውን ችግር ማስወገድ መቻላቸው

1 1

47. በግጥሙ በሳብዕ ሆሄ የጨረሱ ስንት ስንኞች ናቸው?

A. ሁለት
B. ሦስት
C. አራት
D. አምስት

48. "በነመሰናክል በእንቅፋት አጊጦ" የተባለው ምንድን ነው?

A. ችግር
B. ጠይብነት
C. ዘልማዳዊ አኗኗር
D. ጥበብ

49. ግጥሙ ስንት ስንኞች አሉት?

A. 6
B. 8
C. 12
D. 14

50. ግጥሙ የሚያስተላልፈው መልእክት ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

A. ችግራችን ሊወገድ የሚችለው እንደ ታላላቅ ሃገሮች ተባብሮ በመስራት ነው::
B. "ቡዳ ነች" "ጠይብ ነች" በማለት ስራን አንናቅ
C. በእድገት የተራመዱት ሃገሮች ላይ እንዳንደርስ የሚያደርገን ችግራችን ነው
D. በዘልማድ መኖር እንቅፋት ነውና ይወገድ

51. ለግጥሙ ተስማሚ ሊሆን የሚችለው ርእስ የትኛው ነው?

A. ችግራችን ይደምስስ
B. ጥበብ ይጎልምስ
C. ጠንክረን እንስራ
D. ከጊዜው ጋር እንራመድ

1 1

መመሪያ:- ከጥያቄ 52 እስከ 60 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በአጠያየቃቸው መሠረት ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆኑትን መልሶች ምረጭ/ምረጥ።

52. ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች መካከል በአሁኑ ወቅት ተቀባይነት የማይኖረው የትኛው ነው?

A. ከሴት መምከር፣ ደግሶ መስከር
B. ሴትን ያመነ፣ ጉም የዘገነ
C. ከሴት ነገር፣ ከበቅሎ መደንበር አይታጣም
D. ሁሉም ምሳሌያዊ አነጋገሮች ተቀባይነት የላቸውም

53. ከሚከተሉት ስያሜዎች መካከል ለኢልብወለድ ድርሰት ምሳሌ የሚሆነው የትኛው ነው?

A. ረጅም ልቦለድ
B. ግጥም
C. መዝገበ ቃላት
D. ተውኔት

54. በልቦለድ ድርሰት ውስጥ የገሃዱን አለም ሰዎች አምሳያ ሆነው የምናገኛቸው ሰዎች በስነጽሁፍ ስያሜያቸው ምን ይባላሉ?

A. ተዋንያን
B. ደራሲያን
C. ገጸባህርያት
D. ተራኪዎች

55. መጻህፍት ተውሶ ለማንበብ ወደ ቤተ መጻህፍት ለሚሄድ ሰው ጠቃሚ የሆነው ልምድ የትኛው ነው?

A. ማስታወሻ መያዝ እንዲቻል አስፈላጊ የጽህፈት መሣሪያዎችን ይዞ መገኘት።
B. በንባብ የሚገኙ ቁም ነገሮችን ማስታወስ እንዲቻል ቁምነገሮቹን በእርሳስ ወይም በስክሪብቶ ምልክት ማድረግ።
C. በሚያነቡት መጽሃፍ ዙሪያ ቤተ መጻህፍት ውስጥ ከጓደኛ ጋር መወያየት።
D. በንባብ የሚገኙ ተፈላጊ ቁምነገሮችን በማስታወሻ መያዝ እንዲቻል ቁምነገሮቹ የሚገኙባቸውን ገጾች በማጠፍ ምልክት ማድረግ።

56. "ከአያያዝ ይቀደዳል፣ከአነጋገር _____።" ለጅምር ምሳሌያዊ አነጋገሩ መቋጪያነት ትክክል የሚሆነው የትኛው አማራጭ ነው?

A. ይፈረዳል
B. ይጠፋል
C. ይቀሰማል
D. ይሰወራል

1 1

57. ከሚከተሉት ውስጥ በፍጥነት ንባብ ወቅት ተገቢ የሆነው ልምድ የትኛው ነው?

A. የሚያነቡትን ጽሁፍ በጣት እየጠቆሙ ማንበብ
B. ከንፈርን እያነቃነቁ ድምጽ በማሰማት ማንበብ
C. ቃላትን እየቆጠሩ ማንበብ
D. የሚያነቡትን ጽሁፍ አለማ በቅድሚያ ለመገመት መሞከር

58. ከአንድ የውይይት ተሳታፊ ከሆነ ሰው የሚጠበቀው ተገቢ ተግባር የትኛው ነው?

A. የሚያዳምጡትን ንግግር ዋናና ዝርዝር ሃሳቦች በሙሉ ለመለየት መሞከር
B. የአንዳንድ ሰዎች ንግግር ለወይይቱ ጠቃሚ እስካልሆነ ድረስ ከማጥላላትና ከማንኳሰስ አለመታቀብ::
C. አስተያየት መስጠት እንዲቻል ከተለያዩ ተናጋሪዎች የሚቀርቡ ሃሳቦችን በማስታወሻ ለመያዝ መሞከር
D. በውይይቱ ንግግር የሚያደርጉ ሰዎች የሚያቀርቡት ሃሳብ ስህተት ካለበት፣ ወዲያውኑ ንግግራቸውን በማቋረጥ ልክ አለመሆናቸውን በማንቋሸሽ ጭምር መግለጽ

59. "አለባብሰው ቢያርሱ፣ ባረም ይመለሱ::" የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ስራን በተመለከተ ምን ያስገነዝባል?

A. ስራን እንዳያዳግም አድርጎ መስራት እንደሚገባ
B. ስራን መናቅ እንደማይገባ
C. ስራን በወቅቱ አጠናቆ ማቅረብ ጠቃሚ መሆኑን
D. ስራን ከአቅም ጋር ማመጣጠን እንደሚጠቅም

60. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል እርግጠኝነትን የሚያመለክተው የትኛው ነው?

A. ወታደር ብርቅነህ ዘንድሮ ከስምንተኛ ክፍል ወደ ዘጠነኛ ክፍል በጥሩ ውጤት ያልፋል ተባለ::
B. ወታደር ብርቅነህ ወደር የሌለው ጀግና በመባል ልዩ ሽልማት አገኘ::
C. ወታደር ብርቅነህ ከረጅም ጊዜ የፍቅር ጓደኛው ጋር በትዳር ለመጣመር እያሰበ ነው::
D. ወታደር ብርቅነህ ሶስተኛ የመንጃ ፈቃድ ለማውጣት አቅዷል::

አባሪ ሁለት

1 የ2002 ዓ.ም የመከላከያ ሠራዊት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና 1

የጥያቄ ብዛት:- 60 የተፈቀደው ጊዜ:- 60 ደቂቃ

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 1 እስከ 9 ድረስ ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጭ/ምረጥ::

1. "የአቶ ተሰማ ልጅ <u>ቆርጦ ቀጥል</u> ስለሆነ በሰፈሩ ሰው የተጠላ ነው::" በሚለው የተሰመረበት ሃረግ የአቶ ተሰማ ልጅ _____ መሆኑን ያመለክታል::

A. አባይ
B. ቀጣይ
C. ጠጋኝ
D. ነገረኛ

2. ከጥንድ ቃላቱ መካከል አንዱ ቃል ለሌላው ቃል ተቃራኒ በመሆን የቀረበው በየትኛው አማራጭ ነው?

A. ሸር – ተንኮል
B. ሐቅ – እውነት
C. አጋማሽ – እኩሌታ
D. አዛውንት – ወጣት

3. ከጥንድ ቃላቱ መካከል አንዱ ቃል ለሌላው ቃል ተመሳሳይ በመሆን የቀረበው በየትኛው አማራጭ ነው?

A. ወደደ – ጠላ
B. ጨቅላ – ህፃን
C. ጉዳት – ጥቅም
D. ሩቅ – ቅርብ

4. ኮኖ "አስካለችና ዘይነባ ቋንቋ ለቋንቋ ስለሚግባቡ የተሰጣቸውን ስራ በአፋጣኝ ይጨርሳሉ::" የሚለው አረፍተ ነገር እነአስካለች ምን መሆናቸውን ያመለክታል?

A. ነገረኛ መሆናቸውን
B. ንግግር አዋቂ መሆናቸውን
C. ሃሳብ ለሃሳብ የሚግባቡ መሆናቸውን
D. የማይጣጣሙ መሆናቸውን

1 1

5. "ስንቅህ <u>የወጣለት</u> ስራ ሰርቶ በማቅረቡ ተመሰገነ::" የሚለው አረፍተ ነገር የስንቅህ ስራ ምን መሆኑን ያመለክታል?

A. የተሳካ መሆኑን
B. አስቸጋሪ መሆኑን
C. አሰልቺ መሆኑን
D. አድካሚ መሆኑን

6. "ወታደር መሃመድ የፈቃድ ጥያቄው ተቀባይነት ማግኘቱን ካወቀ ወዲህ ልቡ ቆሟል:: " ከሚለው አረፍተ ነገር ምን እንረዳለን?

A. የወታደር መሃመድን መቸኮል
B. የወታደር መሃመድን መታመም
C. የወታደር መሃመድን መደንገጥ
D. የወታደር መሃመድን መደሰት

7. "ተማሪዎች እራሳቸውን <u>ካልባሌ</u> ስፍራ በማራቅ ለትምህርታቸው መትጋት አለባቸው::" በሚለው የተሰመረበትን ቃል ሊተካ የሚችለው የትኛው ነው?

A. ከመጥፎ
B. ከማይረባ
C. ከጎጂ
D. ሁሉም መልስ ይሆናል::

8. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል አንዱ በአገልግሎቱ ይለያል::

A. ትምህርት ቤት
B. ጎጆ
C. በረት
D. ጉረኖ

9. "ወሰደ" ከሚለው ቃል ጋር በፍቺ የማይዛመደው የትኛው ቃል ነው?

A. ተረከበ
B. ተቀበለ
C. ሰረቀ
D. ከመረ

1 1

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 10 እስከ 20 ድረስ ለዋስውን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ::

10. ከሚከተሉት መካከል አረፍተ ነገር በመሆኑ የተሟላ ሃሳብ የሚሰጠው የትኛው ነው?

A. የሃምሳ ሳንቲም ዳቦ::
B. ረጅም ቀንድ ያለው በሬ::
C. ትንሹ ልጅ መጣ::
D. ለእውነት የቆመ ሰው::

11. ከአረፍተ ነገሮቹ መካከል በቃላት አጠቃቀሙ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

A. ትናንት የፈሰሰው ዝናብ ከባድ ጎርፍ አስከተለ::
B. ትናንት የጣለው ዝናብ ከባድ ጎርፍ አስከተለ::
C. ትናንት የተደፋው ዝናብ ከባድ ጎርፍ አስከተለ::
D. ትናንት የወደቀው ዝናብ ከባድ ጎርፍ አስከተለ::

12. በቅጣዩ ከሌሎቹ የሚለየው የትኛው ቃል ነው?

A. ኮተታም
B. ጥርሳም
C. አሸዋማ
D. ሆዳም

13. "ስራ ላይ እያለ የተሰማ ቤት _____:: "የሚለው አረፍተ ነገር ተገቢ መልእክት የሚያስተላልፈው በየትኛው ቃል ሲደመደም ነው?

A. ተዘረፉ
B. ይዘረፋሉ
C. ተዘረፍን
D. ተዘረፈ

1 1

14. "አዲስ አበባ ዓለም አቀፍ ተልእኮ ያላቸው ድርጅቶች መናኸሪያ ናት:: " በሚለው የአረፍተ ነገሩ ባለቤት የትኛው ነው?

A. ዓለም አቀፍ
B. ተልእኮ
C. አዲስ አበባ
D. ድርጅቶች

15. ትክክለኛውን የቃላት አደራደር ስርአት በመጠበቅ መልእክት የሚያስተላልፈው የትኛው ነው?

A. መጻፍና ማንበብ የማይለያዩ ተግባራት ናቸው::
B. የማይለያዩ መጻፍና ማንበብ ተግባራት ናቸው::
C. ተግባራት የማይለያዩ መጻፍና ማንበብ ናቸው::
D. መጻፍና ተግበራት የማይለያዩ ማንበብ ናቸው::

16. ከሃረጎቹ መካከል ገላጭ ያለው የትኛው ነው?

A. ጥልቅ ጉድጓድ
B. ሩህሩህ ሰው
C. ሰፊ ክፍል
D. ሁሉም መልስ ነው::

17. የመሃል ሆዬው ጠብቆና ላልቶ ሲነበብ የተለያየ ፍቺ የሚሰጠው የትኛው ነው?

A. ምግብ
B. ጠላት
C. ጠባይ
D. ስበት

18. የግስ ገላጭ የሌለው በየትኛው አማራጭ የቀረበው አረፍተ ነገር ነው?

A. አለሙ ከዜደበት ዛሬ ይመለሳል::
B. እግር ኳስ ተጫዋቹ ክፉኛ ተጎዳ::
C. የአማርኛ መምህራችን መጡ::
D. ቤቱ በትናንቱ ዝናብ ፈረሰ::

1 1

19. "_____ ሰው ሁልጊዜ ከስህተቱ ይማራል።" ከአረፍተ ነገሩ መልእክት አኳያ ለባዶ ቦታው ተገቢነት የሚኖረው የትኛው ቃል ነው?

A. ብልህ
B. ረጅም
C. ወፍራም
D. አጭር

20. "ቅጠል" የሚለውን ቃል ወደ ብዙ ቁጥር ለመለወጥ የምንጨምረው ቅጥያ የትኛው ነው?

A. - ያን
B. - አች
C. - ች
D. - ሎች

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 21 እስከ 31 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጭ/ምረጥ።

21. ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች መካከል አንዱ በሚያስተላልፈው መልእክት ተቀባይነት የለውም።

A. በሽታውን የደበቀ መድሃኒት የለውም
B. በእውር ጎዳና ብርቅነው አንድ አይና
C. አንድ አይነድም አንድ አይፈርድም
D. ሳይሰሩ ማግኘት ሳይፀድቁ ገነት

22. እርግጠኛ ላልሆነ አባባል ምሳሌ የሚሆነው የትኛው ነው?

A. ፈተናው ለኔ መጀመሪያ ላይ እንደሚሰጥ ተገለፀ።
B. አበበ በዚህ ዓመት መጨረሻ ሊመጣ ይችላል።
C. ለማዳ ከሆኑ የቤት እንስሳት መካከል አንዷ ድመት ናት።
D. ነጭ ሽንኩርት የተለያዩ በሽታዎችን ለመከላከል ይረዳል።

23. "ሙኩት ሲሰባ ሾተል ይልሳል። " በሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ምንን ለማመልከት እንጠቀማለን?

A. ትእቢት የሚያመጣውን ችግር
B. መኩራራት የሚያስገኘውን ጥቅም
C. የድፍረትን ጠቃሚነት
D. የሙከራን አስፈላጊነት

1 1

24. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል አንዱ በምክንያት ውጤት ላይ የተመሠረተ አይደለም::

A. የመጀመሪያ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና መቼ እንደሚሰጥ ታወቀ::
B. የአካባቢንና የግል ንፅህናን አለመጠበቅ አተት ለተባለው በሽታ መተላለፍ አስተዋፅኦ ያደርጋል::
C. ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በደረስ አዝመራ ላይ ጉዳይ ያደርሳል::
D. በወላጆች መካከል ጭቅጭቅ ካለ ልጆች ትምህርታቸውን በትጋት አይከታተሉም::

25. ከሚከተሉት ቃላት መካከል በአማርኛ መዝገበ ቃላት የአደራደር ስርአት መሠረት መጨረሻ መምጣት ያለበት የትኛው ነው?

ረቂቅ፣ ሂሳብ፣ ክትፎ፣ ትችት

A. ሂሳብ
B. ትችት
C. ክትፎ
D. ረቂቅ

26. "ከኤችአይቪ ጋር መኖራቸውን እንደህይወታቸው ፍፃሜ አድርገው የሚቆጥሩ ሰዎች ቁጥር ቀስ በቀስ እየተመናመነ ነው::" ከሚለው አረፍተ ነገር ምን እንረዳለን?

A. ከኤችአይቪ ጋር መኖራቸውን ከህይወታቸው ፍፃሜ ጋር የሚያመሳስሉ ሰዎች ቁጥር በቀላሉ የማይገመት መሆኑን፣
B. ከኤችአይቪ ጋር በመኖራችን ምክንያት ህይወታችን ለአደጋ እንደተጋልጠ ይቆጠራል የሚሉ ሰዎች ቁጥር እያሻቀበ መሆኑን፣
C. ከኤችአይቪ ጋር በመኖራቸው ህይወታችን አብቅቶለታል ብለው የሚያምኑ ሰዎች ቁጥር በሂደት እየቀነሰ መሆኑን፣
D. ከኤችአይቪ ጋር በመኖራቸው ምክንያት ህይወታቸው እንዳለፈ አድርገው የሚቆጥሩ ሰዎች ቁጥር በሂደት እያንሰራራ መሆኑን፣

27. ከፅሁፋዊ ስነፅሁፍ ዘርፎች መካከል የሚቆጠረው የትኛው ነው?

A. አፈታሪክ
B. የእንጉርጉሮ ግጥም
C. ተረት
D. ረጅም ልቦለድ

1 1

28. መመሪያ እንዲፈፅም በአንድ አዛዥ ከታዘዘ ወታደር ምን ይጠበቃል?

A. የመመሪያውን አፈፃፀም በሚገባ መረዳት
B. የመመሪያውን አንዳንድ ድርጊቶች መፈፀም እንደማይችል መግለፅ
C. መመሪያውን በማሻሻል ተግበራዊ ማድረግ
D. መመሪያውን ለመፈፀም የሚያስችል ዝግጁነት የሌለው መሆኑን መግለፅ

29. ከሚከተሉት አንዱ የንባብ ፍጥነትን ያግዛል።

A. የሚያነቡትን ፅሁፍ በጣት እየጠነቆሉ ማንበብ
B. ተነበው የታለፉ ቃላትንና ሃረጎችን መልሶ ማየት
C. የቃላት ስብስብን በአንድ እይታ ለማንበብ መሞከር
D. የሚያነቡትን ፅሁፍ ቃላት እየቆጠሩ ማንበብ

30. ለአንድ የውይይትና የክርክር ተሳታፊ የማያስፈልገው የትኛው ነው? ንግ

A. የአይን አጣጣልን ማሳመር
B. በግልፅ ቋንቋ መጠቀም
C. የጊዜ ገደብ ማክበር
D. መልሱ አልተሰጠም።

31. "የእናት ጡት ወተት በጣም ጣፋጭ የሆነ፣ በህፃን አንጀት በቀላሉ የሚፈጭና ለእድገት የሚያስፈልጉ አልሚ ምግቦችን አሟልቶ የያዘ ምግብ ነው።" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ያልተካተተው የትኛው ሃሳብ ነው?

A. የእናት ጡት ወተት የሚጣፍጥ መሆኑ፣
B. የእናት ጡት ወተት በቀላሉ የሚፈጭ መሆኑ፣
C. የእናት ጡት ወተት ከላም ወተት ይልቅ የሚሻል መሆኑ፣
D. የእናት ጡት ወተት አልሚ ምግቦችን የሚይዝ መሆኑ፣

1

1

መመሪያ:- ከጥያቄ 32 እስከ 36 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች በሚከተለው ግጥም ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: ጥያቄዎቹን በጥሞና በማንበብ ትክክል የሆኑትን መልሶች ምረጥ/ምረጭ::

እኔው እየቀለጥሁ ብርሃን መሆኔ
ለማንስ ገብቶታል ማን ቆመልኝ ለኔ?
መሃንዲስ ፀሃፊው የሚሳቡ ሊቅ
ምሁራን ጠቢባን ለትንሽ ለትልቅ
የእውቀት ምንጭ ከእኔው ነው የሚፈልቅ
ሆኖም ግን ሰማሁኝ የእኔ ሙያ ሲናቅ::

ምንጭ:- በቀለች ጥሩዬ፣ ለምን፣ ገፅ 2

32. ሙያዬ ተናቀ ያለው ማነው?

A. መምህር
B. ሃኪም
C. ነጋዴ
D. መሃንዲስ

33. በግጥሙ ውስጥ የባለሙያውን ማንነት የሚጠቁመው ስንተኛው ስንኝ ነው?

A. 2
B. 3
C. 4
D. 5

34. በግጥሙ አማካይነት በዋናነት የተገለፀው ምንድን ነው?

A. ባለሙያው እየቀለጠ ብርሃን የሚሰጥ መሆኑ፣
B. ባለሙያው ተገቢው ክብር ያልተሰጠው መሆኑ፣
C. ባለሙያው የእውቀት ምንጭ መሆኑ፣
D. ባለሙያው ረዳት የሌለው መሆኑ፣

35. ከመጨረሻው ስንኝ የመጀመሪያ ሃረግ ጋር በቀለም ብዛት እኩል የሆነው የትኛው ሃረግ ነው?

A. የእውቀት ምንጭ
B. ምሁራን ጠቢባን
C. መሃንዲስ ፀሃፊው
D. ሁሉም መልስ ነው::

1 1

36. ግጥሙን በተመለከተ ትክክል ያልሆነው የትኛው ሃሳብ ነው?

A. ግጥሙ ስድስት ስንኞች አሉት::
B. የግጥሙ ስንኞች ቤት የመቱት በሁለት ሆህያት ነው::
C. ግጥሙ ባለአንድ አርኬ /አንቀፅ/ ነው::
D. መልሱ አልተሰጠም::

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 37 እስከ 46 ድረስ ፅሀፈትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጭ/ምረጥ::

37. የአንድን ድርሰት ሰፊ ክፍል የሚሸፍን የድርሰት አካል ምን ይባላል?

A. መደምደሚያ
B. መግቢያ
C. ሃተታ
D. አስተዋጽኦ

38. የሌላን ሰው የህይወት ታሪክ ለመፃፍ ጠቀሜታ የሌለው የትኛው ነው?

A. ታሪኩ የሚፃፍለትን ሰው በተመለከተ ሰዎችን ማነጋገር
B. ታሪኩ የሚፃፍለትን ሰው ማነጋገር
C. ታሪኩ የሚፃፍለትን ሰው የተመለከቱ ፅሁፎችን ማንበብ
D. መልሱ አልተሰጠም::

39. ለኢልቦለድ ፅሁፍ ምሳሌ የሚሆነው _____ ነው::

A. ዜና
B. ግጥም
C. ተውኔት
D. አጭር ልቦለድ

40. አንድ ወታደር ከሚያገኘው ደመወዝ እየተቀነሰ ለቤተሰቡ እንዲሰጥ የሚጠይቀው በየትኛው ነው?

A. በስራ ደብዳቤ
B. በማመልከቻ ደብዳቤ
C. በሰላምታ ደብዳቤ
D. በማስታወሻ ደብዳቤ

1 1

41. የላኪም የተቀባይም አድራሻ አስፈላጊ የሚሆነው በየትኛው ነው?

A. በሰላምታ ደብዳቤ
B. በስራ ደብዳቤ
C. በማመልከቻ ደብዳቤ
D. ሁሉም መልስ ነው::

42. "እንደሚታወቀው በአለም ላይ ብዙ አይነት የእባብ ዝርያዎች አሉ:: በተለይም ደንና ረጃጅም ሳር በሚበዛባቸው አካባቢዎች ብዙ የእባብ ዝርያዎች ይገኛሉ:: ሆኖም አብዛኞቹ እባቦች መርዛማ አይደሉም:: በአለም ላይ ከሚገኙ ከ3000 በላይ ዝርያዎች ውስጥ 15% ብቻ መርዛማና ተናዳፊ መሆናቸው በጥናት ተጠቁሟል:: ከመርዛማዎቹ ውስጥ ነድፈው እጅግ ለከፋ ጉዳት፣ ብሎም ለሞት የሚያበቁት ጥቂቶቹ ናቸው::"

የዚህን አንቀፅ ዋና ሃሳብ የያዘው የትኛው አረፍተ ነገር ነው?

A. በአለም ላይ የሚገኙ እባቦች ብዛት ከ3000 በላይ ነው::
B. በአለም ላይ ብዙ አይነት የእባብ ዝርያዎች አሉ::
C. ደንና ረጃጅም ሳር በሚበዛባቸው አካባቢዎች ብዙ የእባብ ዝርያዎች ይገኛሉ::
D. በአለም ላይ ከሚገኙ የእባብ ዝርያዎች መካከል መርዛማና ተናዳፊ የሆኑት 15% ያህሉ ብቻ ናቸው::

43. "እንዴት ያለች ውብ ሴት ነች_____" በሚለው በባዶ ቦታው መግባት ያለበት የትኛው ስርአተ ነጥብ ነው?

A. አራት ነጥብ
B. ትእምርተ ጥቅስ
C. ትእምርተ አንክሮ
D. ድርብ ሠረዝ

44. "የመፅሃፍ መደርደሪያው በመፅሄቶች___ በታሪክ____በጠቅላላ እውቀት___ በሳይንስና በልቦለድ መፃህፍት የተሞላ ነው::" በሚለው ባዶ በተደረጉ ቦታዎች መግባት ያለበት የትኛው ነው?

A. ድርብ ሠረዝ
B. ሁለት ነጥብ
C. ነጠላ ሠረዝ
D. ትእምርተ አንክሮ

1 1

45. "ከአዲስ አበባ እስከ ድሬዳዋ ድረስ ለመጓዝ የተለያዩ የመጓጓዣ አይነቶችን መጠቀም ይቻላል።" በሚለው በተሰመረበት ቃል ምትክ የትኛውን ስርአተ ነጥብ መጠቀም ይቻላል?

A. ሙሉ ሠረዝ
B. ነጠላ ሠረዝ
C. ድርብ ሠረዝ
D. ሁለት ነጥብ

46. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የጥቅስ ምልክትን ትክክለኛ አጠቃቀም የሚያሳየው የትኛው ነው?

A. የጦሩ አዛዥ፣"የጠንካራ ሠራዊት መሠረቱ የሃገር ልማት ነው።" ሲሉ፣ ተናገሩ
B. "የጦሩ አዛዥ፣የጠንካራ ሠራዊት መሠረቱ የሃገር ልማት ነው።" ሲሉ፣ ተናገሩ
C. "የጦሩ አዛዥ፣የጠንካራ ሠራዊት መሠረቱ የሃገር ልማት ነው ሲሉ ተናገሩ።"
D. የጦሩ አዛዥ፣"የጠንካራ ሠራዊት መሠረቱ" "የሃገር ልማት ነው።" ሲሉ ተናገሩ።

መመሪያ፡- ከጥያቄ 47 እስከ 60 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች የሚከተለውን ምንባብ መሠረት ያደረጉ ናቸው። በአጠያየቃቸው መሠረት ትክክል የሆኑትን መልሶች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጥ/ምረጭ።

ምንባብ

የአንድን ፅንስ መወለጃ ጊዜ በመቅደም ከ28 ሳምንታት በፊት የሚደረግ እርግዝናን የመግታት ሂደት ፅንስ ማቋረጥ ይባላል። ፅንስ ማቋረጥ በሃገራችን ካሉትና ለእናቶች ሞት ሰበብ ከሆኑት ጤና ነክ ችግሮች መካከል በዋናነት ይጠቀሳል። እንደ አለም ጤና ድርጅት መረጃ ከሆነ፣በሃገራችን ሆስፒታሎች ውስጥ እናቶችን ለሞት ከሚያበቁት ጤና ነክ ችግሮች መካከል ህገወጥ ፅንስን የማቋረጥ ተግባር አብዛኛውን ድርሻ ይይዛል። የጤና ባለሙያ በሆኑና ባልሆኑ (ለምሳሌ ጎረቤትና ጓደኛ፣የባህል መድሃኒት አዋቂዎች) አማካኝነት ህገወጥ የፅንስ ማቋረጥ አድርገው ሆስፒታል ከሚመጡት እናቶች መካከል፣ 10 በመቶ ያህሉ እንደሚሞቱ በዚሁ ድርጅት ተጠቁሟል። የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩትም፣ በህገወጥ ፅንስ የማቋረጥ ተግባር ውስጥ ከሚሳተፉ አንድ ሺህ ሴቶች መካከል 200 ያህሉ ይሞታሉ። ከእነዚህም አብዛኛዎቹ ከ16–20 በሚሆነው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣት ሴቶች ናቸው።

1 1

በኢትዮጵያ ሆን ብሎ አንድን ፅንስ ማቋረጥ ህገወጥ ድርጊት መሆኑ በህግ ተደንግጓል። ድርጊቱ ግን በስፋት የሚታይ ችግር ሆኖ ቀጥሏል። በ1949 ዓ.ም. በወጣው የሃገራችን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ላይ፣ በማንኛውም መንገድ ሆን ብሎ ፅንስን ያቋረጠ ወይም ለድርጊቱ መፈፀም የተባበረ በፅኑ እንደሚቀጣ ተገልጿል። በተመሳሳይም የአለም ጤና ድርጅት ህገወጥ ፅንስ ማቋረጥን የሚያበረታቱ ሕጎችን አይደግፍም። ድርጅቱ ህገወጥ ፅንስ የማቋረጥ ተግባርን ለማስወገድና ለመከላከል ህጋዊ ከሆኑ መንገዶች በተጨማሪ፣ ሌሎች ተግባራትም ትኩረት እንዲሰጣቸው ያሳስባል። በዚህም መሠረት፣ የቤተሰብ እቅድን የተመለከቱ አገልግሎቶች እንዲዳረሱ መጣር አይነተኛ መፍትሄ መሆኑን ይጠቁማል።

ፅንስ የሚቋረጥባቸው የተለያዩ ሁኔታዎች አሉ። አንደኛው ሆን ብሎ ወይም በሰው አማካይነት የሚካሄድ ህገወጥ ፅንስ ማቋረጥን ሲያካትት፣ ሌላው በተለያዩ ምክንያቶች ፅንሱ በራሱ ጊዜ ወይም ያለ ፍላጎት በመገደድ የሚቋረጥበትን ሂደት ያመለክታል። ሳይታሰብ የሚካሄድ ፅንስ ማቋረጥ በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል። ዋና ዋናዎቹም፣ አንዲት ሴት በተፈጥሮ የተነሳ ማህፀኗ ለሁለትና ከሁለት በላይ የተከፈለና ከአማካይ መጠኑም ትንሽ ወይም ትልቅ መሆኑ፣ ከተፈጥሮ ጋር የተያያዙ እንደ ሾተለይ ያሉ የወሊድ ችግሮች፣ በመደብደብ፣ በመውደቅና በመሳሰሉ አደጋዎች በማህፀን ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች፣ በሃኪም ያልታዘዙ መድሃኒቶችን መውሰድ የሚሉት ናቸው።

ምንጭ:- አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም.

47. ከሚከተሉት ሃሳቦች መካከል ዝርዝር ሃሳብ የሆነው የትኛው ነው?

A. በሃገራችን ለእናቶች ሞት ምክንያት ከሆኑት የጤና ችግሮች መካከል ዋናው ህገወጥ ፅንስ ማቋረጥ ነው።
B. በሕገወጥ ፅንስ የማቋረጥ ተግባር ውስጥ ከሚሳተፉ አንድ ሺህ ሴቶች መካከል 200 ያህሉ ይሞታሉ።
C. በኢትዮጵያ በህገወጥ መንገድ ፅንስ ማቋረጥ ህገወጥ ድርጊት መሆኑ በህግ ተደንግጓል።
D. የተለያዩ ፅንስን የማቋረጥ ሁኔታዎች አሉ።

48. ህገወጥ ፅንስ የማቋረጥ ተግባር ፈፅመው ሆስፒታል ከሚመጡ ሴቶች መካከል_____።

A. አብዛኛዎቹ ይሞታሉ
B. ሃምሳ ከመቶ ያህሉ ይሞታሉ
C. ሃያ ከመቶ ያህሉ ይሞታሉ
D. ሁሉም ይሞታሉ

1 1

49. ፅንስ ማቋረጥን በተመለከተ ከሃገራችን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንፃር ምን መደምደም ይቻላል?

A. ህጉ ህገወጥ ፅንስ ማቋረጥን በተመለከተ ልል መሆኑን፣
B. ህጉ በህገወጥ ፅንስ የማቋረጥ ሂደት የተሳተፉትን ሁሉ በፅኑ እንደሚቀጣ፣
C. ህጉ ለፅንሱ በህገወጥ መንገድ መቋረጥ የተባበሩትን የቅጣቱ አካል እንደሚያደርጋቸው፣
D. ህጉ ፅንሱ በህገወጥ መንገድ እንዲቋረጥ የፈለጉትን ብቻ ለይቶ እንደሚቀጣ፣

50. በኢትዮጵያ ውስጥ ፅንስ ማቋረጥን በተመለከተ ያለው ህጋዊ አቋም ምን ይመስላል?

A. ፅንስ ማቋረጥ ህጋዊ ነው::
B. ፅንስ ማቋረጥ የህግ ከለላ ይደረግለታል::
C. ህገወጥ ፅንስ ማቋረጥ የፈፀመ እንደ ወንጀለኛ ይቆጠራል::
D. ፅንስ ማቋረጥ ስለሚያስከትለው የቅጣት ሁኔታ በግልፅ አልተደነገገም::

51. ኢትዮጵያ ውስጥ ፅንስ ማቋረጥን በተመለከተ ያለውን እውነታ የሚገልፀው የትኛው ነው?

A. የሚያስከትለውን ቅጣት በመፍራት በህገወጥ መንገድ ፅንስን የማቋረጥ ድርጊት በስፋት አይታይም::
B. ህገወጥ ፅንስ የማቋረጥ ተግባር ከፈፀሙ ሴቶች መካከል አስር ከመቱ የሚሆኑት ይሞታሉ::
C. ፅንስ የሚያቋርጡ ሴቶች በአብዛኛው በጎልማሳነት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው::
D. በህገወጥ የፅንስ ማቋረጥ ድርጊት የሚሳተፉ የህክምና ባለሙያዎች አሉ::

52. ለምንባቡ ተገቢነት ያለው የትኛው ርእስ ነው?

A. የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት አሰጣጥ
B. ፅንስን የማቋረጥ ሁኔታዎችና አደጋዎች
C. ያልተፈለገ እርግዝና
D. የፅንስ ማቋረጥ ህጋዊነት

1 1

53. ሳይታሰብ ለሚካሄድ ፅንስን የማቋረጥ ተግባር ምክንያት ከሆኑት መካከል በዋናነት ሊጠቀስ የሚገባው _____ ነው::

A. ተፈጥሯዊ ሁኔታ
B. ያልታዘዙ መድሃኒቶች መውሰድ
C. ድብደባ
D. በተለያዩ ምክንያቶች መውደቅ

54. ሆነ ተብሎ ለሚካሄድ ፅንስን የማቋረጥ ተግባር ምክንያት የማይሆነው የትኛው ነው?

A. ተገዶ መደፈር
B. ያልታዘዙ መድሃኒቶችን መውሰድ
C. ያልተፈለገ እርግዝና
D. የወሊድ መቆጣጠሪያን ባግባቡ አለመጠቀም

55. ህገወጥ ፅንስ የማቋረጥ ተግባርን ለመከላከልና ለማስወገድ ተመራጭ ነው የተባለው የትኛው ነው?

A. በህገወጥ ተግባሩ የሚሳተፉ ሰዎችን በወንጀል መጠየቅ፣
B. በህገወጥ ተግባሩ ሰዎች እንዳይሳተፉ የሚያደርግ ጠንካራ ህግ ማውጣት፣
C. የተሻሻሉ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ማዳረስ፣
D. የጤና ባለሙያዎች በተግባሩ እንዳይሳተፉ የሚያስችል ግንዛቤ መፍጠር፣

56. ምንባቡ ለየትኛው የድርሰት አይነት ምሳሌ ይሆናል::

A. ለስእላዊ
B. ለገላጭ
C. ለአመዛዛኝ
D. ለተራኪ

1 1

57. የአለም ጤና ድርጅት ህገወጥ ፅንስ የማቋረጥ ተግባርን በተመለከተ ምን ይሁን ይላል?

A. መንግስታት ለህገወጥ ፅንስ የማቋረጥ ተግባር ህጋዊ እውቅና ይስጡ ይላል::
B. መንግስታት ህገወጥ ፅንስ የማቋረጥ ተግባርን አያበረታቱ ይላል::
C. መንግስታት በህግ ብቻ ህገወጥ ፅንስ የማቋረጥ ተግባርን መከላከል አለባቸው ይላል::
D. የእናቶችን ሞት ለመከላከል ሲባል ህገወጥ ፅንስ የማቋረጥ ተግባር የፈፀሙ አይቀጡ ይላል::

58. የመጨረሻው አንቀፅ ዋና ሃሳብ የሆነው የትኛው ነው?

A. አንድ ፅንስ በተለያዩ ምክንያቶች በራሱ ጊዜ ሊቋረጥ ይችላል::
B. ሳይታሰብ ለሚካሄድ ፅንስ ማቋረጥ መነሻ የሆኑ ምክንያቶች አሉ::
C. ተፈጥሯዊ በሆኑ ምክንያቶች ፅንስ ሊቋረጥ ይችላል::
D. አንድ ፅንስ የሚቋረጥባቸው የተለያዩ ሁኔታዎች አሉ::

59. ወጣት ሴቶች ህገወጥ ለሆነው ፅንስ ማቋረጥ ተግባር የሚጋለጡበት ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል?

A. ያልተፈለገ እርግዝና ማጋጠም፣
B. በመደፈር አደጋ ምክንያት በሚመጣ እርግዝና፣
C. የወሊድ መቆጣጠሪያዎች የአጠቃቀም ችግር፣
D. ሁሉም መልሰ ይሆናል::

ሰሞ60. "በኢትዮጵያ ሆን ብሎ አንድን ፅንስ ማቋረጥ ህገወጥ ድርጊት መሆኑ በህግ ተደንግጓል:: ድርጊቱ ግን በስፋት የሚታይ ችግር ሆኖ ቀጥሏል:: " በ"ግን" ምትክ ሁለቱን አረፍተ ነገሮች ለማያያዝ ተመራጭ የሚሆነው የትኛው አያያዥ ነው?

A. ሆኖም
B. እና
C. ወይም
D. ስለዚህ

ኦባሪ ሦስት

1 የሀገር መከላከያ ሠራዊት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት 1
ፈተና
2003 ዓ.ም

የጥያቄ ብዛት:- 60 የተፈቀደው ጊዜ:- 60 ደቂቃ

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 1 እስከ 13 ድረስ ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጭ/ምረጥ::

1. "አወጣ" ከሚለው ግስ ጋር በመቀናጀት ፊሊጣዊ አነጋገር የሚመሰርተው ቃል የቱ ነው?

A. ነገር
B. ሃሳብ
C. አመል
D. ቤት

2. "ሰለጠነ" የሚለው ቃል ከሚኖረው ፍቺ ጋር ዝምድና የሌለው የትኛው ነው?

A. ስልጡን
B. ስልጣኔ
C. ማሰልጠኛ
D. ሰልፈኛ

3. የጌጥነት አገልግሎት የማይሰጠው የትኛው ነው?

A. ሃብል
B. አንባር
C. ወረንጦ
D. ጉትቻ

4. ከሚከተሉት ውስጥ በስራስርነት የማይመደበው የትኛው ስያሜ ነው?

A. ድንች
B. ካሮት
C. ብርቱካን
D. ዝንጅብል

5. " በብዙ አገሮች በአሳሳቢነታቸውና _____ ከሚጠቀሱት በሽታዎች መካከል አንዱ ኤድስ ነው::" በሚለው አረፍተነገር ከመልእክት አኳያ ለባዶ ቦታው ተመራጭ የሚሆነው የትኛው ነው?

A. በአስከፊነታቸው
B. በአካሄዳቸው
C. በአዎንታዊነታቸው
D. በአብነታቸው

6. ከሚከተሉት ቃላት መካከል አንዱ በሚሰጠው ፍቺ ይለያል።

A. ከተተ
B. ጨመረ
C. አከለ
D. በለጠ

7. ከሚከተሉት ቃላት መካከል "ሸረፈ" የሚለው ቃል ፍቺ ያልሆነው የትኛው ነው?

A. ቀለጠ
B. ቆረሰ
C. ሰበረ
D. ቀነሰ

8. ከቃላቱ መካከል ለቀሪዎቹ ተቃራኒ ፍቺ የሚሆነው የትኛው ነው?

A. ፍስሃ
B. ሃሴት
C. መከራ
D. ደስታ

9. "የሚሠራ ሲከበር፣ የሚያለምጥ_____።" በሚለው የአረፍተነገሩን መልእክት ከማሟላት አኳያ ለባዶ ቦታው የሚስማማው የትኛው ቃል ነው?

A. ይወደሳል
B. ይሞገሳል
C. ይወቀሳል
D. ይዘከራል

10. አንድ ሰው "ትምህርት አይዝም" ሲባል ምን ማለት ነው?

A. ትምህርት አይወድም።
B. ትምህርት አያዘወትርም።
C. ትምህርት ይሰለቸዋል።
D. ትምህርት አይገባውም።

11. "ልጁ በትንሽ በትልቁ አፍንጫውን ይነፋል።" በሚለው ልጁ በባህሪው _____ ነው።

A. ተደባዳቢ
B. አኩራፊ
C. ተለማማጭ
D. ጉረኛ

12. "አቶ እስማኤል ለሠራተኞቻችው 'ስራውን ገፋ ገፋ አደርጉት!' ብለው ተናጋሩ።" በሚለው አረፍተነገር፣ አቶ እስማኤል ያስተላለፉት መልእክት ምንድን ነው?

A. እረፍት ወስዱ
B. ፈጠን ፈጠን በሉ
C. በጀመራቻሁት ስራ ምትክ ሌላ ጀምሩ
D. የተለያዩ ስራዎችን በአንድ ጊዜ ስሩ

13. "ትህትና <u>በነገር ሰሪነቷ</u> በይበልጥ ትታወቃለች።" በተሰመረበት ፈሊጥ ፍቻ መሠረት፣ ትህትና በምን ትታወቃለች?

A. በለፍላፊነቷ
B. በነገር አዋቂነቷ
C. በአሳባቂነቷ
D. በተሟጋችነቷ

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 14 እስከ 27 ድረስ ለዋስውን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ።

14. ከሚከተሉት ቃላት መካከል የመጨረሻ ሆሄው ጠብቆና ላልቶ ሲነበብ የተለያየ ፍቺ የሚሰጠው የትኛው ነው?

A. ደግ
B. ጎጥ
C. በራ
D. ራሰ

15. ባስቀጠለው ቅጥያ የሚለየው የትኛው ቃል ነው?

A. ደስተኛ
B. ሃዘንተኛ
C. መለስተኛ
D. ነፍጠኛ

1

1

16. ከአረፍተ ነገሮቹ መካከል በቃላት አጠቃቀሙ ስህተት ያለበት _____ ነው።

A. ዘንድሮ የጣለው ዝናብ አዝመራውን ጥሩ አድርጎታል።
B. ዘንድሮ የተወረወረው ዝናብ አዝመራውን ጥሩ አድርጎታል።
C. ዘንድሮ የዘነበው ዝናብ አዝመራውን ጥሩ አድርጎታል።
D. ዘንድሮ የወረደው ዝናብ አዝመራውን ጥሩ አድርጎታል።

17. በትክክል በመፃፉ ተገቢ መልእክት የሚያስተላልፈው የትኛው አረፍተነገር ነው?

A. የሂሳብ መምህራችን ሲታስተምር ጎበዝ ነው።
B. የሂሳብ መምህራችን ሲታስተምር ጎበዝ ናት።
C. የሂሳብ መምህራችን ስታስተምር ጎበዝ ናቸው።
D. የሂሳብ መምህራችን ስታስተምር ጎበዝ ነኝ።

18. በቅንፉ ውስጥ ያሉት ቃላት ተገቢውን መልእክት እንዲያስተላልፉ እንዴት መቀናበር አለባቸው?

(ታምራለች፣መምህራችን፣የአማርኛ፣መኪና)
A. መምህራችን የአማርኛ መኪና ታምራለች።
B. የአማርኛ መኪና መምህራችን ታምራለች።
C. የአማርኛ መምህራችን መኪና ታምራለች።
D. መኪና የአማርኛ መምህራችን ታምራለች።

19. ከቃላቱ መካከል አንስታይ ፆታን የሚያመለክተው የትኛው ነው?

A. አማች
B. ወይፈን
C. ወጠጤ
D. አክስት

20. የባለቤት ገላጭ ያለው የትኛው አረፍተነገር ነው?

A. ሃይሉ ጎበዝ ልጅ ነው።
B. የሃይሉ እናት በጣም ደግ ናቸው።
C. ሃይሉ ማንበብ ያዘወትራል።
D. ሃይሉ ከክፍሉ አንደኛ ወጣ።

21. ከአረፍተነገሮቹ መካከል የማሰሪያ አንቀፅ ገላጭ የሌለው የትኛው ነው?

A. መምህሯ አልማዝ ብዙ ዛፍ ተከለች።
B. መምህሯ አልማዝ ወለደች።
C. መምህሯ አልማዝ ስራ ትወዳለች።
D. መምህሯ አልማዝ ክፉኛ ተበሳጨች።

22. "ፈለቀች ትናንት በገዛችው ሳሙና ተበሳጨች።" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የአረፍተነገሩ ባለቤት ምን የሚለው ነው?

A. ፈለቀች
B. ሳሙና
C. በገዛችው
D. ትናንት

23. ከቃላቱ ውስጥ አንዱ መነሻ ቅጥያ አለው።

A. ለግላጋ
B. ህጋዊ
C. አስጨናቂ
D. ቤተኛ

24. "በትናንቱ ገበያ ቡና በርካሽ ዋጋ ሲሸጥ እንደዋለ ተገለጸ።" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ካሉት የስያሜ ቃላት መካከል አንዱ _____ነው።

A. በርካሽ
B. ሲሸጥ
C. ቡና
D. ተገለጸ

25. የአንድ ነገር መቋጫ ወይም ማረፊያ ነው የሚባለው የትኛው ነው?

A. አረፍተነገር
B. ሃረግ
C. ቃል
D. ድርሰት

1 1

26. " ወታደር ዓለሙ ለቤተሰቦቹ ደብዳቤ ፃፈ።" የሚለው አረፍተነገር በአሉታ ሲፃፍ ትክክል የሚሆነው የትኛው ነው?

A. ወታደር ዓለሙ ለቤተሰቦቹ ደብዳቤ ይፃፍ።
B. ወታደር ዓለሙ ለቤተሰቦቹ ደብዳቤ አልፃፈም።
C. ወታደር ዓለሙ ለቤተሰቦቹ ደብዳቤ አይፅፍም።
D. ወታደር ዓለሙ ለቤተሰቦቹ ደብዳቤ ይፅፋል።

27. "_____ ወታደር የማእረግ እድገት አገኘ።" በሚለው ከመልእክት አካያ ለባዶ ቦታው ተገቢነት የሌለው የትኛው ነው?

A. ጠመንጃው
B. አልሞተኳሹ
C. ልበሙሉው
D. አይበገሬው

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 28 እስከ 42 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጭ/ምረጥ።

28. "አነቃነቀ" የሚለውን ቃል ፍቺ ከመዝገበቃላት ለማግኘት የሚጠቅመን ቃል _____ ነው።

A. ነቃነቀ
B. ነቀነቀ
C. ነቃ
D. አነቃ

29. "አፄ ምኒልክ ከአድዋ ድል በኋላ ሠራዊታቸውን አስከትለው ግንቦት 3 ቀን 1888 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ።" የሚለው አረፍተነገር ዋና ሃሳብ ምንድን ነው?

A. በአድዋ ድል መገኘቱ
B. አፄ ምኒልክን ሠራዊታቸው የሚከተላቸው መሆኑ
C. የአፄ ምኒልክ አዲስ አበባ መግባት
D. ከግንቦት 3 ቀን 1888 ዓ.ም. በፊት በአድዋ ድል መገኘቱ

30. ኮሚኩኬሽን አረፍተ ነገሮች መካከል አንዱ በሚያስተላልፈው መልእክት ይለያል።

A. ለኑሮአችን ፀር ከሆኑት ነገሮች መካከል አንዱ ስንፍና ነው።
B. ስንፍና ለኑሮአችን ፀር ናቸው ከሚባሉት ነገሮች መካከል አንዱ ነው።
C. ኑሮአችን ላይ ተፅዕኖ አላቸው ከሚባሉት ነገሮች ውስጥ እንደ አንዱ ተደርጎ የሚቆጠረው ስንፍና ነው።
D. በኑሮአችን ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮችን በውል በመለየት መንቀሳቀስ እንደሚገባ ተገለፀ።

31. በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ የሚደረግ ንግግር አድማጭን ሳቢና ማራኪ እንዲሆን የሚያደርገው የትኛው ነው?

A. የንግግሩን ርእሰ ጉዳይ ሳያስተዋውቁ በቀጥታ ወደ ዋናው የንግግሩ ፍሬ ሃሳብ መሸጋገር።
B. ከንግግሩ ታዳሚዎች መካከል የተወሰኑት ለንግግሩ በሚሰጡት ትኩረት መበረታታት።
C. የሚያደረጉት ንግግር በአካል እንቅስቃሴ የታጀበ እንዲሆን በማድረግ የአድማጭን ትኩረት ለማግኘት መጣር
D. በንግግሩ ሂደት ከአድማጮች ስሜትና ፍላጎት ይልቅ ለመልእክቱ መተላለፍ የበለጠ ትኩረት መስጠት።

32. "የታሪክ፣የሳይንስና የሂሳብ መማሪያ መፃህፍት" እንዴት መነበብ አለባቸው?

A. በገረፍታ
B. በአሰሳ
C. በማስተዋል
D. በፍጥነት

33. "ሰርቆ ከማሰብ እጅን መሰብሰብ።" የሚለውን ምሳሌያዊ አነጋገር መልእክት የሚያንፀባርቀው የትኛው ነው?

A. የሰውን ንብረት መውሰድ ያስጨንቃል።
B. አንድን ነገር ካከናወኑ በኋላ ከመፀፀት አስቀድሞ ማሰብ
C. እጅን ከሰበሰቡ መስረቅ አይኖርም።
D. ሰርቆ ከመጨነቅ የሰረቁትን መመለስ ይጠቅማል።

34. ለግል አስተያየት ምሳሌ የሚሆነው የትኛው ነው?

A. ሳንባ ነቀርሳ በገዳይነታቸው ከሚታወቁ በሽታዎች መካከል አንዱ ነው::
B. ኤችአይቪ ለሳንባ ነቀርሳ በሽታ መስፋፋት አስተዋፅኦ ያደርጋል::
C. ሳንባ ነቀርሳ በቫክቴሪያ አማካይነት የሚተላለፍ በሽታ ነው::
D. የሳንባ ነቀርሳ በሽታ እንዳይዘን ስለበሽታው በቂ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል::

35. " 'ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ::' የሚለውን ምሳሌያዊ አነጋገር በመዘንጋት፣ አንዳንድ ተማሪዎች ባገኙት ውጤት ሲያዝኑ ነበር::" በሚለው በነጠላ ትእምርተ ጥቅሱ ያለው ምንን ያመለክታል?

A. ሳይታመሙ በፊት ላለመታመም መጣር የሚገባ መሆኑን
B. ምንም ጥንቃቄ ቢደረግ ማንም ሰው የሚታመም መሆኑን
C. የታመመ ሰው ተገቢውን ጥንቃቄ ካደረገ በፍጥነት ከህመሙ ሊድን እንደሚችል
D. የተለያዩ ችግሮች ከመድረሳቸውና ከማጋጠማቸው በፊት የሚደረግ ጥንቃቄ ጠቃሚነት ያለው መሆኑን

36. ነገሥ "የፆታ ጥቃት ወንዶችንም አልፎ አልፎ የሚመለከት ቢሆንም፣ በአብዛኛው በሴቶች ላይ ይፈፀማል::" ከሚለው አባባል ምን እንረዳለን?

A. የፆታ ጥቃት በእኩል መጠን በሴቶችም በወንዶችም ላይ የሚደርስ መሆኑን
B. የፆታ ጥቃት በአብዛኛው በወንዶችም በሴቶችም ላይ የሚፈፀም መሆኑን
C. የፆታ ጥቃት በሁሉም ሰው ላይ ሊፈፀም የሚችል ክስተት መሆኑን
D. የፆታ ጥቃት በእኩል ደረጃ በወንዶችም በሴቶች አማካይነት የሚፈፀም መሆኑን

37. ከሚከተሉት አንዱ በተውኔት ሥራ ውስጥ ተሳትፎ የለውም ::

A. ሠዓሊነት
B. ሙዚቀኛነት
C. ደራሲነት
D. መምህርነት

38. ለኢልቦለድ ጽሁፍ ምሳሌ የሚሆነው የትኛው ነው?

A. አጭር ልቦለድ
B. ግጥም
C. ተውኔት
D. ዜና

39. " ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል:: " ከሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ጋር በፍቺ የሚስማማው የትኛው ነው?

A. ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ::
B. የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል::
C. የቸኮለ አፍሶ ለቀመ::
D. አተርፍ ባይ አጉዳይ::

40. "የኔ ጌታ የሰጠኝ ሙክት፣
ከግንባሩ ላይ አለው ምልክት፣
መስከረም ጠባ እሱን ሳነክት:: "

ይህን ግጥም በተመለከተ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?
A. ገጣሚው ማን እንደሆነ በትክክል ይታወቃል::
B. መቼ እንደ ተገጠመ በትክክል ይታወቃል::
C. ከዘመን ዘመን በቃል ሲተላለፍ እንደመጣ ይታወቃል::
D. በሁሉም የሃገራችን አካባቢዎች በሚገባ ይታወቃል::

41. ጥያቄ 45 ላይ የቀረበው ግጥም ስንት ስንኞች አሉት

A. አንድ
B. ሁለት
C. ሦስት
D. አራት

42. ጥያቄ 45 ላይ የቀረበው ግጥም ቤት የመታው በየትኛው ሆሄ ነው?

A. ክ
B. ት
C. ነ
D. ሳ

1 1

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 43 እስከ 49 ድረስ ፅሀፈትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ::

43. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል በስርአተ ነጥብ አጠቃቀሙ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው::

A. "ምርጥ ምርጡን ለህፃናት" የሚለው ምክር ምን ያስገነዝበናል?
B. ስእል ለመሳል አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች የትኞቹ ናቸው::
C. መምህሩ ተማሪውን "ለመሆኑ ምን አጥፍተህ ነው ወላጅ አምጣ የተባልከው?" አሉት::
D. ግርማ በማያገባው ነገር ለምን ጥልቅ ይላል!

44. "እኛ የሰለጠነው አለም ስልጡን ወታደሮች፣ምንም አያውቁም ከሚባሉት ኢትዮጵያውያን የምንማረው ትምህርት አለ:: አበሾች ለባሩድና ለጥይት ይሳሳሉ:: የሚገድሉ ካልሆነ በስተቀር አይተኩሱም:: ለዚያውም ቢሆን 10 እና 15 ያርድ ያህል ቀርበው ባንድ ጥይት ደራርበው መግደል ይፈልጋሉ እንጂ ጥይት ማበላሸት አይወዱም::"

በሚለው አንቀጽ ሊተላለፍ የተፈለገው ዋና መልእክት ምንድን ነው?
A. የአበሾች በጦርነት ጊዜ ለባሩድና ለጥይት መሳሳት
B. የኢትዮጵያውያን ምንም አያውቁም መባል
C. የአበሾች በጦርነት ጊዜ ባንድ ጥይት ደራርበው የመግደል ፍላጎት ያላቸው መሆኑ
D. የሌላው አለም ስልጡን ወታደሮች ከኢትዮጵያውያን የሚማሩት ትምህርት ያለ መሆኑ

45. "ወታደር መሰለ ለቤተሰቦቹ የፃፈውን ደብዳቤ በፖስታ አድርጎ የላከ ቢሆንም፣ ሳይደርስ ተመላሽ ሆነበት::"

ፖስታው ተመላሽ ሊሆን የሚችልበት ዋና ምክንያት ምንድን ነው?
A. ፖስታው ቀን ያልተፃፈበት መሆኑ
B. ፖስታው የተቀባይና የላኪ አድራሻ ያልተፃፈበት መሆኑ
C. ደብዳቤው መግቢያ፣ ሃተታና መደምደሚያ የሌለው መሆኑ
D. የተፃፈው ደብዳቤ ያልተፈረመበት መሆኑ

46. " ከቀሪው አለም ጋር ሲነፃፀር በአሜሪካ ዝቅተኛ የኤችአይቪ ስርጭት ቢኖርም፣ ሁኔታውን በቅርብ ለሚከታተሉ ግን የበሽታው ስርጭት አሳሳቢ ነው። ስለሆነም፣ በየእለቱ ከአንድ መቶ በላይ አሜሪካውያን ከኤችአይቪ ጋር ሕሚኖሩ ሰዎች ጎራ ይቀላቀላሉ። በየአመቱም ከ40ሺህ በላይ አሜሪካዊያን በአዲስነት ከኤችአይቪ ጋር መኖር ይጀምራሉ። ከሁሉም በላይ አስደንጋጭ የሆነው ግን፣ ከ25 አመት የቫይረሱ ጉዞ በኋላ እንኳን 10% የሚሆነው ወጣት አሜሪካዊ ቫይረሱን እንዴት መከላከል እንዳለበት ወይም በቫይረሱ እንዴት ሊጠቃ እንደሚችል ጠንቅቆ አለማወቁ ነው።"

የዚህ አንቀጽ ዋና መልእክት የትኛው ነው?

A. የአሜሪካ ወጣቶች ስለኤችአይቪ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ ነው።
B. በአሜሪካም ጭምር የኤችአይቪ ስርጭት አሳሳቢ ነው።
C. ከሌሎቹ ሃገራት ጋር ሲነፃፀር የኤችአይቪ ስርጭት በአሜሪካ ዝቅተኛ ነው።
D. በየእለቱ ከአንድ መቶ በላይ አሜሪካውያን ከኤችአይቪ ጋር መኖር ይጀምራሉ።

47. ከሚከተሉት ስያሜዎች መካከል የፈጠራ ፅሁፍ የሆነው የትኛው ነው?

A. የህይወት ታሪክ
B. የሥራ ማመልከቻ
C. መዝገበ ቃላት
D. ልቦለድ ታሪክ

48. "ወታደር ዘይነባ ቤተሰቦቿን በጣም ናፍቃለች ____ ከሳምንት በኋላ ልትጠይቃቸው አቅዳለች።" በሚለው አረፍተነገር ለባዶ ቦታው ተገቢነት ያለው የትኛው ስርአት ነጥብ ነው?

A. ኣጠላ ሠረዝ
B. ድፎብ ሠረዝ
C. ሁለት ነጥብ
D. ሶስት ነጥብ

49. የስርአት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት የሚታየው በየትኛው አማራጭ ነው?

A. 8፡45 ሰዓት
B. 10.50 ብር
C. አ.አ.
D. አዎ፤

1

1

መመሪያ፡- ከጥያቄ 50 እስከ 60 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች የሚከተለውን ምንባብ መሠረት ያደረጉ ናቸው። በአጠያየቃቸው መሠረት ትክክል የሆኑትን መልሶች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጭ/ምረጥ።

ምንባብ

ውሃ ለህይወታችን በጣም አስፈላጊ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት ነው። በእፅዋትና በእንስሳት አካል ውስጥ በብዛት ይገኛል። ስለሆነም፣ ከመቶ ሰባ አንድ እጅ (71%) የሚሆነው የመሬት አካል በውሃ እንደተሸፈነ ሁሉ፣ ከመቶ ሰባ እጅ (70%) የሚሆነው የሰውነታችን ይዘትም ውሃ ነው።

ማንኛውም ህይወት ያለው ነገር ያለማቋረጥ ውሃ ማግኘት አለበት። ሆኖም መጠኑ እንደ አካባቢው ሙቀት ይለያያል። ለምሳሌ፣ የበቆሎ ተክል በቀን ከ2 እስከ 4 ሊትር ውሃ ማግኘት ይፈልጋል። የሰው ልጅ ደግሞ፣ በቀን ከ2.8 እስከ 13 ሊትር ውሃ ማግኘት ይኖርበታል።

ከመቶ ዘጠና ሰባት እጅ(97%) የሚሆነው የአለማችን ውሃ በባህሮችና በውቅያኖሶች ይገኛል። ከመቶ ሁለት እጅ (2%) የሚሆነው ደግሞ በምድር ዋልታዎችና በቀዝቃዛ ስፍራዎች በበረዶ መልክ ይገኛል። በባህሮችና በውቅያኖሶች ውስጥ የሚገኘው ውሃ በቀጥታ ለመጠጥነት ሊውል አይችልም። ምክንያቱም ውሃው ጨዋማ ስለሆነ ነው።

ከጠቅላላው የአለማችን ውሃ ለመጠጥነት ሊውል የሚችለው ከመቶ አንድ እጅ (1%) የሚሆነው ብቻ ነው። ለመጠጥ ከሚያገለግለው ውሃ ውስጥ ከመቶ ሰባ እጅ (70%) የሚሆነው በሃይቆች፣ በወንዞችና በከባቢ አየር ውስጥ ይገኛል። የቀረው ማለትም ከመቶ ሰላሳ እጅ (30%) የሚሆነው ደግሞ ከከርሰ ምድር፣ ከምንጮችና ከጉድጓዶች ይገኛል።

ውሃ በአለማችን እጅግ ውድ ከሆኑት የተፈጥሮ ሃብቶች ውስጥ አንደኛው ነው። በተለየ ንፁህ ውሃ በጣም ውድ ነው። ይህም የሆነው፣ የውሃ ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየጨመረ የሚሄድ በመሆኑ ነው። ለዚህም በዋና መንስዔነት የሚጠቀሱት የህዝብ ብዛት መጨመርና የኑሮ ደረጃዎች መሻሻል ናቸው።

የፅሁፉ ምንጭ፡- በላቸው በቀለ። 1996 ዓ.ም.። አካባቢያችን (ተሻሽሎ የቀረበ)

50. የሰው ልጅ በቀን ውስጥ ማግኘት የሚገባው ዝቅተኛው የውሃ መጠን ስንት መሆን አለበት?

A. 2 ሊትር
B. 2.8 ሊትር
C. 4 ሊትር
D. 13 ሊትር

51. ከጠቅላላው የአለማችን ውሃ ውስጥ ምን ያህሉ ለመጠጥ አገልግሎት ይውላል?

A. ከመቶ አንድ እጅ
B. ከመቶ ሁለት እጅ
C. ከመቶ ሰላሳ እጅ
D. ከመቶ ዘጠና ሰባት እጅ

52. አብዛኛው የአለማችን ውሃ ጥቅም ላይ የማይውልበት ዋና ምክንያት ምንድን ነው?

A. የማይጥም በመሆኑ
B. የሚመር በመሆኑ
C. ጨዋማ በመሆኑ
D. ቆሻሻ በመሆኑ

53. በሰውነታችን ውስጥ የሚገኘው የውሃ መጠን ምን ያህል ይሆናል?

A. ከመቶ ሰላሳ እጅ
B. ከመቶ ሰባ እጅ
C. ከመቶ ሰባ አንድ እጅ
D. ከመቶ ዘጠና ሰባት እጅ

54. ለውሃ ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ መጨመር ዋና ምክንያት ምንድን ነው?

A. የዝናብ እጥረት
B. የእርሻ መስፋፋት
C. የውሃ አካላት እየጎደሉ መሄድ
D. የህዝብ ቁጥር እየጨመረ መሄድ

55. ከሚከተሉት ውስጥ ለመጠጥ የሚሆን ብዙ ውሃ የማይገኘው ከየትኛው ነው?

A. ከሃይቅ
B. ከወንዝ
C. ከዝናብ
D. ከምንጭ

56. ከሚከተሉት አገላለፆች መካከል ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

A. የሰው ልጅ ሁሉ በየቀኑ የሚወስደው የውሃ መጠን እኩል ነው::
B. ተክሎችና እንስሳት የሚወስዱት የውሃ መጠን ከሰው ልጅ ጋር እኩል ነው::
C. የሰው ልጅ በየቀኑ የሚወስደው የውሃ መጠን እንደ የአካባቢው ይለያያል::
D. ውሃ ከእፅዋት ይልቅ በእንስሳት አካል ውስጥ ብቻ ይገኛል::

57. በአለማችን ከሚገኘው የውሃ መጠን ውስጥ 97% ያህሉ የት ይገኛል?

A. በምድር ዋልታዎችና በቀዝቃዛ ስፍራዎች
B. በአለማችን በሚገኙ ባህሮችና ውቅያኖሶች
C. በሃይቆች፣ በወንዞችና በከባቢ አየር
D. በከርሰ ምድር፣ በምንጮችና በጉድጓዶች

58. "ውሃ በአለማችን እጅግ ውድ ከሆኑት የተፈጥሮ ሃብቶች ውስጥ አንደኛው ነው::" ሲባል ምን ማለት ነው?

A. በአለማችን በጣም ውዱ የተፈጥሮ ሃብት ውሃ ብቻ ነው::
B. በአለማችን ውሃ ካልሆነ በስተቀር ሌሎቹ የተፈጥሮ ሃብቶች ሁሉ በቀላሉ ይገኛሉ::
C. ውሃን ጨምሮ አንዳንድ የተፈጥሮ ሃብቶች እንደልብ የሚገኙ አይደሉም::
D. በውድነት ውሃን የሚስተካከል ሌላ የተፈጥሮ ሃብት የለም::

59. ለምንባቡ ርእስ ሊሆን የሚገባው የትኛው ነው?

A. ውሃና ጥቅሙ
B. ውሃማ አካላት
C. ጨዋማ ውሃ
D. የውሃ እጥረት

60. ምንባቡ ለየትኛው የድርሰት አይነት ምሳሌ ይሆናል::

A. ለስእላዊ
B. ለገላጭ
C. ለአመዛዛኝ
D. ለተራኪ

ኣባሪ ኣረጋ

1 የሀገር መከላከያ ሠራዊት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ፳፻፱/2004 ዓ.ም 1

የጥያቄ ብዛት:- 60

የተፈቀደው ጊዜ:- 1 ሰዓት

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 1 እስከ 10 ድረስ ሰዋስውን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጭ/ምረጥ።

1. ብዙ ቁጥር <u>ያልሆነው</u> የትኛው የስያሜ ቃል ነው?

   A. ምሁራን
   B. ተክሎች
   C. እፅዋት
   D. አንቀጽ

2. "በቃሉ የማይፀና <u>አባይ</u> ሰው አለ።" በሚለው አረፍተነገር በተሰመረበት ቃል ውስጥ ያለው "ባ" ሆሄ መነበብ ያለበት እንዴት ነው?

   A. ጠብቆ ነው።
   B. ላልቶ ነው።
   C. ላልቶም ጠብቆም መነበብ አለበት።
   D. ላልቶም ጠብቆም አይነበብም።

3. "ብርጭቆው ወድቆ _____ አለ።" ለአረፍተነገሩ ባዶ ቦታ <u>የማይስማማው</u> የትኛው ነው?

   A. እንክት
   B. ስብር
   C. ቁርጥ
   D. ድቅቅ

4. የስም ገላጭ ያለው የትኛው አረፍተነገር ነው?

   A. ውሻው ትናንት ሞተ።
   B. ቀዩ ስክሪብቶ ገነፈለ።
   C. በሬው ለምን አልተሸጠም?
   D. ሌባው እጅ ከፍንጅ ተያዘ።

5. ፈለገ _____ አስፈለገ ከሆነ፣ ጀመረ _____

A. ጀማመረ
B. አስጀመረ
C. አስጀማመረ
D. ጅማሮ

6. ድርብ ቃል **<u>ያልሆነው</u>** የትኛው ነው?

A. ህገወጥ
B. ነገረፈጅ
C. ትናንሽ
D. ወፍዘራሽ

7. "የካኪ ልብስ እንደ ሱፍ ልብስ መቀት አይሰጥም።" የሚለው አረፍተነገር ባለቤት _____ ነው።

A. ካኪ
B. ልብስ
C. የካኪ ልብስ
D. የሱፍ ልብስ

8. ባለቤቱ ገላጭ **<u>የሌለው</u>** የትኛው አረፍተነገር ነው?

A. የእርሻ መኪና የግብርና ስራን ያቀላጥፍል።
B. ግብርና የኢኮኖሚያችን መሠረት ነው።
C. የግብርና ስራ ዘመናዊ እንዲሆን ጥረት እየተደረገ ነው።
D. ውጤታማ ገበሬዎች የማበረታቻ ሽልማት ተሰጣቸው።

9. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች መካከል ተሳቢ ያለው የትኛው ነው?

A. ወታደር አስናቀ ወደ ቤተመጽሃፍት ሄደ።
B. ወታደር አስናቀ ከስልጠና ተመለሰ።
C. ወታደር አስናቀ ቤተሰቦቹን ናፍቋል።
D. ወታደር አስናቀ ብስጭት ብሏል።

1

1

10. "ፈለጠ" ብለን "አፈላለጥ" ካልን፣ "አደለ" ብለን _____ እንላለን፡፡

A. አደላደል
B. አዳዳል
C. አዳዳለ
D. አደላደለ

መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 11 እስከ 14 ድረስ የተለያዩ የሥርአተነጥብ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡

11. "ታሪኩ ብዙ ጊዜ ከትምህርት ቤት ይቀራል _ ስለሆነም የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ተሰጠው፡፡" በሚለው ለባዶ ቦታው ተገቢ የሆነው የትኛው ሥርዓተነጥብ ነው?

A. ድርብ ሠረዝ
B. ነጠላ ሠረዝ
C. የጥያቄ ምልክት
D. ትእምርተአንክሮ

12. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች መካከል ትእምርተአንክሮ (!) የሚያስፈልገው የትኛው ነው?

A. የማይጠቅም ሥራ ጊዜን ያባክናልና እንጠንቀቅ
B. የማይጠቅም ሥራ ጊዜን እንደሚያባክን ይታወቃል
C. የማይጠቅም ሥራ ጊዜን በከንቱ ያባክናል
D. የማይጠቅም ሥራ ጊዜን እንደሚያባክን የማያውቅ የለም

13. "ከመጋቢት 26 <u>እስከ</u> ሰኔ 25 ድረስ የሚቆየው ወቅት ፀደይ በመባል ይታወቃል፡፡" በሚለው አረፍተነገር የተሰመረበትን ቃል ሊተካ የሚችለው የትኛው ሥርአተነጥብ ነው?

A. እዝባር /
B. ቅንፍ ( )
C. ሙሉ ሠረዝ —
D. ነጠላ ሠረዝ ፣

1 1

14. "እህል ተፈጭቶ፣ ተለውሶ___ተበክቶና ተጋግሮ ሊበላ ይችላል።" ለባዶ ቦታው ተገቢነት ያለው የትኛው ሥርአተነጥብ ነው?

A. ነጠላ ሠረገ
B. ድርብ ሠረገ
C. ትእምርተአንክሮ
D. ትእምርተጥቅስ

መመሪያ፦ ከተራ ቁ ር 15 እስከ 27 ድረስ ቃላትንና ፈሊጦችን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጭ/ምረጥ።

15. አንዱ ቃል ለሌላው ቃል ተመሳሳይ ሆኖ የቀረበው በየትኛው አማራጭ ነው?

A. ቅጣት/ሽልማት
B. ተስፋፋ/ተንሰራፋ
C. የቀድሞ/የአሁን
D. ከፍታ/ዝቅታ

16. "ወታደር አለ የግንባር ስጋ ስለሆነ፣ ያየውን ክፉ ነገር ከመናገር አይመለስም።" የተሰመረበትን የትኛው ይተካዋል?

A. በኩን
B. ነገረኛ
C. ደደብ
D. ደፋር

17. "ወታደር አስቴር የማዕረግ እድገት ካገኘች ወዲህ ትከሻ መስጠቷን አቁማለች።" በሚለው ወታደር አስቴር ያቆመችው ምንድን ነው?

A. ትከሻ ለትከሻ መሳሳም
B. ለባልደረቦቿ አክብሮት ሰላምታ
C. ታሳይ የነበረውን ንቀት
D. በትንሽ በትልቁም ማኩረፋዋን

1

1

18. "አቶ አህመድ **አመለ ናጫ** የሆነ ባህሪውን ካልተወ እንደሚጎዳ ተነገረው።" የአቶ አህመድ ባህርይ ምንድን ነው?

A. ጨቅጫቃነት
B. ኩሩነት
C. አታላይነት
D. ቂመኝነት

19. "ወታደር ሃሊማ አሁን ለደረሰችበት ደረጃ የጠቀማት ነገር የበላች መሆኗ ነው።" አሰለፈችን የጠቀማት ምን መሆኗ ነው?

A. ምስጢረኛ
B. አስተዋይ
C. ገራገር
D. ሃይለኛ

20. "ላከከ" ብለን "አሳበበ" ብንል፣ "ላቆጠ" ብለን _____ እንላለን።

A. ተቆጣ
B. ቀለጠ
C. ጨቀየ
D. ለቀቀ

21. "ጤናማ" ብለን "በሽተኛ" ካልን፣ "ውስጣዊ" ብለን _____ እንላለን።

A. ውጭያዊ
B. ላይላዊ
C. ስራዊ
D. ታቻዊ

22. ከሚከተሉት መካከል ከሚሰጠው አገልግሎት አኳያ ከሌሎቹ የሚለየው የትኛው ነው?

A. መዳመጫ
B. እንቅብ
C. እንዝርት
D. ደጋን

23. የተለየ ፍቺ ያለው የትኛው ነው?

A. አታካች
B. አሰልቺ
C. አሽቃባጭ
D. አድካሚ

24. "ቀመቀመ" "አስተካከለ" ከሆነ፣ "ዘነጠለ _____ ነው።

A. ነጣጠለ
B. ቦተረፈ
C. ጨቀጨቀ
D. ጠመዘዘ

25. "ከውካዋ" "ቀልቃላ" ከሆነ፣ "አከንፋሽ" _____ ነው።

A. አታላይ
B. አሸርጋጅ
C. አሽሚጣጭ
D. ነገረኛ

26. "ከበደ ታማኝ እንደሆነ ሁሉ፣ ዘለቃሽም _____ ነች።

A. አመለኛ
B. ሆደቡቡ
C. ሁነኛ
D. የነቃች

27. "ሠራዊቱ <u>ግርማው</u> ያስፈራል።" የሚለው ምንን ያመለክታል?

A. ሠራዊቱ ቀትረ ቀላል እንደሆነ
B. ሠራዊቱ ሞገሳም እንደሆነ
C. ሠራዊቱ ልባም እንደሆነ
D. ሠራዊቱ የልብ አውቃ እንደሆነ

1 1

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 28 እስከ 32 ድረስ ምሳሌያዊ አነጋገርን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጭ/ ምረጥ።

28. "አንድን ሥራ እስከመጨረሻው ካላጠናቀቁት ውጤት ላይ አይደረስም።" የሚለውን የትኛው ይገልፀዋል?

A. ካጨደ የሰበሰበ።
B. አሳን መብላት በብልሃት።
C. ሥራን ለሠሪው እሾህን ላጣሪው።
D. አለባብሰው ቢያርሱ ባረም ይመለሱ።

29. ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አገላለጾች መካከል <u>የተለየ</u> መልዕክት የሚያስተላልፈው _____ ነው

A. ነገርን አዳምጠ እህልን አላምጠ።
B. ለመስማት የፈጠንህ ለመናገር የዘገየህ ሁን።
C. ለሰባቂ ጆሮህን አትስጠው።
D. መናገር ብር ነው ማድመጥ ወርቅ ነው።

30. መጥፎ ልማድ እንዲሁ በቀላሉ የማይታረምና የማይለቅ መሆኑን ለማመልከት የሚጠቅመን የትኛው ምሳሌያዊ አነጋገር ነው?

A. ሌባ ላመለ ዳቦ ይልሳል።
B. የቤት ቀጋ የውጭ አልጋ።
C. በገዛ ዳቦዬ ልብልቡን አጣሁት።
D. አመልና ጅራት በስተኋላ ይበቅላል።

31. በሚሰጠው ፍቺ <u>የሚለየው</u> የትኛው ምሳሌያዊ አገላገር ነው?

A. ዝንብ ሳያቆሙ ዝግን አይቅሙ።
B. ዳገቱን ካልወጡት ሜዳው አይገኝም።
C. በወደቀ ግንድ ምግር ይበዛበታል።
D. ጠላት ሳይነቀል ሰብል አይለቀም።

1 1

32. "ሕመም ቢኖርም ባይኖርም የኤችአይቪ ምርመራ ማድረግና ራስን ማወቅ አስፈላጊ መሆኑን የሕክምና ባለሙያዎች ይናገራሉ።" በዚህ አረፍተነገር ከተላለፈው መልዕክት ጋር የትኛው ምሳሌያዊ አነጋገር ይስማማል?

A. ያልጠረጠረ ተመነጠረ።
B. ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ።
C. ሐኪም ሲበዛ በሽተኛ ይሞታል።
D. ላለፈው አይፀፀቱም፤ ለሚመጣው አይበለጡም።

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 33 እስከ 37 ድረስ ጽሀፈትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ምረጭ።

33. የሚከተሉት አረፍተነገሮች አንቀጽ ቢመሰርት የአንቀጹን ዋና ሃሣብ የትኛው አረፍተነገር ይይዛል?

1. ሽኮኮ እግሮቹ አጫጭር ናቸው።
2. ሽኮኮ ጅራት ከናካቴው የለውም።
3. ሽኮኮ መጠኑ፣ መልኩ፣ ባህርዩ ከትልልቅ አይጦች የማይለይ አነስተኛ ፍጡር ነው።
4. ሽኮኮ ርዝመቱ እስከ ሃምሣ ሣንቲም ቁመቱ እስከ ሃያ ሣንቲም ይደርሳል።
5. ሽኮኮ ከወደ አፉ ሞጥሞጥ ያለና ጆሮዎቹ ትንንሽና ክብ የሆኑ ናቸው።

A. 4
B. 3
C. 5
D. 2

34. በህይወት ያለን የአንድን ሰው የህይወት ታሪክ ለመጻፍ በዋናነት የሚመረጠው የትኛው ነው?

A. ባለታሪኩን ከሚያውቁ ሰዎች መረጃ መሰብሰብ
B. ባለታሪኩን ራሱን በመጠየቅ መረጃ መሰብሰብ
C. ባለታሪኩን በተመለከተ የተጻፉ ጽሁፎችን ማንበብ
D. ባለታሪኩን በተመለከተ ከቅርብ ቤተሰቦች መረጃ መሰብሰብ

1 1

35. "ሕልም አልባ እንቅልፍ በአራት ደረጃዎች ሊከፈል ይችላል። ወዲያው እንደተኛን ሽለብ ያደርግናል። በዚህ ጊዜ ጡንቻዎችን ይዝናናሉ፣ የአንጐላችን የኤሌክትሪክ ሞገዶች ፈጣንና አንድ ወጥ ስርዓት የሌላቸው ይሆናሉ። እውነተኛ እንቅልፍ ወደሚባለው ሁለተኛ ደረጃ ስንሸጋገር፣ የአንጉል የኤሌክትሪክ ሞገዶች ረጅም ይሆናሉ። ሃያ በመቶ የሚሆነው የእንቅልፍ ጊዜያችንን የምናሳልፈው በዚህ ደረጃ ነው። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የእንቅልፍ ኃይል እየጨመረና እየበረታ የሚሄድባቸው ሦስተኛ እና አራተኛ የአንቅልፍ ደረጃዎች ይመጣሉ።"

የዚህ አንቀጽ ዋና ሃሣብ ምንድን ነው?

A. ወዲያው እንደተኛን የምናሸልብ መሆናችን
B. ሃያ በመቶ የሚሆነው የእንቅልፍ ጊዜያችን እውነተኛው የእንቅልፍ ደረጃ በመባል የሚታወቅ መሆኑ
C. እንቅልፋችን ሕልም አልባ የሚሆንበት አጋጣሚ ያለ መሆኑ
D. ሕልም አልባ እንቅልፍ በአራት ደረጃዎች የሚከፈል መሆኑ

36. ሰውን ማክበርና ትሁትና ታማኝ መሆን ለንግድ ስራ አስፈላጊና ጠቃሚ _____፣ የዋህ መሆንና ሙሉ በሙሉ በሰው ላይ እምነት መጣል አይገባም።
ለባዶ ቦታው ተመራጭ የሚሆነው የትኛው አያያዥ ነው?

A. ሲሆን
B. በመሆኑ
C. ስለሆነ
D. ቢሆንም

37. የሠራዊቱ የተለያዩ ኮሚቴዎች ያካሄዷቸውን ስብሰባዎች ሂደት በተሟላ መልኩ የሚያቀርበው _____ ነው።

A. ቃለጉባኤ
B. ስራደብዳቤ
C. ማመልከቻ
D. ዘገባ

1 1

መመሪያ፦ ከተራ ቁጥር 38 እስከ 47 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ምረጭ።

በቁጣ ራሳችንን መርዘን ከማጥፋት በስተቀር የምናተርፈው አንዳችም ቁብ የለም። የዚህን ገዳይ መርዝ አደገኛነት የጥንት ፈላስፎች እንኳ በጊዜያቸው ሲያስጠነቅቁ ኖረዋል። የእነሱ የማስጠንቀቂያ ደውል ደግሞ ዘመን አልፎ ዘመን በተተካ ቁጥር ጎልቶ እያስተጋባ አሁን ያለንበት ጊዜ ላይ ደርሷል። በርግጥም ቁጣ ህይወትን የሚያሰናክልና የሚያበላሽ፣ ጫን ሲልም ለህልፈት የሚያበቃ መርዝ መሆኑ በተለያዩ ጥናቶች በበቂ ሁኔታ ተረጋግጧል።

የጥንታዊቷ ግሪክ ፈላስፋ የነበረው ፓይታጎረስ "ቁጣ በሞኝነት ተጀምሮ በፀፀት ይጠናቀቃል" ብሏል። ዘመናዊው የስነ-ልቡና ሳይንስ አባባሉን ይበልጥ በሚያጠናክር መልኩ የቁጣን አደገኝነትና አስከፊ ውጤቱን ሲገልጽ፣ "ቁጣ እሳት ሆኖ በይፋ ሲገለጽ፣ እሱን ተከትሎ የሚመጣው ፀፀት ደግሞ በፈንታው ከውስጥ **ይታመቅና** እያመረቀዘ በቀፋፊ የጥፋተኝነትና የምሬት ስሜት ድብቁን አእምሮ ይመርዛል።" ይላል። የገዛ ቁጣችን ወላፈን መልሶ እኛኑ ይገርፈንና በላያችን ላይ **የማይሽር ጠባሳውን ያሳርፋል**። ጠባሳውን ደግሞ የጊዜ ርዝመትና የፀፀት ስሜት ከቶውንም ሊፈውሱትና ሊደብቁት አይችሉም።

ቁጣ የሰውን ልጅ ስብዕና በእጅጉ እንደሚያበላሽና እንደሚያጎድፍ ሲገልጽ፣ ዶን ዊብስተር የሚከተለውን ብሏል። "በተፈጥሮ እንደ ቁጣ የሰውን ልጅ እጅግ አስቀያሚና ቀፋፊ የሚያደርግ ነገር የለም" ሲል፣ የታሪክ ተመራማሪ የነበረው እንግሊዛዊው አርል ኦፍ ካልዶሮን ደግሞ፣ "ቁጣ ከተሰነዘረበት ሰው ይልቅ ይበልጥ የሚጎዳው ራሱን ተቆጪውን ነው" ብሎ ነበር።

በርግጥም ቁጣ፣ ለመጥፊያችን የምናፈልቀው መርዝ በመሆኑ፣ የበለጠ የሚጎዳው እኛኑ (ተቆጪዎቹን) ነው። እንዲህ ቢባልም ግን፣ ቁጣው የተሰነዘረበት ሰው አይጎዳም ማለት አይደለም። አሳምሮ ይጎዳል። ክፋቱ ግን አሁንም ነጥሮ ወደኛ የሚመለስ መሆኑ እንጂ። በቁጣችን ሌሎችን በመጉዳታችን ጠላትነትን እናተርፋለን። እኛም የእነሱም ቁጣ በኛ ላይ እንዲገነፍል በር እንከፍታለን። "ቁጣ ቁጣን ይወልዳል" የሚባለው ለዚህ ነው።

ምንጭ፦ ዘመን መፅሄት፣ መጋቢት 2004 ዓ.ም

1 1

38. በመጀመሪያው አንቀጽ የሚገኘውን "ቁጣ" የሚለውን ቃል የትኛው ሊተካው ይችላል?

A. ጥቃት
B. ጥቅም
C. ጥላቻ
D. ጥፋት

39. በሁለተኛው አንቀጽ "...የማይሽር ጠባሳውን ያሳርፋል..." የተባለው ምንድን ነው?

A. የጥፋተኛነትና የምሬት ስሜት
B. የፀፀት ስሜት
C. የቁጣችን ወላፈን
D. አእምሮአችን

40. በሁለተኛው አንቀጽ "**ይታመቅና**" የሚለውን ለመተካት የትኛው ይመረጣል?

A. ይጨመርና
B. ይከመርና
C. ይካተትና
D. ይታፈንና

41. የመጨረሻው አንቀጽ ዋና ሃሣብ ምንድን ነው?

A. ቁጣ ከመርገዝ እኩል ይቆጠራል።
B. ቁጣ ከተሰነዘረበት ሰው ይልቅ ክፉኛ የሚጎዳው ተቆጭው ነው።
C. ብዙ ጊዜ ቁጣ የሚሰነዘርበት ሰው አይጎዳም።
D. ቁጣው የሚሰነዘርበት ሰው እንደ ተቆጭው በቁጣው ክፉኛ ይጎዳል።

42. ቁጣ ለህይወት አስጊ መሆኑ _____።

A. ተረጋግጧል
B. ወደፊት የሚረጋገጥ ይሆናል
C. የሚረጋገጥበት ጊዜ ቅርብ ነው
D. አልተረጋገጠም

1 1

43. በምንባቡ ውስጥ ቁጣ ከምን ጋር ተነፃፅሯል?

A. ከሞኝነት ጋር
B. ከምሬት ጋር
C. ከፀፀት ጋር
D. ከመርዝ ጋር

44. በምንባቡ መሠረት ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

A. ቁጣ የሚጎዳው ተቆጪውን ብቻ ነው።
B. ቁጣ ተቆጭውንም ቁጣው የሚሰነዘረበትንም እኩል ይጎዳል።
C. ቁጣ ተቆጭውን የበለጠ ቢጎዳም፣ ቁጣ የሚሰነዘረበትም መጎዳቱ አይቀርም።
D. ቁጣ ገዳይ መርዝ ሆኖ ለህልፈት የሚያበቃው የተወሰኑ ሰዎችን ነው።

45. በምንባቡ የተላለፈው መልዕክት ምንድን ነው?

A. ቁጣችንን በልክ እናድርገው።
B. ቁጣችን ሌላውን ሰው የማይጎዳ መሆኑን እናረጋግጥ።
C. ከቁጣ የሚገኘው ጉዳት እንጂ ጥቅም አይደለምና ከቁጣ እንታቀብ።
D. ከቁጣ በኋላ መፀፀት ሊለመድ ይገባል።

46. ምንባቡ ለየትኛው የድርሰት ዓይነት ምሣሌ ይሆናል?

A. ለአመዛዛኝ
B. ለተራኪ
C. ለስእላዊ
D. ለገላጭ

47. የምንባቡ ርእስ ቢሆን የሚመረጠው የትኛው ነው?

A. ፀፀት
B. መርዝ
C. ቁጣ
D. ህልፈት

1 1

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 48 እስከ 60 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጭ/ምረጥ።

48. ከሚከተሉት ውስጥ ለስነቃል.ምሣሌ ሆኖ <u>የማይቀርበው</u> የትኛው ነው?

A. ምሣሌያዊ አነ.ጋገር
B. እንቆቅልሽ
C. ተረት
D. ልቦለድ

49. በአንድ ግጥም ውስጥ ሙሉ ስሜትን የሚ.ያሳይ የግጥም ክፍል ምን ይባላል?

A. ሃረግ
B. ስንኝ
C. አንጓ
D. ቤት

50. በአንድ የግጥም ሃረግ 6 የሚነበቡ ቀለማት ያሉት የትኛው ሃረግ ነው?

A. የወል ቤት
B. የቡሄ በሉ ቤት
C. የስንኅ መገን ቤት
D. አይታወቅም

51. ከሚከተሉት ዐረፍተነገሮች መካከል ስለኤችአይቪ ሃቅነት ያለው የትኛው አረፍተነገር ነው?

A. የግብረስ.ጋ ግንኙነት ከማድረግ በመታቀብ ብቻ ከኤችአይቪ ራስን መከላከል ይቻላል።
B. የኤችአይቪ ምርመራ ማድረግ ያለባቸው ለኤችአይቪ የተ.ጋለጡ ሰዎች ናቸው።
C. .ጋብቻ ፈፃሚዎች እስከተማመኑ ድረስ የኤችአይቪ ምርመራ ማድረግ አያስፈል.ጋቸውም።
D. ማንኛውም ሰው የኤችአይቪ ምርመራ እስካላደረገ ድረስ ከቫይረሱ ነፃ ነኝ ማለት አይችልም።

52. "አንድን ግለሰብ ወይም ሁኔታ ለመግለፅ የሚያገለግሉ ቃላትና ምስሎች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት ሊኖራቸው ይችላል። አንድን ግለሰብ በአካል ጉዳቱ ላይ በመመርኮዝ መፈረጅን ያስወግዱ! አካል ጉዳቱን ሣይሆን ግለሰቡን ይጥቀሱ!።" የሚለው ማሳሰቢያ በሌላ አባባል ሲቀርብ የትኛው ትክክል ይሆናል?

A. አንድን ግለሰብ ወይም ሁኔታ ለመግለፅ የሚያስችሉ የተለያዩ ቃላትና ምስሎች አሉ።
B. አንድን ግለሰብ ለመግለፅ የምንጠቀምባቸው ቃላትና ምስሎች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት ሊኖራቸው ይችላልና እንጠንቀቅ!
C. አንድን ግለሰብ ወይም ሁኔታ ለመግለፅ የሚያገለግሉ ቃላትና ምስሎች እንደሁኔታው ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።
D. አንድን ግለሰብ ወይም ሁኔታ ለመግለፅ የሚያገለግሉ ቃላትና ምስሎች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል!

53. ከአረፍተነገሮቹ መካከል ለግል አስተያየት ምሣሌ የሚሆነው _____ ነው።

A. ታላቁ የህዳሴ ግድብ በአምስት ዓመት ውስጥ ይጠናቀቃል።
B. የመጻህፍትን የውስጥ ገፆች የሚቀዱ ተማሪዎች ያለምንም ርህራሄ በእስራት መቀጣት አለባቸው።
C. ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ሀገሮች መካከል አንዷ ናት።
D. በአፍሪካ አህጉር 54 ሀገራት ይገኛሉ።

54. "ሠራዊቱ የተሰጠውን ግዳጅ በሙሉ ጀግንነት _____ ተመለሰ።" ለባዶ ቦታው <u>የማይስማማው</u> የትኛው ነው?

A. ዳር አድርሶ
B. አሳክቶ
C. ፈፅሞ
D. ረክቶ

1 1

55. ከአንድ የውይይት አወያይ የትኛው ይጠበቃል?

A. የውይይቱ ተሣታፊዎች እርስ በርስ እየተወያዩ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ማበረታታት
B. የውይይቱ ተሣታፊዎች ከውይይቱ ርዕስ ጉዳይ አኳያ ሃሣብ ማቅረባቸውን ማረጋገጥ
C. የውይይቱ ተሣታፊዎች በሙሉ ተመሳሳይ አስተያየት እንዲሰነዝሩ ማበረታታት
D. በውይይቱ ሂደት ተሣታፊዎች የእርሱን አቋም እንዲያንፀባርቁ መገፋፋት

56. የ8ኛ ክፍል የሳይንስ መጽሐፍ ከየትኛው ይመደባል?

A. ከፈጠራ ጽሁፍ
B. ከኢልቦለድ
C. ከልቦለድ
D. ከዘገባ

57. "ያህል" የሚለውን ቃል ፍቺ ከመዝገበቃላት ፈልገን ለማግኘት የትኛው ቃል ይጠቅመናል?

A. እህል
B. ይህ
C. አከለ
D. አለ

58. ከአንድ የቤተመጻህፍት ተጠቃሚ ምን ይጠበቃል?

A. የመጻህፍት አፈላለግ ስርዓትን ማወቅ
B. በሚያነቡት መጽሃፍ ውስጥ ቁምነገሮች የሚገኙባቸውን ገፆች በማጠፍ ከንባብ በኋላ ማስታወሻ መውሰድ
C. መጻህፍትን እያነበቡ ከጓደኛ ጋር የሃሳብ ልውውጥ ማድረግ
D. በሚያነቡት መጽሃፍ ውስጥ የሚገኙ ጠቃሚ ቁምነገሮችን ማስመር

1 1

59. ስለ ሂስ ንባብ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

A. ሂሳዊ ንባብ የአንድን ልቦለድ ጠንካራ ጎን ብቻ ለመለየት ይጠቅማል።
B. በሂሳዊ ንባብ ስለ አንድ ልቦለድ ቅርፅ ጠንካራና ደካማ ጎን አስተያየት ይቀርባል።
C. በሂሳዊ ንባብ የአንድ ልቦለድ ይዘት ጠንካራና ደካማ ጎን ይለይበታል።
D. ሂሳዊ ንባብ የአንድን ልቦለድ ጠንካራና ደካማ ጎን ከቅርፅና ከይዘቱ አኳያ ለመለየት ይጠቅማል።

60. ለክርክር የሚያመቸው የትኛው ርእሰ ጉዳይ ነው?

A. ታላቁ የህዳሴ ግድብ የኢትዮጵያ ኩራት ነው።
B. ለታላቁ የህዳሴ ግድብ የቦንድ ግዥው እንደቀጠለ ነው።
C. ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ጎረቤት ሃገሮች ያላቸውን ድጋፍ መግለፃቸው ያስደስታል።
D. ታላቁ የህዳሴ ግድብ ለኢትዮጵያ እንጂ ለጎረቤት ሃገሮች ምንም ፋይዳ የለውም።

ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለጸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ የአማርኛ ማስተማር መረሃ ግብር ተማሪ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የራስ ስራ ስለመሆኑንና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኳቸውን ተዛማጅ ጽሑፎች እና የመረጃ ምንጮች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም _____

ፊርማ _____

አድራሻ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የማስረከቢያ ቀን ሰኔ 2005 ዓ.ም